አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድኅረ ምረቃ ት/ቤት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

A. A. UNIVERSITY
LIBRARIES

# በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በድፕሎማው መርሀ-ግብር የሚሰጡ አቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ትንተናና ግምገማ

ደረጀ ገብሬ

ሰኔ 1986

# በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ
# በዲፕሎማው መርሀ-ግብር የሚሰጡ አበይ የአማርኛ
# ኮርሶች ይዘት ትንተናና ግምገማ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት
የቀረበ ጥናት /ቴሲስ/

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ቤተ መጻሕፍት
ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES

በቋንቋዎች ጥናት ተቋም
አማርኛን በማስተማር ዘዴ
ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ
ይረጋ ገበሬ

1986

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በዲፕሎማው መርሀ-ግብር የሚሰጡ አቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ትንተናና ግምገማ

በ
ደረጀ ገበሬ
ዶንዶያች ጥናት ተዶም

<u>የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ</u>

[illegible] (ዶ/ር) ______
አማካሪ
[illegible] (ዶ/ር) ______
ፈታኝ
[illegible] ______
ፈታኝ

## አጠቃሎ / Abstract/

ይህ ጥናት በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በዲፕሎማ መርሀ-ግብር ለአማርኛ መምህርነት የሚሰለጥኑ ዕጩ መምህራን ከሚወስዷቸው ኮርሶች ውስጥ አበይት የሆኑትን የአማርኛ ኮርሶች ይዘት በመተንተንና በመገምገም ላይ ያተኮረ ነው።

ጥናቱ በአገራችን የአማርኛ የመምህራንን ሥልጠና የሚመለከቱ ጥናቶችን በመቃኘት የተሰነዘሩ አስተያየቶችን ለመዳሰስ ሞክሯል። ለቋንቋ መምህርነት ለሚሰለጥኑ ዕጩ መምህራን ስለሚቀርቡ ኮርሶች ይዘት ለመረዳት እንዲቻል ንድፈ ሀሳባዊ መንደርደሪያዎችንና የመተንተኛ ስልቶችን የሚያስጨብጡ ዝግጅ ጽሁፎችን ቃኝቷል።

በተደረገውም የዝግጅ ጽሁፍ ቅኝት አማካይነት ጥናቱ ሊተኮርባቸው አቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት መተንተኛና መመዘኛ የሚሆኑ መስፈርቶች ወጥተዋል። የወጡትም መሥፈርቶች የቋንቋ ክሂሎችን፣ ቋንቋና ሥነ-ልሳንን፣ የቋንቋ አገልግሎትን፣ ቋንቋን የማስተማር ዘዴዎችን፣ ቋንቋ መፈተንንና ለቋንቋ ትምህርት ድጋፍ መረጃ የሚሰጡ ኮርሶችን የሚመለከቱ ናቸው።

በነዚህ መስፈርቶች አማካይነት አቢይ የአማርኛ ኮርሶች፣ ይዘት ሊጠቀሙ የሚችሉት የየኮርሶቹ ዓላማዎች፣ ቢጋሮች፣ የተማሪዎች ማስታወሻዎችና የመጨረሻ ፈተናዎች የያዙ ሰነዶች ተመርምረው ተተንትነዋል። የሰነዶችን ትንታኔ የበለጠ ለማዳበር ለተማሪዎች መጠይቅ ቀርቦ ከመጠይቁ የተገኘው ምላሽ በየርዕስ ጉዳዮቹ ስር ተተንትኗል።

ከሰነዱና ከመጠይቁ ትንታኔ የተገኙት መረጃዎች በሙሉ ተጠቃለው ሲታዩ በአቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ውስጥ ሊተኮርባቸው የሚገቡ የቋንቋ ክሂሎችን የሚመለከቱ ኮርሶችና ቋንቋን የመፈተን ጉዳይ ተገቢው ትኩረት ያልተሰጣቸው መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል። የሌሎቹም ኮርሶች ይዘት አቀጣጣውን አማርኛ ቋንቋን ከማስተማር ዓላማ ጋር ስለማገናዘቡ ታይቷል።

በዚህ መሠረት በአማርኛ ኮርሶች ይዘት በኩል ሊተኮርባቸው የሚገቡ የመፍትሔ ሀሳቦች ቀርበዋል። ከቀረቡትም የመፍትሔ ሀሳቦች ውስጥም የቋንቋ ክሂሎች ራሳቸውን ችለው ቢቀርቡ የተሻለ መሆኑንና ቋንቋን የመፈተን ጉዳይም ትኩረት ሊሰጠው የሚሉት [illegible]

# ምስጋና

ይህ ጥናት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በየደረጃው የሚያጋጥሙ የምርምር ችግሮችን ለመፍታት እንድችል ያሳሰለሰ ምክራቸውን ለለገሱኝና ረቂቁን በማረምና ገንቢ አስተያየት በመስጠት ለረዱኝ አማካሪዬ ለዶር. ታደለ አጎሙ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ።

ጥናቴን ሳካሂድ ሳጋጠሙኝ አንዳንድ አደናቃፊ ሁኔታዎች ውይይም ሆነ ዐንድማዊ ድጋፋቸው ሳልተለየኝ ለዶር. ደጀኔ ለታ ለዶር. ኀይሉም ባንቲርጉ፣ ለዶር. ይመር ከፍሌ፣ ለአቶ ዘሪሁን አስፋው ለአቶ ተክሉ ገ.ማርያም ለአቶ ጌትነት ተዐዘዙና ለአቶ ብርሃኑ ገበየሁ ከፍ ያለ ምሥጋና አቀርባለሁ።

የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ ዲንና ረዳት ዲን፣ በኮሌጁ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል መምህራን በሙሉና በተለይ አቶ ጌታሁን አማረ ያደረጉልኝ ትብብር የማይረሳ ነው።

እህቴ ወ/ት ፋንታዬ ሽመልስ እህት ብቻ ሳትሆን እናትም ሆና ቤተሰቧና ማህበራዊ ጉዳዮችን ሁሉ የተሸከመችልኝ በመሆኑ ከአንጀቴ አመሰግናታለሁ።

ወ/ሮ ጽጌረዳ ታደለና ወ/ት ጽሳት አዱነው የጽሁፉን ረቂቅ በመተየብና አስፈላጊውን እርማት በማድረግ ስለረዱኝ በጣም አመሰግናቸዋለሁ። በዚህ ረገድ ወ/ሮ ንጋቷ ብሩና ወ/ት ብፁዓት አየለም ባለውለታዎቼ ናቸው።

| አርዕስት | ገጽ |
|---|---|


አጠቃሎ

ምስጋና

የሰንጠረዥ ዝርዝር

ምዕራፍ አንድ

1. መግቢያ ............................ 1

1.1 የጥና ቱ ዳራ ......................... 1

1.2 የጥና ቱ ዓላማ ........................ 5

1.3 የጥና ቱ ጠቀሜታ ...................... 6

1.4 የጥና ቱ ክልል ........................ 7

1.5 የጥና ቱ ገደብ ........................ 8

1.6 የጥና ቱ ዘዴ ......................... 8

1.7 የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ አጭር ታሪክ... 9

ምዕራፍ ሁለት

2. የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት .................... 12

2.1 የመምህራን ሥልጠና፡- በጠቅላላ ............ 12

2.1.1 የመምህራን ሥለጠና አስፈላጊነት ...... 14

2.1.2 በቋንቋ መምህር ሥልጠና የጠቅላላ ትምህርት ትምህር ቶች ጠ ቀሜታ ............... 15

2.1.3 በቋንቋ መምህር ሥልጠና ዐቢይ የሙያ ኮርሶች ቀጠሜታ ................. 17

2.1.4 በ ተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት መሠረትነት የ ተውጣጡ መሥፈር ቶች ............ 26

2.2 የይዘት ትን ተና ምን ነት አገልግሎቱና የምርምር ስልትነት ....................... 29

2.2.1 የይዘት ትን ተና ምን ነት ........... 29

2.2.2 የይዘት ትን ተና አገልግሎት ......... 30

2.2.3 የይዘት ትን ተና ሥልት/የአሠራር ሥርዓት/ [illegible]

ምዕራፍ ሦስት

3. የጥናቱ አሠራር ዘዴና የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች.... 35
3.1 የአሠራር ዘዴ ........................ 35
3.2 የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች................ 36
3.2.1 የሰነድ ምርመራ .................. 36
3.2.1.1 ዓላማና ቢጋር ............. 36
3.2.1.2 የተማሪዎች ማስታወሻ ደብተር
አመራረጥና ምርመራ .......... 36
3.2.1.3 የመጨረሻ ፈተና ............ 38
3.2.2 የጽሑፍ መጠይቅ .................. 38

ምዕራፍ አራት

4. የአቢይ ክርክሮች ይዘት ትንተናና ግምገማ ........... 40
4.1 የይዘት ትንተናና ግምገማ—ጠቅላላ.............. 40
4.2 የክርክሮች ሥርጭት ..................... 41
4.2.1 የዲኘሎማ መርሀ-ገብር ክርክሮች ሥርጭት ..... 41
4.2.2 የአቢይ ክርክሮች ስርጭት ............. 41
4.3 የአቢይ ክርክሮች ይዘት ትንተና ............. 46
4.3.1 የተሟላ የቋንቋ ችሎታ መኖር ........... 46
4.3.1.1 የሰነድ ትንተና ............. 46
4.3.1.2 የቋንቋ ክሂሎችን የሚመለከት ከመጠይቅ
የተገኙ መልሶች ትንተና ........ 49
4.3.2 የቋንቋ ባህርይና የሥነ-ልሣን ሚና ....... 53
4.3.2.1 የሰነድ ትንተና ............. 53
4.3.2.2 የመጠይቅ ትንተና ............ 58
4.3.3 የቋንቋን አገልግሎት/ጠቀሜታ መገንዘብ...... 59
4.3.3.1 የሰነድ ትንተና ............. 59
4.3.3.2 የመጠይቅ ትንተና ............ 62

4.3.4 አማርኛ ቋንቋን የማስተማር ዘዴ ............ 63
4.3.4.1 የስነጽ-ትንተና ............... 63
4.3.4.2 ከመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና.... 65
4.3.5 ቋንቋን መፈተን ..................... 68
4.3.5.1 የስነጽ ትንተና ............... 68
4.3.5.2 የመጠይቅ ትንተና .............. 69
4.3.6 ተጓዳኝ መስኮች ..................... 70
4.3.6.1 የስነጽ ትንተና ............... 70
4.3.6.2 የመጠይቅ ትንተና .............. 72
4.4 አቢይ ኮርሶችን በጠቅላላው የሚመለከት ከመጠይቁ የተገኙ መልሶች ትንተና ..................... 73
4.4.1 የጥያቄ 9 እና 12 መልሶች ትንተና ........ 73
4.4.2 የክፍት ጥያቄዎች 17፣18፣19 መልሶች ትንተና.. 75
ምዕራፍ አምስት
5. ማጠቃለያ፣መደምደሚያና የመፍትሔ ሀሳቦች ............ 78
5.1 ማጠቃለያ ....................... 78
5.2 መደምደሚያ ...................... 80
5.3 የመፍትሔ ሀሳቦች .................. 82
ዋቢ መጽሐፍት 83
አባሪዎች 1 የዘገባ አፃፃፍና ሂሳዊ ንባብ 87
2.1 የቋንቋና የሥነ ልሣን መግቢያ 88
2.2 የቋንቋና የሥነ ልሣን መግቢያ 90
2.3 አማርኛ ሰዋሰው 92
2.4 አማርኛ ሰዋሰው 94
2.5 የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ቅኝት 96

አባሪዎች 3.1 የሥነ-ጽሑፍ መሠረታውያን 98

3.2 የአማርኛ ሥነ-ግጥም 99

3.3 ተውኔት/ድራማ 100

4.1 አማርኛን የማስተማር ልዩ ዘዴ 102

4.2 አማርኛን የማስተማር ልዩ ዘዴ 104

4.3 ሴሚናር በማስተማር ዘዴዎች 105

5.1 የመጀመሪያ ደረጃ ግዕዝ 106

5.2 የትርጉም መግቢያ 107

6. መጠይቅ 108

# የሰንጠረዥ ዝርዝር


| ሠንጠረዥ | | ገጽ |
|---|---|---|
| 1 | የዲፕሎማ መርሀግብር ኮርሶች ስርጭት .............. | 41 |
| 2 | የአብይ ኮርሶች ስርጭት ...................... | 45 |
| 3 | የቋንቋ ክሂሎችን የሚመለከቱ ከመጠይቅ የተገኙ መልሶች... | 50 |
| 4 | ስለ ስነ ልሣን ዒና ከመጠይቅ የተገኙ መልሶች ........ | 58 |
| 5 | የአማርኛ ቋንቋ ልዩ ልዩ አገልግሎት ............. | 62 |
| 6. | ቋንቋ ማስተማር ዘዴን የሚመለከቱ ከመጠይቅ የተገኙ መልሶች .......................... | 67 |
| 7 | የቋንቋ ፈተናን የሚመለከቱ ከመጠይቅ የተገኙ መልሶች ... | 69 |
| 8 | ተጓዳኝ መስኮችን የሚመለከቱ ከመጠይቅ የተገኙ መልሶች .......................... | 72 |
| 9 | አጠቃላይ አቢይ ይዘቶችን የሚመለከቱ ከመጠይቅ የተገኙ መልሶች .......................... | 74 |

## ምዕራፍ አንድ

# 1. መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

በአገራችን መምህራንን በዘመናዊ ዘዴ የማሰልጠን ተግባር የተጀመረው በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ቅጥረ ግቢ ውስጥ በ1937 ዓ.ም ነበር:: /ት/ሚ፤ 1983 ኢት.አ፣ አብርሃም ሁሴን፤,1990/*:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሊያስተምሩ የሚችሉ መምህራንን የማሰልጠን እንቅስቃሴ ቀስ በቀስ እየተጠናከረ መጥቷል:: በአብዛኛዎቹ የትምህርት መስኮችም በኮሌጅ ደረጃ ሊያስተምሩ የሚችሉ መምህራንን የሚያሰለጥኑ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማትም ተቋቁመዋል::

ይሁንና ያሉን የመምህራን አሰልጣኝ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ መምህራንን ለማሰልጠን ዓላማቸው አድርገው ይነሱ እንጂ ለዕጩ መምህራኑ የሚያቀርቧቸው ትምህርቶች ተፈላጊውን የሥልጠና ይዘት መምህሩ ወጥቶ ከሚሰማራበት ሥራ ጋር አገናዝበው እንደማያቀርቡ በቅርብ ጊዜ የተደረጉ ጥናቶች ይጠቁማሉ /ት/ሚ፤ 1983 ኢት.አ.፣ አብርሃም ሁሴን፣ 1990፣ ሀይሌም ባንተይርጋ፤ 1992፣ ሀብታሙ፣ 1994/::

በመሠረቱ በመምህርነት ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ለሚሰለጥኑ ዕጩ መምህራን የሚቀርብላቸው የሙያ ሥልጠናና ልምምዱ የተማሪውን አዳጊ ችሎታ ለማነቃቃት፣ ለመጉትጎትና ለማሳደግ የሚያስችል፤ ተጨባጩን ዓለምና የሕብረተሰብ የእርስ በእርስ ግንኙነት እንዲሁም በውስጡ የሚያከናውነውን የለውጥ ሂደት /እንቅስቃሴ/ ለመረዳት የሚያበቃ ዝግጅት እንዲኖረው ለመረዳት የሚያስችላቸው መሆን አለበት እንጂ የተማሩትን በማስተማር ወይም ያገኙትን ዕውቀት እንዳለ በማስተላለፍ ላይ የሚያተኩር መሆን የለበትም/ዓለም አቀፍ የትምህርት ቢሮ፤ 1973:41/::

ዓለም አቀፍ የትምህርት ቢሮ ከዛሬ ሃያ ዓመት በፊት ያስገነዘበው ከላይ የተገለፀው ሀሳብ አሳሳቢነት አሁንም ቢሆን ያለና የቀጠለ ይመስላል::

---

*በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ያሉት ዓመተ ምህረቶች ኢት.አ. የሚል መጠቆሚያ ካልተከተላቸው በስተቀር የአውሮፓውያንን የዘመን አቆጣጠር የሚያመለክቱ ናቸው::

ለሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ ብቁ የሚያደርጋቸው ሙያ ስልጠና ያላገኙ መምህራን በማስተማር ሥራ ላይ እንደሚሰማሩ ፤ ኃይሌ ወ/ሚካኤል፣ "የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት አስተዳደር ከሚያስፈልገው በታች ሥልጠና ያላቸው በርካታ መምህራን እንዲቀጠሩ ያደርጋል" /1976:33+/ በማለት የገለጹት እውነታ ከዚያም ወዲህ በተከታታይ በተደረጉ ሌሎች ጥናቶች ተደግፏል /ተ/ሚ፤ 1983 ኢት.እ. ላስት 1989/::

አጠቃላይ ከሆነው የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ሥልጠና ተነስተን ወደ አማርኛ መምህራን ሥልጠና ስንመጣ፤ ቶኔስኮ በ1988 ባሳተመው የሁለተኛ ደረጃ መምህራንን ሥልጠና በሚመለከት ሰነዱ ውስጥ የቋንቋ መምህርም በሚመደብበት የቋንቋ ማስተማር ሥራ ብቁ ሆኖ ተፈላጊውን ውጤት እንዲያስገኝ በተገቢ ሥልጠና ውስጥ ማለፍ ይኖርበታል፤ ሲል ያቀረበው ሃሳብ በአገራችን መምህራንን የማሰልጠን እንቅስቃሴ ውስጥ ተሟልቶ ይገኛል ለማለት አያስደፍርም::

በሀገራችን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች እስከ 1950ዎቹ /ኢት.እ./ መጨረሻ ድረስ ሲያስተምሩ ከነበሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ውስጥ አብዛኞቹ ተፈላጊው እውቀትና ችሎታ እንዳልነበራቸው በወቅቱ የተደረገ ሴሚናር ላይ የቀረበ ጥናት ይጠቁማል /ተ/ሚ እና ቀ.ኃ.ሥ.ዩ. ትምህርት ፋኩልቲ 1959 ኢት.እ./::

በ1959 ዓ.ም /ኢት.እ./ በተደረገው በዚያ ሴሚናር ላይ ከቀረቡት የጥናት ወረቀቶች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን ሥልጠናና የማስተማር ብቃት የሚያሳይ ሀተታ ይገኛል:: በውስጡም፣ በወቅቱ ከነበሩት የአማርኛ መምህራን መካከል "...አብዛኞቹ የትምህርት ደረጃና የማስተማር ዘዴ ያንሳቸዋል"/ገጽ 3/ የሚል ነጥብ ሰፍሮ ይገኛል:: በተጨማሪም ቀደም ሲልና በዚያን ወቅት የነበሩትን መምህራን ትምህርትና ሥልጠና የሚገመገመው ይኸው ጥናት እንደሚያትተው አማርኛን እንዲያስተምሩ ይመደቡ የነበሩት መምህራን ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ስር ተደከስ ቤተክርስቲያን የሚሰጠውን የግዕዝ ትምህርት የተማሩ እንጂ አማርኛን ለማስተማር የሚያስችላቸው ዕውቀትም ሆነ ሥልጠና ያልተሰጣቸው እንደነበሩ ጌታቸው ኃይሌ/1959:10 ኢት.እ/ "...በዚያን ጊዜ ግን ግዕዝን የተማሩ እንጂ አማርኛን [illegible]

በማለት ጽፈውት ይገኛል።

ከላይ የጠቀስነው በጎታቸው ኃይሉ የተጠቀመው ፅውነታ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተመራቂ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የሚያስለጥኑ ክፍለ ቤና ባሕርዳር መምህራን ኮሌጆች በመቋቋማቸው መሻሻል ማሳየቱ ቢታመንም ችግሩ የሚፈለገውንና መሆን የሚገባውን ያህል ያልተቃለለና እስካሁን ድረስም የቀጠለ መሆኑን በት/ሚኒስቴር/1983 ኢት.አ/ የተደረገ ጥናት ያመለክታል። በዚህ ጥናት ውስጥ በተለይ የአማርኛ መምህራንን ሥልጠናና ምደባ በማመለከት ከዚህ በታች የቀረበው ሃሳብ ሰፍሮ ይገኛል።

> በማስተማር ላይ ያሉት የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ መምህራን ሁኔታ በትምህርት ዓይነቶችና በትምህርት ደረጃ አንፃር በዝርዝር ሲታይ በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ በአማርኛ 21.5 ...ያህል የሚገኙማና ከዚያም በላይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ሲሆኑ የቀሩት ከሚገኙት በታች ብሉ የነኛ ደረጃ መምህራን ተከፍሏል። በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃም ያለው ሁኔታ ሲታይ በአማርኛ 39.3.% ...ያሁ የሚገሪ ምሩቃን ሲሆኑ የተቀሩት ከአለው ስታንዳርድ አኳያ ሲታይ ከሚፈለገው በታች የትምህርት ደረጃ ባላቸው መምህራን የተሸፈነ ነው /ት/ሚ፣ 1983፡8/።

በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሊያስተምሩ የሚችሉ የአማርኛ መምህራንን የማሰልጠን እንቅስቃሴ አጀማመር ስንመለከት ስስት የተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን እናገኛለን። የመጀመሪያው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ሁለተኛው የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ነው። ሦስተኛው ደግሞ የባህርዳር መምህራን ትምህርት አካዳሚ ነው። በተለያዩ ጊዜያት የተከፈቱት እነዚህ ተቋማት ለተለያዩ ደረጃዎች ብቁ ናቸው የሚሏቸውን የአማርኛ መምህራን አሰልጥነው በማውጣት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ /ት/ሚ፣ 1983 ኢት.አ./።

ከላይ ከተጠቀሱት ተቋማት ውስጥ ሰልጥነው የሚወጡ መምህራን በሚሰማሩባቸው ትምህርት ቤቶች ተጠቃሚ የሚሆኑ ተማሪዎች ከአማርኛ ቋንቋ ጋር ስላላቸው ግንኙነት በቂ መረጃ አገኘተዋል ለማለት አያስደፍርም። አማርኛ በአፍ መፍቻነት በሚነገርበት አካባቢ አማርኛን ለማስተማር የሚመደቡ መምህራን እንዳሉ ሁሉ

አማርኛ በአፍ መፍቻነት በማይነገርበትና በሁለተኛ ቋንቋነት ደረጃ በሚገኝበት /በወን፡1976፡469/ እና የአካባቢው ቋንቋ በተለያዩ ማህበራዊ ገለጋሎቶች ከፍ ያለ ሚና በሚጫወትበት አካባቢ ባሉ ት/ቤቶች የሚመደቡ መምህራንም አሉ፡፡ ነገር ግን አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለማስተማር ምን ምን ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚያስፈልግ የሚያመለክት የስልጠና ይዘት በአስለጣኝ ተቋማት በኩል የቀረበ ለመሆኑ መረጃ አልተገኘም፡፡ ይልቁንም በአስለጣኝ ተቋማት ውስጥ የሚሰጠው የሥልጠና ትምህርቶች ይዘት በዚህ ረገድ ትኩረት ያልተደረገበትና የአካባቢውን ተጨባጭ ዕውነታ የማያገናዝብ፣ ከአጠቃላይ የአገሪቱ ሥርዓተ ትምህርትም ጋር ያለው ግንኙነትና ዝምድና እጅግን የላላ መሆኑን መረዳት ተችሏል/ተ/ሚ፣ 1983 ኢት.አ/፡፡

ይሁንና አማርኛን ለማስተማር እየሰለጠኑ የሚወጡ መምህራን ስለአስለጣጠናቸው ሁኔታ፣ ስለሚሰለጥኑባቸው ትምህርቶች ይዘትም ሆነ ሥነ-ዘዴ በውል የሚያሳይ፣ የሚተነትን ወይም የሚያብራራ ጠለቅ ያለ ጥናት አለመገኘቱን ከላይ ብንጠቅምም በ1986 ዓ.ም /ኢት.አ/ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በአማርኛው ትምህርት ክፍል ላይ አንድ ጥናት በሣህሉ አከሉ ለሴሚናር ቀርቧል፡፡

ሣህሉ አከሉ ያቀረቡት ጥናት የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ባዘጋጀው ሁሉን አቀፍ ሴሚናር ላይ <u>በአማርኛ ቋንቋ ንዑስ የማስተማር ልምምድ ውስጥ የተማሪ አስተማሪዎች ይዘትንና የማስተማር ዘዴዎችን ማዘመድ</u> የሚል ነው፡፡ በመነሻውም፤

> ይህ ጥናት በኮተቤ መምህራን ኮሌጅ በአማርኛ ቋንቋ የማስተማር ስልጠና ውስጥ የሚመደቡ መደበኛና የማታ ተከታታይ የሚገኙት ተማሪዎች የንዑስ ማስተማር ልምምድ ሲያደርጉ ለሚመርጡት አርእስት ተስማሚ የሚሆኑትን የማስተማሪያ ዘዴዎች ለመምረጥ ስለሚያቀታቸው ምክንያቶን ለማመልከት የተደረገ ነው /ሣህሉ፣1986፡1/

ይላል፡፡ ይህን ሃሳብ ዓላማ በማድረግ ከቀን 24፣ ከማታ ደግሞ 29 ተማሪዎች የተካተፉበት ጥናት አካሂደው የደረሱበት ማጠቃለያ ወይም መደምደሚያ፤

> በመደበኛም ሆነ በማታ ተከታታይ የንዑስ ማስተማር ልምምድ ክትትል የተደረገባቸው ተማሪዎች የመረጧቸውን የማስተማሪያ አርእስት በቋ [illegible] ... የንዑስ ማስተማር ልምምድ ትምህርት ለመደበኛ

> ተማሪዎች በአንደኛ ዓመት ሁለተኛ ሴሚስተር ላይ የሚሰጥ በመሆኑ ለንባብ ማስተማር ለምምድ ለ ሶ ያቶ አርአስት የሚያስፈልጋቸውን ገንዘቤ ከትምህ ርት ክፍሉም አላገኙም /ገጽ 25/

የሚል ሲሆን አንደ ወፍተሴ ያቀረቡት ሃሳብ ደግሞ፣

> የትምህርት ክፍሉ ሥርዓተ ትምህርቱን በሚገመግም በት ጊዜ ተቀራራቢ በሚሆኑት ትምህርቶች ዎትክ አንዳንዱ የትምህርት ዓይነቶች ለምባሌ መሠረታዊ የሆርስት አጻጻፍና ሥነ-ቃል ቢታከልበት ጠቃሚ ይሆናል /ገጽ 26/::

ይላል::

ከዚህ በላይ ከቀረበው የሣህሉ ጥናትና አስተያየት በስተቀር የአማርኛን ቋንቋ ለማስተማር ለሰልጥ ነዋል ብለው በሥራው ላይ የሚወደቡት መምህራን ለሚሰማ ሩበት የሙያ ዘርፍ ብቁ የሚያደርጋቸው ንድፈ ሃሳብንና ተግባርን ያጣመረ ሥልጠና ማግኘት አለማግኘታቸውን፣ አሰልጣኝ ተቋማትም የሚያቀርቧቸው ሙያዊ ትምህርቶች ተፈላጊውን ዕውቀት፣ ችሎታና ልምምድ የሚያስጨብጡ መሆን አለመሆናቸውን የገመ ገመና ያሳየ ዝርዝር ጥናት አላጋጠመንም::

በተቋሙ ውስጥ በእጩ የአማርኛ መምህራን ስለሚቀርቡት፣ የትምህርት ዓላማ፣ ይዘት፣ የማስተማር ዘዴ፣ የመገምገሚያ መሣሪያዎች፣ የማስተማሪያ ጽሑ ፎች ብቃትና ጥራት፣ ምላትና ጉድለት የሚያስረዱ ሐተታዎች አልተገኙም/አበር ሃም ሁሴን፣ 1990፣ 1991፤ ተ/ሚ፣ 1978፣ /ኢት.አ/ላስተ 1989/::

ይህ ጥናት ይህንኑ ጥናትና ምርምር ክፍተት ለማጥበብ ይረዳ ዘንድ በማሰብ መምህራን አሰልጣኝ ከሆኑት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ አንዱ በሆነው በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ለዲፕሎማ መርሐ ግብር የሚሰጧቸውን ዐቢይ የአማርኛ ትምህርቶች ይዘት ለመተንተንና ለመገምገም ይሞክራል::

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ

በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በዲፕሎማው መርሃ ግብር የሚሰጡትን ዐቢይ የአማርኛ ኮርሶች ከኮሌጁ መምህራንን የማሰልጠን ዓላማ ጋር በማስተያየት ይዘ ታቸውን መተንተንና መመዘን የዚህ ጥናት ዓላማ ነው:: ዝርዝር ዓላማዎቹ

ደግሞ የሚከተሉት ናቸው::

ሀ. የየኮርሶቹን ይዘት ምንነት መተንተንና ጥንካሬና ድክመታቸውን መመዘን

ለ. እንደድክመቶች የሚቀርቡ ካሉ የሚሻሻሉበትን መንገድ መጠቆም::

## 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

ከላይ በጥናቱ ሥራ ውስጥ እንደተጠቀሰው የመምህራንን ሥልጠና በጠቅላይም ሆነ የአማርኛ መምህራንን ትምህርት ለብቻ ስንመለከት ለዕጩ መምህራኑ የሚቀርቡት የትምህርት ይዘቶች ተፈላጊውን ዕውቀት፣ ልምድና ክህሎት ማስጨበጥ አለማስጨበጣቸውን በውል ለመረዳት ያዳገተ ይመስላል:: በዚህም የተነሣ ይህን በይዘት ትንተና ላይ ያተኮረ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ሆኗል:: ከጥናቱም ውጤት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይገኛሉ የሚል ዕምነት አለ::

ሀ. የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን ሥልጠና ለመረዳትና በይዘት መረጣና በትኩረት አቅጣጫ በኩል ይበልጥ የሚሻሻልበትንና የሚጠነክርበትን መንገድ መጠቆም፣

ለ. ጀማሪ ሰልጣኝ መምህራን የመምህርነት ሙያቸውን በራሳቸው ጥረት ለማሻሻል የሚችሉበትን ሥልት ማስጨበጥ /መጠቆም/ የሚቻልበትን ሐሳብ ማመልከት፣

ሐ. በቀደመ ሥራ የተጀመረው የሙያ ሥልጠና በክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ ኅብር በተከታታይ በሥራ ላይ ሥልጠና እየተጠናከረ ሊሄድ እንደሚችል በማስገንዘብ ዐቢይ ትምህርቶችም በዚሁ አቅጣጫ የሚቀረፁበትን ሥልት ማሳሰብ፣

መ. ከዚህ በኋላ ለሚደረጉ ጥናቶች መነሻ ሀሳብ በመጠቆም ረገድም ሊጠቅም ይችላል::

## 1.4. የጥናቱ ክልል /Scope of the Study/

ከላይ በጥናቱ ዳራ ውስጥ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ መምህራንን የሚያሰለጥኑ ተቋማት ሦስት መሆናቸውን ጠቁመናል:: ከእነዚህ ከሦስቱ /አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቋንቋዎች ጥናት ተቋምና የባህርዳር መምህራን ኮሌጅ እና የከተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ/ የአማርኛ መምህራን አሰልጣኝ ተቋማት ውስጥ የከተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ለዚህ ጥናት የተመረጠባቸው ምክንያቶች:-

1ኛ. ኮሌጁ ገና ከጥንስሱ ከ1962 ዓ.ም ጀምሮ የሥልጠና ትኩረቱን በመምህራን ስልጠና ላይ ብቻ በማድረጉ

2ኛ. የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም ደግሞ ከመምህርነት ሙያ ውጭ የሚሠማሩ ተማሪዎችን የማሰልጠን ተደራቢ ዓላማ ስላለው እና መርሀ-ግብሩም አራት ዓመት የሚፈጅ የዲግሪ በመሆኑ ሰፋ ስላለው፤ እንዲሁም የባህር ዳር መምህራን ኮሌጅ ደግሞ በቦታው ርቀት የተነሳ ሊያጋጥም የሚችለውን የጊዜና የገንዘብ እጥረት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው::

ይህ ጥናት የሚያተኩርባቸው ኮርሶች በያዝነው የትምህርት ዓመት በመሰጠት ላይ በሚገኙት ሲሆን፤ እነዚህም ኮርሶች ኮሌጁ አንዳንድ የማሻሻያ ለውጦችን አካሂዶ ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ያዋላቸው ናቸው:: በዚህም የተነሣ፤ ቀደም ሲል /ከ1985 ዓ.ም በፊት/ ይሰጡ የነበሩትን ኮርሶች እና እነሱንም ተምረው የተመረቁ መምህራን በጥናቱ ውስጥ አላካተትንም::

ከላይ በተጠቀሱት ዋና ዋና ምክንያቶች የተነሳ ለዚህ ጥናት በተመረጠው በከተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ዲፕሎማ መርሀ-ግብር በአሁኑ ወቅት ለሚሳተፉ ዐው የአማርኛ መምህራን 28 ያህል ኮርሶች ይሰጧሉ:: እነዚህ ኮርሶችም በክሬዲት ሲሰሉ 74 ይሆናሉ:: ኮርሶቹ የሚያተኩሩባቸው ርእሰ ጉዳዮች ሲታዩ፤ ጠቅላላ ዕውቀት /23 ክሬዲቶች/፤ ሥነ-ዘዴ /13 ክሬዲቶች/ እና አቢይ ትምህርቶች ደግሞ 38 ክሬዲቶች ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በዲፕሎማው መርሀ-ግብር የሚሰጡትን የጠቅላላ እና የሥነ ዘዴ ትምህርቶችን መመልከት ሳይሆን በዐቢይነት የቀረቡትን ብቻ በመሆኑ ሌሎችን አስፈላጊ ሆነው ሲገኙ ከመነካካት በስተቀር ሙሉ ትኩረት አናደርግባቸውም ::

የጥናቱ ዋና ትኩረት ዐቢይ ኮርሶቹ ምን ምን የትምህርት ይዘት አካተዋል ለቋንቋ መምህር መቀረብ አለባቸው ከሚባሉት ሙያ ነክ ኮርሶች ውስጥ ምን ያህሉን ይዘዋል በምን ያህል ስፋትና ቅደም ተከተል ቀርበዋል በሚሉትና ሌሎችም ተመሳሳይ ጥያቄዎች አካባቢ የሚያጠነጥን ይሆናል ::

## 1.5. የጥናቱ ገደብ /Limitation of the Study/

ይህ ጥናት በ14 ዐቢይ ኮርሶች /38 ክሬዲቶች/ ይዘት ትንተና ላይ ያተኮረ መሆኑ ቀደም ሲል ተገልፀአል :: የኮሌጁን ዓላማ ተንተርሶ የተነደፈና የተቀናበረ ሥርዓተ ትምህርትም፣ በሥርዓተ ትምህርቱም ላይ የተመረኮዘ መርሀ-ትምህርት አልተገኘም :: ወይም በሁለቱም ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ የማስተማሪያ መጽሐፍ (text) ለየትኛውም ኮርስ አልተገኘም :: በዚሁ ችግር የተነሣ የአቢይ ኮርሶችን ይዘት ለመረዳትና ለመተንተን የየኮርሶቹ ይዘት ይገኙባቸዋል ተብለው የተገመቱ ሌሎች ሰነዶች /ዓላማን እና ቢጋርን የሚመለከቱ፣ የተማሪዎችን ማስታወሻዎች እና የኮርሶቹ የመጨረሻ ፈተናዎች/ በትንታኔ ውስጥ ታቅፈዋል :: ይሁንና ካሉት 14 ኮርሶች የመጨረሻ ፈተናዎች /12 ክሬዲቶች/ አሁን ባለንበት /በ1986 ዓ.ም/ ሁለተኛ ሴሚስተር የሚሰጡ በመሆናቸው ሙሉ በሙሉ ባለመሸፈናቸውና የማጠቃለያ ፈተና ስላልተሰጠባቸውም የፈተና ወረቀቶችን ለማግኘት መጠነኛ ችግር ገጥሞናል :: ከእነዚህም 5 ትምህርቶች ውስጥ አጋማሽ ፈተና የተሰጠባቸው ቢኖሩ ለማግኘት በተደረገ ጥረት፣ "የአማርኛ ሰዋሰው ክፍል ሁለት" ለሚባለው ኮርስ የአጋማሽ ፈተና መስጠቱ ስለተረጋገጠ በጥናቱ ውስጥ ታቅፏል ::

.../

## 1.6. የጥናቱ ዘዴ /Research Method/

ይህ ጥናት መሠረት የሚያደርገው በአመዛኙ በገላጭ የምርምር ዘዴ ውስጥ በሚታቀፈው በይዘት ትንተና (content analysis) ሥልት ነው ። በዚህ ስልት በመጠቀም በክለሳ የሚሰጡትን ዐበይት የአማርኛ ትምህርቶች ይዘት ለመተንተን ይሞከራል ። አሠራሩም፣

ሀ. በክተባ መምህራን ትምህርት ክፍል የሚሰጡ ዐበይት የአማርኛ ትምህርቶችን በመውሰድ የአያንዳንዳቸውን ዓላማና የትኩረት አቅጣጫ ከዝርዝር ቢጋራቸው ጋር በማመሳከር ይዘቶቻቸው በምን በምን ጉዳዮች ላይ እንደሚያጠነጥኑ መረዳት፡—

ለ. በማስተማሪያነት የሚያገለግሉ የማስተማሪያ መጻሕፍት ካሉ ይዘቶቻቸውን መርምሮ መረዳት፡—

ሐ. በየኮርሶቹ ቢጋር ውስጥ የተጠቀሰው ይዘት በትምህርትነት መቅረቡን ለመረዳት የተማሪዎችን የማስታወሻ ደብተር /ሌክቸር ኖት/ በመመርመር ከየትምህርቶቹ ቢጋር ጋር ማመሳከር

መ. ለየትምህርቶቹ የሚሰጡትን ፈተናዎች /መልመጃዎች መመርመርና የትኩረት ነጥቦቻቸውን ከዋናው የትምህርቱ ዓላማና ቢጋር ይዘት ጋር ማመሳከር ሲሆኑ በዚህ ስልት የተገኙትን መረጃዎች ይበልጥ ለማጠናከር የተማሪዎችን አስተያየቶች በመጠየቅ ሰብስቦ ለመተንተን ይሞከራል ። በመጨረሻም የተሰበሰቡትን መረጃዎች ከተዛማጅ ጽሁፎች በተውጣጡ መሥፈርቶች መሠረት የይዘት ትንተና እና ግምገማ ይደረጋል ።

## 1.7. የክተባ መምህራን ትምህርት ክፍል አጭር ታሪክ

የክተባ መምህራን ትምህርት ክፍል በትምህርት ሚኒስቴርና በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ፋኩልቲ በምምነት የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ /7ኛ–8ኛ ክፍሎች/ የሚያስተምሩ ዕጩ መምህራንን ለማሰልጠን በ1952 ዓ.ም /ኢት.አ./ የተጠነሰሰ ነው ።

ለ10 ዓመታት ያክል በትምህርት ፋኩልቲና በትምህርት ሚኒስቴር ኃላፊነት ሥር ዕጩ መምህራንን የሚያሰለጥን [illegible] ሲያገለግል ከቆየ በኋላ በ1961 ዓ.ም በዩኒቨርሲቲው [illegible] መሥሪያ ቤት መካከል በተደረገ

ስምምነት በ1962 ዓ.ም በኮሌጅ ደረጃ ተቋቋመ:: የማስተዳደሩንም ሥራ ኃላፊነት ትምህርት ሚኒስቴር ተረከበ::

ይህ ኮሌጅ ከ1962 – 1968 እ.ኤ.አ. ባሉት ዓመታት ውስጥ የአዲስ አበባ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ በሚል ስያሜ እየተጠራ ሜክሲኮ አደባባይ በሚገኘው የተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ውስጥ መምህራንን የማሰልጠን ተግባሩን አካሂዷል::

ከ1969 ዓ.ም /እ.ኤ.አ/ ጀምሮ ደግሞ ኮሌጁ አሁን ወደሚገኝበት የአዲስ አበባ ከተማ ሰሜናዊ ዳርቻ ወደቀድሞው ቀ.ኃ.ሥ. መምህራን ማሰልጠኛ ዞረ:: የኮሌጁም መጠሪያ በሚገኝበት ቦታ ተሰይሞ ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ተባለ:: ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ በአዋጅ ቁ. 109/68 መሠረት ኮሌጁን የማስተዳደር ኃላፊነቱን ትምህርት ሚኒስቴር ለከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን አስረከበ::

የኮተቤ መ.ት.ኮ. ከጊዜ ወደ ጊዜ የመርሀ-ግብርና የሥልጠና ዓይነቶች ለውጥ በማድረጉ ከ1973 /ኢት.አ/ ጀምሮ እስከ 1977 ዓ.ም/ኢት.አ/ ድረስ ዕጩ መምህራንን በአንድ ዐቢይ እና በአንድ መለስተኛ ትምህርት ያሰለጥን ነበር:: ከ1978 /እ.ኤ.አ/ጀምሮ ግን በዲፕሎማ መርሀ-ግብር ያሉትን ዕጩ መምህራን በአንድ ዐቢይ የትምህርት አይነት ብቻ በማሰልጠን ላይ ይገኛል::

ኮሌጁ ከጊዜ ወደጊዜ የሥልጠና መርሀ-ግብሩን እያስፋፋ በመሄዱ ከ1982 ዓ.ም /ኢት.አ/ ጀምሮ በአንዳንድ የትምህርት መስኮች ከዲፕሎማው መርሀ ግብር በተጨማሪ የዲግሪ መርሀ ግብር ማካሄድ ጀምሯል:: ለ4 ዓመታት አሰልጥኖ በቢ.ኤድ/B.ED/ የሚያስመርቃቸው ዕጩ መምህራንም በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የመጨረሻዎቹ ክፍሎች /11ኛ –12ኛ ክፍሎች/ ለማስተማር የሚሰለጥኑ ናቸው:: ስልጠናው በሦስት የትምህርት ዘርፎች ሲካሄድ ሰልጣኞቹም በአንድ ዐቢይና በአንድ መለስተኛ የትምህርት አይነት ይሰለጥናሉ::

በአሁኑ ወቅት ኮሌጁ በ17 ክፍለ-ትምህርቶች የተደራጀ ሲሆን

በሚገለግሉ ወርሀ—ገብር በ13 የትምህርት ዓይነቶች ዕጩ መምህራንን ያሰለጥናል፤ ኮሌጁ ሥልጠናውን በ3 ወርሀ ገብሮች ያከሄዳል፡፡ እነዚህም የቀን፣ የማታ እና የክረምት ተከታታይ ወርሐ ገብሮች ናቸው፡፡ በቀኑ ወርሀ ገብር በዲግሪና በዲፕሎማ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራንን ያሰለጥናል፡፡ በማታው ወርሀ ገብር እንደ ቀኑ ሁሉ በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሊያስተምሩ የሚችሉ ዕጩ መምህራንን ሲያሰለጥን፣ በክረምት ተከታታይ ትምህርት በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን፣ በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለማስተማር የሚያስችላቸውን የሙያ ማሻሻያ ይሰጣል /ካታሎግ፡ 1992፣ ዓለማየሁ ገ/ማርያም፡1984፣ በውን፡1976፣ ት/ሚ፡1983 ሊት. አ/፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## 2. የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

ይህ የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ሥር የሚተኮርባቸው ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮች፣ በመጀመሪያ ደረጃ የመምህራን ሥልጠና አስፈላጊነት፣ የቋንቋ መምህር ሥልጠና እና በሥልጠናው ወቅት ስለሚሰጡ ጠቅላላ ትምህርቶች ጠቀሜታና አብይ የሥልጠና ትምህርቶች ይዘት ምንነት የሚያካትቱ ይሆናሉ:: በሁለተኛ ደረጃም፣ የዚህ ጥናት አምብርት የምርምር ስልት ስለሆነው ስለ ይዘት ትንተና ምንነት፣ አገልግሎትና የአሠራር ስልት ከተለያዩ መረጃዎች የተጠናቀረ መጠነኛ ሀተታ ይቀርባል::

### 2.1. የመምህራን ሥልጠና —በጠቅላላ

የተለያዩ አገሮች የመምህራን ሥልጠና ጠቅላላ ልምዱ ሲታይ በብዙ ጉዳዮች ተቀራራቢነት አለው:: ከሚቀራረብባቸው ጉዳዮች ውስጥ የሚከተሉትን እንደ ምሳሌ መውሰድ ይቻላል::

| የንድፈ ሃሳብ ትምህርት | የተግባር ትምህርት |
|---|---|
| — አጠቃላይ ትምህርት | — የክፍል ምልከታ |
| — ንጽጽራዊ ትምህርት | — የሪፖርት አፃፃፍ |
| — የትምህርት ሳይኮሎጂ | — የቤት ሥራዎችን ማረም |
| — አጠቃላይ የማስተማር ዘዴ | — ረዳት መምህር ሆኖ የመሥራት |
| — የማስተማሪያ መሣሪያዎች አጠቃቀም | — ክለቦችን መምራት |
| — ዋናና ተከታይ ትምህርት የማስተማር ዘዴ | — ራስን ችሎ ማስተማር |
| — የትምህርት ቤትና የትምህርት ታሪክ | |
| — የትምህርት ፍልስፍና | |
| — የትምህርት አደረጃጀት | |

/ተ/ሚ፣ 1983፡119

አብርሃም 1990፡95/

ከዚህ በላይ የተነሡት አጠቃላይ የትምህርትን ንድፈ ሀሳብና ተግባርን ያጣመረ ርዕስ ነገሮች በተለያዩ አገሮች የሥልጠና ሂደት ውስጥ በአማካይነት ይታቀፉ እንጂ ከሚሰጡበት የሥልጠና ጊዜ ርዝማኔ አንፃር ሲታዩ ደግሞ ልዩነት እንዳላቸው ጥናቶች ይጠቁማሉ /አበር ሃም 1990:47-48/::

አንዳንድ አገሮች የሁለት ዓመት፣ አንዳንዶቹ የሦስት ዓመት ሌሎች ደግሞ የአራት ዓመትና ከዚያም በላይ ሥልጠና አካሂደውና ፈትነው ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣሉ:: የሚከተሉት አገሮች በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ::

| አገሮች | የሥልጠና ርዝመት በአመት |
|---|---|
| አርጀንቲና | 4/5 |
| ኩባ | 5 |
| ግብጽ | 4 |
| ፈረንሣይ | 4 |
| ጋና | 3 |
| ጉዋቲማላ | 3 |
| ፓራጉዋይ | 2 |
| ኢራቅ | 2 |

/አበር ሃም ሁሴን 1990: 47-48/

ይሁንና አንዳንድ አገሮች ደግሞ በተወሰነ ሙያ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ተመጣጣኝ የምስክር ወረቀት ያላቸውን ሰዎች በመቀበል ለተወሰነ ጊዜ ለመምህርነት የሚያዘጋጅ ሥልጠና አቅርበው የችሎታ ማረጋገጫ ፈተና በመስጠት ወደ ሥራ ያሰማራሉ /ማሪያኔ:1987:76/:: እንደዚሁም ሁሉ፣ የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት የሆነውን ኮሌጅ ስንመለከት የዲፕሎማው መርሃ-ግብር ሙያዊ ትምህርቶችና የማስተማር ስልጠናውን በማጣመር በሁለት ዓመታት ጊዜ ውስጥ የሚያጠናቅቅ ሆኖ እናገኘዋለን::

የመምህራንን ሥልጠና ከጨትሲሲ የትኩረት ነጥቦና ከጊዜ ርዝመት ባሻገር በኮርሶች ይዘት በኩል ስንመለከተው የሚታየውን ገጽታ ከዚህ ቀጥ ለን እንመለከታለን::

## 2.1.1. የመምህራን ሥልጠና አስፈላጊነት

ማስተማር ዓላማን የተመረኮዘና በመምህራንና በተማሪዎች መካከል በተወ ሰነ ቦታና ጊዜ የሚካሄድ ዕውቀት የችሎታና የባሕርይ መገንቢያ ክንውንና የግንኙነት ሒደት መሆኑ ይታወቃል:: ይህ የባሕርይ ግንባታ በታቀደው መስ ረት እንዲሳካ መምህሩ ሲሰለጥን የሚሰለጥንበትን የትምህርት ዓላማና ሥርዓት ተንትኖ ሊያውቅ ይገባል/ማርያኔ 1987፣ ሄይት 1977፣ ት/ሚ. 1978፣ 1983 ሌት.ስ/

የመምህሩ አጠቃላይ ችሎታ እውቀትና ተገቢ ልምድ ከተማሪው በሚጠበቀት የባሕርይ ለውጦች መሠረት የሚሆኑት የአእምሮ ብስለቱ ስሜቱ፣ ፍላጎቱ፣ ምርጫው፣ አስተሳሰቡና ተግባራዊ እንቅስቃሴው ሁሉ ለሚቀረጹበት፣ ለሚያድጉበት፣ ለሚሻሻሉበት፣ ለሚለወጡበት እንቅስቃሴ ሁሉ መነሻ ይሆናል:: መምህሩ ለእነዚህ ተግባራት ተሰላፊ ሆኖ እንዲገኝ ጊዜውንና ሙያው የሚጠይቀውን፣ የሚያስተምረውን ትምህርት ማወቅና መውደድ፣ ተማሪዎችን ማወቅና መውደድ ዘወትር ለመማር ዝግጁ መሆን፣ የመሳሰሉት ባሕርያት ሊኖሩት ይገባል / ሄይት 1977፡ ብሩምፊት 1983፤ 15/::

አንድ መምህር በሚያስተምርባቸው ክፍሎች ውስጥ ለሚያጋጥሙት ሁኔታዎች አስፈላጊውን እንዲፈጽም ሙያው የሚጠይቀውን ሥልጠና ማቅረቡ ተገቢ ነው /ማሪያኔ 1987፣ ሳራስንና ሌሎች 1986/::

ዕጩ መምህራን በሚሰለጥኑበት ወቅት የሚቀርብላቸው ትምህርት/የሥልጠና ሂደት/ ተማሪዎቻቸው በመማሩ ሂደት ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማበረ ታታት የሚለውን ይዘት የሚመረኮዝ በክፍል ውስጥ ከማስተማሩ ተግባር ይልቅ

የመማሩ ጠቀሜታ የላቀ መሆኑን፣ ተማሪዎቹ እንዴት ሊማሩ እንደሚችሉ ማስተዋር፣ ማስተማር ማለት ተማሪዎቹ ወስደው የሚናገሩትን መንገር እንዳልሆነ፣ የመማሩን ስምምዱ ማድረግ ያለበት ተማሪው እንጂ መምህሩ አለመሆኑን..../ሉዊስና ሚሚ 1990/ በሚገባ እንዲረዱት ማለማመድና ማስገንዘብ ያስፈልጋል። በተጨማሪም በሚያስተምሩበት ትምህርት ተገቢ እውቀት፣ የማስተማሪያ ዘዴ ክህሎት፣ የትምህርት መሣሪያዎች አጠቃቀም ዘዴ፣ በማስተማር ሙያ በቂ ስምምዱ፣ የሥነ ምግባር ገንቢነታና ዝግጅት፣ ለሙያው ፍቅርና ጽኑ እምነት ያላቸው እንዲሆኑ ሥልጠናው ሊረዳቸው ይገባል /ቁነስክ 1988 ፣ማልካሻና ቡልቶሳን 1988/።

ከአጠቃላይ መምህራን ሥልጠና ወጥተን ርዕስ ጉዳያችን ወደሆነው የቋንቋ መምህራን ሥልጠና ስንገባ የቋንቋ መምህራን ከሌሎች ትምህርቶች መምህራን ጋር የሚጋሯቸው ባህርያት ወይም ሁኔታዎች እንዳሉ እንረዳለን። እነዚህ የጋራ የሆኑ ባሕርያት የሚከሰቱባቸው ርዕስ ጉዳዮች ደግሞ በጠቅላላ ትምህርት ውስጥ ሊጠቃለሉ /ሊጠቀሱ/ የሚችሉ ናቸው።

## 2.1.2. በቋንቋ መምህር ስልጠና የጠቅላላ ትምህርቶች ጠቀሜታ

መምህራን የወደፊቱን አገር ተረካቢና ገንቢ ትውልድ የሚያሳድጉና የሚያስለጥኑ መሆናቸው በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ በሚያደርጉቸው ማኅበራዊ ተራክቦዎች ገንቢ ሚና ሊጫወቱ ይገባል። በሕብረተሰቡ ውስጥ ባላቸው አባልነትና ተሳትፎ ደግሞ የየወቅቱን ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ለመፍታት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችሏቸው ኮርሶች በሥልጠናው ወቅት ሊቀርቡላቸው ይገባል /ቁነስክ፡1988/። ለዚህ የሚያበቋቸው ኮርሶች ደግሞ ከሚሰለጥኑበት ልዩ የሙያ ስልጠና በተጨማሪ የሚቀርቡላቸው የጠቅላላ ትምህርቶች አካል ናቸው። እንደማንኛውም የትምህርት መስክ መምህራን ሁሉ የቋንቋ መምህርም ከጠቅላላ ትምህርቶች የሚያገኛቸውን ጠቀሜታዎች በተመለከተ ከላይ ሄይት፡1977፣ ማሪያኔ 1987፣ ባራስንና ሌሎች፡ 1986፣ ሉዊስና ሚሚ፡1990፣ ጠቅለል አድርገው ያስገነዘቧቸውን ስተሪቨንስ /1977፡72 – 73/ [illegible] በቋንቋ መምህራን ስልጠና አስፈላጊነት [illegible]

ጥናቱን ያካሄዱ ባለሙያ እንደሚከተለው በዝርዝር አቅርበዋቸዋል::

ሀ. በመሠረተ ትምህርቱ ጠቅላላ የሕብረተሰቡን ሁኔታና በህብረተሰቡ ውስጥም የመምህሩን ግንኙነትና ሚና በሚያሳይ መልኩ መቀረጽ አለበት:: በሥልጠናም ወቅት የሚያተኩሩባቸው ፍሬ ነገሮች የትምህርትና ሥነ-ልቡና፣ የህፃናት /ልጆች/ ዕድገት ጥናት፣ ማኅበራዊ ሥነ-ልቡናን እና ትምህርታዊ የሆኑ የአስተሳሰብ ወርሆዎችን የሚመለከቱ ሊሆኑ ይገባል::

ለ. ጠቅላላ ትምህርት በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን ዋና የትምህርት ቢጋር መያዝና ለዋናው ሥልጠና የሚያገዙና ለቢጋሩም ምንነት አንዳንድ መሠረታዊ ነጥቦች ማቅረብ ይኖርበታል:: የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚያገዙ፣ የሚደገፉና የሚያበረታቱ ተግባራት ወኖር አለመኖራቸውን ማወቅ ለሰልጣኝ መምህሩ ይጠቀማል:: መምህሩ በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ያለውን የሥራ ድርሻ ይገነዘብ ዘንድ ለሙያው የሚያገዙ/የሚያደናቅፉ የገንዘብ አቅም ድርጅቶችና የአስተዳደር አርከኖች ወኖር አለመኖር ሁሉ ሊገለጹለትና ሊገነዘባቸው ይገባል::

ሐ. ደረጃውን ለማሻሻል፣ የሥነ ምግባር እድገቱን ለመጠበቅ እንዲቻል ተጨማሪ ሥልጠናና ትምህርት የሚያገኝበትን መንገድ በመጠቆም ረገድ የጠቅላላ ዕውቀት ትምህርት ፍንጭ ሊሰጠው ይችላል:: መምህሩ በግሉ ግላዊ ፍላጎትና እምነት ያለው እንደመሆኑ የሌሎችን ተጎትኖ እንዳይዝ ነጋና የሚያስተምርባቸው የትምህርት መሣሪያዎች የህብረተሰቡን ባሕል የተከከሉ መሆናቸው፣ የሚያስተምርበት አካባቢ የራሱ ተፅዕኖ እንዳለውና እነዚህ ሁሉ ተደማምረው በማስተማር ሥራው ላይ ተፅዕኖ እንደሚኖራቸው ተረድቶ በተቻለ መጠን ከአድሎአዊነት ነፃ ሆኖ የሚያስተምርበትን ፍንጭ ከጠቅላላ ትምህርት ሊያገኝ ይችላል::

ወ. በሥልጠናው ጊዜ ውስጥ ልቅ ልቅ በሆኑት ሜለትም የክፍል አያያዝ

የሥነ ሥርዓት አጠባበቅ፣ በዚሁ ትምህርት ተማሪዎች ሲሆኑ ሊደረግ የሚገባውን ማወቅ ያስፈልገዋል::

ሠ. መሠረታዊ ስለሆኑ የመስተማር ዘዴዎችና በክፍል ውስጥ የመምህርና የተማሪ ግንኙነትን የሚመለከት ጠቅላላ ዕውቀት እንዲኖረው በስልጠናው ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል::

ረ. መምህር ለሚያስተምረው ትምህርት ዝግጅት ሳይኖረው ወደ ክፍል እንዳይገባ፣ ያለዝግጅት ወደ ክፍል መግባት ፍጹም ስህተት መሆኑን እንዲረዳ ማድረግ ያሻል::

ሰ. መምህሩ የሚያስተምረውን ትምህርት ሥርዓተ ‒ ትምህርት፣ መርሃ‒ትምህርት፣ የማስተማሪያ መጽሐፍ ምንነት እንዲረዳ፣ ያላቸውንም ግንኙነት በቅደሚያ እንዲገነዘብ ሥልጠናው ሊያመቻቸለት ይገባል::

ሸ. የማስተማር ሙያን ለማሳደግና ለማስፋፋት መምህሩ ሙሉ እምነት እንዲኖረው በጠቅላላ ትምህርት ወቅት መጉትጎት ያስፈልጋል::

በማለት የጠቅላላ ትምህርትን (General Education) አገልግሎት አስረድተዋል::

## 2.1.3. በቋንቋ መምህር ሥልጠና አበይ የሙያ ክርበኞ ጠቀሜታ

ከዚህ በላይ ከተገለጹት ከጠቅላላ ትምህርቶች ሌላ በቋንቋ መምህርነት የሚሰለጥን መገን በቋንቋ መምህርነቱ ብቻ ሊያጠና ቸው /ሊማራቸው/ እና ቢለማመዳቸው የሚገቡ ሙያዊ ክርበኞ አሉ:: ይህም በመሆኑ በመጀመሪያ የቋንቋ መምህራን ትምህርት ወይም ስልጠና ብለን ስንነሳ የምናተኩርበት ዋነኛ ርዕስ ነገር ቋንቋን ማስተማር መማር የሚለው ነው:: ሂሳብን፣ ኬሚስትሪን ወይም ታሪክን ለማስተማር የሚሰለጥኑ መምህራን፣ ሂሳብን፣ ኬሚስትሪን ወይም ታሪክን በርዕስ ነገርነት እንደሚማሩት ሁሉ በቋንቋ መምህርነት የሚሰለጥኑ ዕጩ መምህርም ያስተምረዋል ዘበሉ የሚሰለጥንበትን ቋንቋ በሚገባ መማር ይኖርበታል:: ቋንቋን መማር ሲባልም ነው ቀበልም [illegible] ረገድ የቋንቋ ከሌሎች በለበት መሆንን የሚወቅ

ጉዳይ ነው:: የቋንቋ ክሂሎች ስንልም፤ ንግግርን በተገቢው መንገድ አዳምጦ መረዳትን፤ ሀሳብን በንግግር በተከከለ መግለፅን፤ የተጻፈ ነገርን አንብቦ መረዳትን፤ ሀሳብን በተከከለ በጽሑፍ መግለጽን ይመለከታል /ዊልያምስ 1984፤ ፍውለር 1965፤ ተስፋዬ ሸዋዬ 1981 ኢ.ት.አ/:: መምህሩም የእነዚህ ክሂሎች ባለቤት መሆን ይገባዋል/ ሂስ እና ደቢን፡ 1984/::

ከዚሁ ከቋንቋው ትምህርት ጋር ተያይዞም፤ ተማሪዎች ለትምህርት የሚቀርብላቸውን የቋንቋ አካል /ይዘት/ እንዴት ሊማሩት እንደሚችሉ ለማሳየት /ለመምራት/ የሚያበቃውን ሥልጠና ሊሰጠው ይገባል:: ፍሪማን /1989:28/ ስለዚህ ጉዳይ "...የቋንቋ መምህራን ትምህርት ትኩረት በቋንቋ ማስተማር ውስጥ ቋንቋን መማርንና ማስተማርን የሚይዝ ነው" በማለት ጽፈዋል::

በዚህ የተነሳ ቋንቋን ለማስተማር ለሚሰለጥኑ መምህራን ምን እናቀርብላቸው? የምናቀርብላቸውን የቋንቋ ትምህርት አካል /ይዘት/ እንደምን እንወስነው? ቋንቋውን ማስተማሩንና መፈተኑን እንደምን እናስተምራቸው? በሚሉና በመሳሰሉት አሳሳቢ ጥያቄዎች እንወጠራለን::

ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለመሻት በሙያው ምርምር ያካሄዱ ባለሙያዎችን ቀደምት ሥራዎች መፈተሹ አግባብ በመሆኑ፤ ከዚህ ቀጥለን ለቋንቋ መምህራን ቢቀርቡ የሙያ ብቃት ያስገኛሉ የሚባሉትን አንዳንድ ርዕስ ነገሮች እንቃኛለን::

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ለቋንቋ መምህርነት ለሚሰለጥኑ ዕጩ መምህራን ጠቅላላ ትምህርቶች ከሚያስጨብጧቸው ፍሬ ነገሮች በሰፋ ሁኔታ ሙያ ነክ የሆኑት ለዋናው የወደፊት ሥራቸው ፅምብርት ናቸው:: እነዚህንም ሙያ ነክ ዋና ዋና ትምህርቶች የተለያዩ ምሁራን በተለያዩ መንገዶች ያቀርቧቸዋል::

የቋንቋ መምህራንን ሥልጠና በሚመለከት ለሚነሱ በርካታ ጥያቄዎች መልስ ለመፈለግ ምርምር ያካሄዱ፤ የምርምራቸውንም ውጤት ለተጠቃሚዎች ካቀረቡ ባለሙያዎች መካከል ብሩምፊት /1987/ አንዱ ናቸው:: ብሩምፊት የቋንቋ መምህራን ትምህርት በሥነ-ልሣን ወይም በትምህርታዊ ንድፈ ሀሳብ ላይ ብቻ አትኩሮ መምህራኑን የአንድ የተወሰነ ሙያ አቀንቃኝ የሚያደርጋቸው መሆን የለበትም:: ይልቁንም

ንድፈ ሀሳብንና ተግባርን ያጣመረ ስልጠኝ አካል በራሱ ተማሮና እንዲሰራ ም፡
ሁኔታዎችን የሚያመለክተው መሆን ይኖርበታል /ገጽ 3 — 8/ ሲሉ ያስረዳሉ::

ብሩምፊት "ንድፈ ሃሳብንና ተግባርን ማጣመር" በሚለው በዚሁ ጥናታዊ ጽሁፋቸው ውስጥ ለቋንቋ መምህርነት ለሚሰለጥኑ ዕጩ መምህር በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በዋናነት የሚታዩትን ክሂሎች /ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ፣ መጻፍ/ አጣምሮ ማስተማር ያስፈልጋል ሲሉ ጠቀለል አድርገው አቅርበዋቸዋል:: እንዲሁም ሰልጣኝ መምህር በስልጠናው ወቅት የየክሂሎችን አቀራረብ ሥልትና ድጋፍ የሚሆነውን የንድፈ ሀሳብ መሠረትና ተማሪዎች ደግሞ ምን ምን ተግባራትን ቢፈጽሙ/ቢያከናውኑ የቀረበላቸውን ክሂል ሊማሩና ሊለምዱ እንደሚችሉ የሚያሳዩ፣ የሚያስረዱ፣ የሚያስገነዝቡ ክንዋኔዎችን በማቀረብ እንዲለማመዱ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አስረድተዋል:: ፍሪማን /1989: 28—33/፣ "የመምህራን ሥልጠና ችሎታ ዕድገትና ውሳኔ አሰጣጥ" በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጥናት ውስጥ ለቋንቋ መምህርነት የሚሰለጥኑ ወገኖች ሊማሯቸው የሚገቡ ዋና ዋና ሙያ ነክ የሥልጠና ትምህርቶች በአራት ሊመደቡ እንደሚችሉ አስገንዝበዋል:: እነሱም፤ ዕውቀት (Knowledge) ክሂል (Skill) ዝንባሌ (Attitude) ፣ እና ግንዛቤ (Awareness) ናቸው::

እነዚህ አራት ምድቦች በውስጣቸው ዝርዝር ፍሬ ነገሮችን ያካተቱ ናቸው:: እነሱንም እንደሚከተለው ተንትኖ ማየት ይቻላል::

ዕውቀት:— ለትምህርት በሚቀርበው ርዕስ ነገር ምንነት፣ ይህ ጉዳይ ለነማን ይቀርባል? /በዚሁ ውስጥ የሚነሱት የተማሪዎች ዓራ፣ ለምድና የቋንቋ ችሎታ የመሳሰሉት ይሆናሉ/ የት ነው ትምህርቱ የሚሰጠው? /ባሕላዊ ሁኔታዎችን፣ ማኅበራዊ ተቋማትን፣ አውዱን የሚመለከቱ ይሆናሉ/ የሚሉትን ይይዛል::

ክሂል:— መምህሩ ምን ሊሰራ ይችላል? እንዴት ሊሰራ ይችላል? /የማስተማሪያ መሣሪያ አጠቃቀም፣ የትምህርት አቀራረብ፣ የክፍል ውስጥ ተራክቦ፣ የክፍል ውስጥ ሥርዓት ማስጠበቅ/

ዝንባሌ፦ በመማር ማስተማሩ ሂደት ዉስጥ መምህሩ ለተማሪዉ፣ ተማሪዉ ለትምህርቱ ያለውን አመለካከትና ዝንባሌ ለመለከት የሚቻ ልበትን ሥልት ማግኛ ነው።

ግንዛቤ፦ በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎች ትምህርቱን መከታተላቸውንና አለመከታተላቸውን ለማወቅና ለመረዳት የሚደረግ ጥረት ነው። ተገቢውን ትኩረት ካልሰጡ ለማባሰብ፣ ሰጥተው ከሆነም ለማበረታታት ይረዳል። እንዲሁም በአጠቃላይ በት/ቤቱ አካባቢ ያለው ማህበራዊ ሁኔታ ትምህርቱን በማፋጠንም ሆነ በማጓተት የሚያደርገው ተፅዕኖ ካለ ያንን ለመረዳት ያመቻል።

ስትሪቨንስ /1977:74–77/ በበኩላቸው፣ ለቋንቋ መምህርነት ለሚሰለጥን ሰው የሚቀርቡ ዐቢይ የሙያ ሥልጠና ኮርሶች ሊያካትታቸው የሚገቡትን የትምህርት ይዘቶች በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፍሏቸዋል። እነሱም፦

1. የክሂል ክፍሎች /The skills component/
2. የመረጃ ክፍሎች /The information component/
3. የንድፈ ሀሳብ ክፍሎች (The theory component)

ናቸው። እነዚህም ክፍሎች በዝርዝር ሲታዩ የሚከተለውን ይመስላሉ።

## 1. የክሂል ክፍሎች

የክሂል ክፍሎች የሚባሉት የቋንቋ ችሎታን፣ የማስተማር ዘዴን፣ እና የመማር ማስተማር ሂደትን መቆጣጠርን የሚያመለክቱ ዝርዝር ነጥቦችን ይይዛሉ።

### ሀ. የቋንቋ እዝታ /Language command/

መምህሩ በሚያስተምረው ቋንቋ የሚያስተምርበትን ደረጃ የሚመጥን ችሎታ ሊኖረው ይገባል። በተመደበበት ክፍል ለማስተማር የሚያበቃ ችሎታ የሌለው መምህር የሚያስተምራቸውን ተማሪዎች ችሎታ የባሰ ሊያበላሽ ይችላል። ተፈላጊ በሆኑት የቋንቋ ክሂሎች /ማዳመጥ፣መናገር፣ መጻፍ፣ ማንበብ/ ጥሩ ችሎታ የሌለው መምህር የተማሪዎቹን ፍላጎት [illegible] የራሱንም ሆነ የተማሪዎቹን ጊዜ ከማባከኑ [illegible]

ወገለሴ አለበት /ብሪምሬት፣ 1987፡ በሠነዘረት ሃሳብ ጋርም ይጣጣማል/::

ለ. <u>የክፍል ውስጥ ክንውንና የማስተማር ዘዴ</u>

በትምህርት ነት የሚቀርቡት የቋንቋ አካሎች እንዴት እንደሚከፋፈሉ፣ አያንዳንዱን ክፍፍል ለማስተማር በሚያመች መልኩ እንዴት እንደሚዘጋጁና በትምህርት ነት እንዴት እንደሚቀርብ አጭምሮ ማወቅ ያስፈልጋል:: የሚቀርበውን የቋንቋ አካል /ለምሳሌ፣ የድምፀ አወዳደቅና አነባበ፣ ማጥበቅና ማላላት፣ ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ፣ ትክክለኛ የስዋ ሰው አጠቃቀም/ እንዴት ወደተማሪያቹ ማስተላለፍ እንደሚቻልና ተማሪ ያቹም በተቀላጠፈና በቀላል ዘዴ እንዲለምዷቸው ማድረጊያውንም ስልት ማስለየት ያስፈልጋል/ፍሪማን፣ 1987 እና ሸው፡1987 ጠቅለል አድርገው ያስፈረት አስተያየት ከዚህ ጋር ተዛምዶ አለው::/

ሐ. <u>መማርን ማስተዳደር / Management of learning</u>/

በትምህርት ሂደት ውስጥ አያንዳንዱ የማስተማር እንቅስቃሴ ወዲያውኑ ውጤት አያሳይ ይሆናል:: አንዳንዱ የትምህርት አካሎች ደግሞ ወዲያውኑ በተማሪያቸ ገንዘቤ ያገኛሉ:: አንዳንደቹን ለመገንዘብ ደግሞ ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስድ ይቻላል:: እንዲሁም ትምህርቱን በመገንዘብ ረገድ በተማሪያቸ መካከል ልዩነት ይኖር ይሆናል:: አን ዳቸው ካንዳቸው በፈጠነ/በዘገየ የጊዜ ልዩነት ሊማሩ ይቻላሉ:: መምህሩም እንዲህ ያሉ ልዩነቶች መኖራቸውን በመገንዘብ ትምህርቱን ማቀረብ አለበት:: በፍጥነት የሚገባቸው ተማሪያቸ እንዳይሰለቹ በዝግታ የሚረዱት ደግሞ ተስፋ ቆርጠው ትምህርቱን እንዳይጠሉት ለማድረግ የሚያስችለውን ብልሃት ከሥልጠናው ማግኘት አለበት፣ በማለት ስትሪቨንስ የከሂል ክፍሎችን ያጠቃልሏቸዋል::

2. <u>የመረጃ ክፍሎች</u>

በዚህ ክፍል ሥር የሚነሱት ነጥቦቹ መምህሩ ስለቋንቋ ባሕርይ አጠቃላይ [illegible]

መጻህፍት በቂ መረጃ፣ ስለ ቋንቋ ማስተማር የተለያዩ አቀራረቦችና የማስተማር ዘዴዎች ግንዛቤ የሚጠበቅበት ነው—መምህሩ::

ሀ. <u>ስለ ቋንቋ ትምህርት /ማስተማር አጠቃላይ ግንዛቤ/ መረጃ ሊኖረው ይገባል::</u>

ቋንቋን በማስተማር ሙያ ውስጥ የተለያዩ የማስተማር አቀራረቦች /approaches/ እና የማስተማር ዘዴዎች መኖራቸውን ማወቅ ለሰለጠነ መምህር ጠቃሚ ነው:: የአፍ መፍቻ ቋንቋን ለማስተማር /ሀሊዴይ:1965/ እና ሁለተኛ ቋንቋን ለማስተማር በተለያዩ ጊዜያት የወጡ ልዩ ልዩ አቀራረቦች /ዘዴዎች/አሉ:: /ስተርን 1983:452–76/:: እነዚህን አቀራረቦች /ዘዴዎች ማወቅ በመምህርነቱ ለሚያደርገው የተሟላ እድገትና እንቅስቃሴ መሠረት ይሆነዋል:: ለእምሮአዊ ግንዛቤው እንዲዳብርም ይረዳዋል::

ለ. <u>በማስተማር ስራው ላይ ስለሚገለገልባቸው ወርሃ ትምህርትና ማስተማሪያ መጽሐፍ ጥልቅ ግንዛቤና በቂ መረጃ ሊኖረው ይገባል::</u>

ይህም ማለት ወርሃ ትምህርቱ፣ ለማስተማሪያነት የተመረጠው /የተዘጋጀው መጽሐፍ፣ ሌሎች ደጋፊ ቁሳቁሶች/ ካርዶች፣ ቀርጻቅርጾች፣ ቻርቶች፣ የቋንቋ ማስተማሪያ ላቦራቶር ቁሳቁሶች፣ ቴፕሪከርደርና የመሳሰሉት/ሁሉ በማስተማር ሙያው ላይ ሊያስፈልጉት ስለሚችሉ ስለ አገልግሎታቸው ሊያውቅ ይገባዋል:: /ማስተማሪያ መጽሐፍ በሌለበት በታ ራሱ ለማዘጋጀት የሚያስችለው/ የመረጃ ሊኖረው እንዲችል ሥልጠናው መርዳት አለበት/

ሐ. <u>ስለሚያስተምረው ቋንቋ በቂ መረጃ ሊኖረው ይገባል::</u>

ስለሚያስተምረው ቋንቋ በቂ መረጃ ይኖረው በሚገባበት ጊዜ ሊተኮርባቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ:: መምህሩ ወደ ሥልጠና ከመምጣቱ በፊት ስለ ቋንቋ ባሕርይ የተሟላ ግምት ሊኖረው

ይችላል፡፡ ለምሳሌ ይህ ቋንቋ ጥሩ ነው፣ መጥፎ ነው፣ ደስ አይልም/ የመሳሰሉትን አመለካከቶች ይዞ ሊመጣ ስለሚቻል ይህን ተገንዝቦ ትክክለኛውን ማስረዳት — ይህ አንዱ ነው፡፡ ሌላው ስለሰው ልጅ እና ስለእንስሳት መግባቢያ ልዩነት፣ ስለሀፃ ናት የአፍ መፍቻ ቋንቋ መልመድ ዕድሜና አለማመድ ሁኔታ፣ ስለ አባላት ልሣናትና የእነሱ መጓደል በቋንቋ ላይ ስለሚኖረው ተጽእኖ፣ ስለቋንቋ ማህበራዊነት ሁሉ ማስገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ኅብረተሰቡ ስለቋንቋ ያለውን ልዩ ልዩ ማህበራዊ አስተያየ ቶች መገንዘብ የቋንቋውን ልዩ ልዩ ገጽታዎችና ዓይነቶች /ዘዬ/ መረዳት፣ ቋንቋው ከሌላ ቋንቋ ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ሣቢያ ስለሚፈጠሩ አዳዲስ ክስተቶች /መወራረስ፣ መዋዋስ፣ መጥፋት/ ስለ ቋንቋው ሥነ ጽሁፍ፣ ስለቋንቋና ተጠየቃዊ አካሄድ ስለመሳሰሉት ሁሉ ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

የቋንቋ መምህር ስለሚያስተምረው ቋንቋ ምንነት በባለሙያ የተሰጡ ገለፃዎችን /descriptions/ ማወቅ አለበት፡፡ /ስለ ቋንቋ የተሰጡ ገለፃዎችን የቋንቋ መምህሩ ማወቅ እንዳለበት ዊደሰን /1991:74-75/ ያስገነዝባሉ፡፡ የገለፃዎች እው ቀት ሲባል በተለይ በሚያስተምርባቸው መሣሪያዎች እና ደረጃ ውስጥ የሚገኙትን የቋንቋ አካሎች የሚመለከተትን መረጃዎች በይበልጥ ቢያውቅ ይመረጣል፡፡ በማለት ስትሪቨንስ ያስረዳሉ፡፡

3. <u>የንድፈ ሃሳብ ክፍሎች</u>

ሌላው በስትሪቨንስ የተቀረበትና ለቋንቋ መምህርነት የሚሰለጥን ዕጩ መምህር የሚቀርብለት ሙያ ነክ የስልጠና ትምህርቶች ውስጥ እንደ አንዱ ክፍል የሚታየው የንድፈ ሃሳብ ክፍሎችን የሚመለከት ነው፡፡

የቋንቋ ማስተማር ሙያ ከልዩ ልዩ ሙያዎች ጋር ግንኙነት

የተማረውንና ያል ተማረውን፣ ያወ ቀውንና ያላወ ቀውን፣ የገባውንና ያልገባውን ለመለየት እንዲሁም መምህሩ የትምህርት ይዘቱን ሲያቀርብ ለተማሪው በሚመጥን አኳኋን ማቅረብ አለማቅረቡን ለመረዳት እንዲቻል አንዱ ዓይነት ማረጋገጫ ሥልተ መቀየስ ያስፈልጋል፡፡ ይህም የማረጋገጫ ስልት መለመኛ /ፈተና ነው /ሄይዝ 1991፣ ማክገራዝ፡1987፣ ሸው 1987 ማዱሰን፡1983/፡፡

በዚህ የተነሣ መለመኛ/ፈተና የሥራ ፍሬን፣ የድክም ጎን ለማወቅና ደካማ ጎንን ለማሻሻል የሚበጅ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ እንደ ቋንቋ ትምህርት ዐውቀት፣ ክህሎት፣ የማስተማር ዘዴና ለምዱ ሁሉ ከቋንቋ ትምህርት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው በመሆኑ በስልጠና ወቅት በትምህርት ይዘትነት መቀረብ ይገባዋል /ደጀኑ፡1991 ሸው፣1987፣ ሀሪሰን፡ 1983፣ ክነፋ፣ ሸዋ፣ 1981 ኢ.ት.አ./

መለመኛ/ፈተና በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ከማስተማር ሙያ ጋር የተያያዘና የቀረበ ግንኙነት ያለው መሆኑን ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡ ለአብነት ያክል የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት፡፡

> ...ማስተማርና መፈተን የተቀራኙና የተወሳሰቡ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ፈተና የከፍለን ውስጥ የመማር ማስተማርን ሥራ ክትትሉ የሚመጣ በመሆኑ ለተማሪ ውም ሆነ ለመምህሩ የሚሻሻሉበትን አቅጣጫ በማሳየት ረገድ ጠቃሚ መረጃ ይሰጣል፡፡ /ሀሪሰን፣1983፡1/

በጥቅሉ ፈተና እና ማስተማር የተገናኙና የተቀራኙ እንደሆኑ፣ ለመ ምህሩም ሆነ ለተማሪው የማሻሻያ ሃሳቦችን መረጃዎችን የሚያቀብል የትምህርት አካል መሆኑን ያስረዳል፡፡ ፈተና ይህን ዓይነት ገለጋሎት ከሰጠ ደግሞ ለቋ ንቋ ፈተና ምንነት፣ ዓይነትና አገልግሎት፣ ስለአዘገጃጀት ሥልት በቂ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ የትምህርት ይዘት በሥልጠናው ወቅት ሊቀርብለት ይገባል፡፡

ከዚህ በላይ በቀረበው የዝግጅ ጽሑፎች ቅኝት ውስጥ ለቋንቋ መምህርነት የሚሰለጥን ዕጩ መምህር በሥልጠና ላይ እያለ ሊቀርቡለት ስለሚገቡ ትምህርቶች ይዘት አንዳንድ ነጥቦች ተነስተዋል፡፡ ትምህርቶች ስለሚያካትቷቸው ይዘት ምንነት

ሙያዎች ጋር ግንኙነት ያለው በመሆኑ እጅግ ውስብስብ ነው። ይሁን እንጂ ከልዩ ልዩ ሙያዎች ጋር ስንል ሙያዎቹ፤ ሥነ-አእምሮአዊ ሥነ-ልሣን፣ማኅበራዊ ንድፈ ሃሳብ እና ሥነ-ትምህርትን ሁሉ የሚያቅፍ ነው። እነዚህ የተዘረዘሩት ልዩ ልዩ የንድፈ ሃሳብ ክፍሎች ቋንቋን ለማስተማር የሚያገለግሉ ግንዛቤያችን በማስጨበጥ ረገድ የሚጠቀሙ ቢሆንም በአገልግሎት ቀደም ተከተላቸው ባለሙያዎች ገና ያልተስማሙባቸው መሆኑን አብሮ መገንዘብ ያሻል። ይሁን እንጂ ቋንቋን ለምን እንደምናስተምር፣ እንዴት እንደምናስተምር መሠረታዊ የሆኑ ንድፈ ሃሳባዊ መርሆዎችን በማስጨበጥ ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። /ዓፋ፤ 1983፤ 118-120፤ ስተርን፡1983፤ ዊደውሰን፡ 1991/

ከዚህ በላይ የቀረቡት ሦስቱ ክፍሎች በቋንቋ መምህራን ስልጠና የሚታሰቡ ዋና ዋና ይዘቶች መሆናቸውን ልዩ ልዩ ምሁራን የተስማሙበት ሲሆኑ ከሦስቱ ውስጥ የኋላ ክፍሎች የሚለው የበለጠ ትኩረት ሊደረግበት እንደሚገባ ስትሪቨንስ /1977፡77-78/ አጠንክረው ያስገነዝባሉ።

ከእዚህ በላይ ከቀረቡት ዝርዝሮች በተጨማሪ በቋንቋ መምህራን ሥልጠና ውስጥ ሊካተት የሚገባው ሌላው የኮርስ ይዘት ቋንቋን የመፈተን ጉዳይ ነው። ይህንኑ በተመለከተ ከዚህ ቀጥለን እንገልጻለን።

## 4. ቋንቋን መፈተን

በቋንቋ መምህር ሥልጠና ወቅት ሊካተት የሚገባው ሌላው ዋነኛ የትምህርት ይዘት ቋንቋን የመፈተን ጉዳይ ነው። ምክንያቱም አንድ የቋንቋ አካል በትምህርት አይነተኛ ዓላማ ተነድፎለትና ዓላማውንም ግብ የሚያስመታ ይዘት ተመርጦለት ለትምህርት ከቀረበ በኋላ፣ መምህርና ተማሪ በክፍል ውስጥ ተገናኝተው ያንን የትምህርት ይዘት ተግባራዊ በማድረግ የማስተማርና የመማር ክንዋኔ ያካሂዳሉ። መምህሩ ያስተምራል፣ ተማሪው ይማራል፣ ይለማመዳል፣ ችሎታውን ያዳብራል። የመማር [illegible]

ለማበራራትና ለመተንተንም ጥረት ተደርጓል::

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ከላይ በቀረበው ቅኝት ውስጥ በተለያዩ ባለሙያዎች የቀረቡትን ዝርዝር ነጥቦች በማብላላትና ማዕከላዊ ጭብጣቸውን በማዋሃድ ከዚህ በታች የቀረቡትን ለቋንቋ መምህራን ስልጠና ኮርሶች ውስጥ በይዘትነት ጎልተው የታዩትን ዋና ዋና ርዕስ ጉዳዮች ለማውጣት ተሞክሯል::

### 2.1.4. በተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት መሠረትነት የተወጣጡ መስፈርቶች

ሀ. **የተሟላ የቋንቋ ችሎታ**

በቋንቋ መምህርነት እንዲሰራ በመሰልጠን ላይ የሚገኝ መምህር በቋንቋ ክሂሎች/ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ/ በሚገባ የሰለጠነና በብቃት የሚገለገልባቸው መሆን አለበት:: ለሚያስተምርበት የክፍል ደረጃ በምሳሌነት የሚታይ መሆን ይገባዋል:: በሚገባ የሚያዳምጥ፣ የሚናገር፣ የሚያነብና የሚጽፍ ሆኖ እንዲገኝ ሥልጠናው ሊረዳው ይገባል:: ይህ እስካልሆነ ድረስ ተማሪዎቹ የእነዚህ ክፍሎች ባለቤቶችና ተጠቃሚዎች መሆን አይችሉም::

ለ. **የቋንቋን ባህርይና የሥነ–ልሣንን ሚና መገንዘብ**

የቋንቋን ተፈጥሮአዊ ባሕርይ መረዳት፣ የቋንቋና የሰው ልጅ ቁርኝት፣ የቋንቋን መሣሪያነት፣ የቋንቋን የእርስ በእርስ ግንኙነት ዝምድና እና ልዩነት መረዳት ያስፈልገዋል:: የቋንቋን ጥናት ታሪክ ማወቅ ስለሚያስተምረው ቋንቋ ምንነት ለማወቅና ለመመራመር እንዲችል በማስተማሪያ መሣሪያ ዝግጅት ጊዜና የትምህርት ይዘትን ለመምረጥ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ለመረዳት ያግዘዋል /በተርነር፣ 1983:173–87/

ሐ. **የሚያስተምረውን የቋንቋ አገልግሎት /ጠቀሜታ/ መረዳት**

አገልግሎት እንደሚውል ማወቅ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቦታውን መረዳት፣ ቋንቋው በታሪክ ያሳለፈባቸውን ልዩ ልዩ ክንዋኔያቸ፣ አገልግሎቶቹ ስፋትና ጥበት መገንዘብ ይገባዋል:: የቋንቋው የሥነ—ጽሁፍ ውጤቶች፣ የመገናኛ አገልግሎት ስፋትና የአደባባይ መግባቢያነት ደረጃው ሁሉ ለዕጩ መምህሩ ሊያኙለት ይገባል::

ወ. <u>የቋንቋ ማስተማር ዘዴ</u>

ቋንቋ ራሱን የቻለ ትምህርት እንደመሆኑ መጠን ከሌሎች ትምህርቶች የሚለይበት ባሕርያት አሉት:: እነዚህ ባሕርያቱ በትምህርት አሰጣጥ ዘዴም ላይ ይታያሉ:: በዚህ የተነሳ ላለፉት ብዙ አመታት ቋንቋን ለማስተማሪያ ያገለግላሉ ተብለው አያሌ ዘዴዎች ቢቀረጹ፣ በሥራ ላይ ውለው ሲፈተኑ ኖረዋል:: አዳዲሶችም እየተቀረጹ ይገኛሉ:: እነዚህን ልዩ ልዩ ዘዴዎችን የአቀራረብ ስልቶች ለቋንቋ መምህርነት የሚሰለጥን ዕጩ መምህር ሊመለከታቸው ይገባል:: በሥራ ላይ ሲሰማራ የሚስማማውን እንዲመርጥ አዲስም ስልት እንዲቀይስ ይረዳዋል::

ሠ. <u>ቋንቋውን መፈተን</u>

የቋንቋውን ትምህርት በተገቢው መንገድ መከሄዱ አለመከሄዱን ተማሪው ተፈላጊውን ችሎታ መቀሰም አለመቀሰሙን፣ የተመረጠው የትምህርት ይዘት ለተማሪው ለምዱ፣ ችሎታና ዕድሜ መመጠን አለመመጠኑን፣ ለመለየትና በየትኛውም በኩል የታየ ጉድለት ካለ ለማሻሻል እንዲቻል ፈተና የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ፣ ስላለው የፈተናን ምንነት ዐይነት አገልግሎትና አዘገጃጀት የሚመለከት የትምህርት ይዘት በመምህራን ሥልጠና ውስጥ መካተት አለበት::

ረ. <u>ተጓዳኝ መስኮችን መቃኘት</u>

ከቋንቋና ከቋንቋ ትምህርት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ማህበራዊ ሥነ—ልሣን፣ ትርጉም የመሳሰሉና ሌሎች የተለያዩ

ሙያ መስኮች ንድፈ ሃሳቦችን ቢያውቁ፣ ተግባራዊ አገልግሎታቸውን ቢረዱ ለቋንቋ ማስተማሩ ሥራ ይረዱት ይሆናል የሚል እምነት አለ፡፡ ስለዚህም ከስልጠናው ሂደት ውስጥ ሊያገኙቸው ወይም ሊቀርቡለት ይገባል፡፡

ከዚሁ በላይ ያየናቸው ዋና ዋና ርዕስ ነገሮች በቋንቋ መምህር ስልጠና ወቅት ሊቀርባቸው ከሚገቡ አጠቃላይ ጥናቶች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡ ይህንኑ በማመን በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሚሰጡትን ዐበይት የአማርኛ ትምህርቶች ይዘት ለመመርመርና ለመተንተን እንደ ዋና ዋና የመመዘኛ ነጥቦች እንጠቀምባቸዋለን፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ቀደም ሲል በዚህ ምዕራፍ መንደርደሪያ ላይ እንደ ጠቆምነው ስለ ይዘት ትንተና ምንነት አገልግሎትና የምርምር ስልትነት አጭር ያለ ማብራሪያ እናቀርባለን፡፡

## 2.2. የይዘት ትንተና ምንነቱ አገልግሎቱና የምርምር ስልትነቱ

የዚህ ጥናት የምርምር ስልት በገላጭ የምርምር ዘዴ ውስጥ የሚታቀፈው የይዘት ትንተና ስልት መሆኑ ቀደም ሲል የተገለፀ ነው፡፡ ይሁንና ስለይዘት ትንተና ምንነት አገልግሎትና የአሰራር ስልት በውል የተብራራ ጉዳይ የለም፡፡ የዚህ ንዑስ ምዕራፍ ዓላማ ይህንኑ ጉዳይ የሚያነሳ ይሆናል፡፡

### 2.2.1. የይዘት ትንተና ምንነት

የሥነ-አእምሮ መዝገበ ቃላት የይዘት ትንተናን እንደሚከተለው ይገልፀዋል፡፡

> የይዘት ትንተና የተለያዩ ጽሁፎችን የያዙ ሰነዳዊ መልዕ
> ክቶችን፣ ሀሳቦችን፣ ስሜቶችና አስተያየቶች የሚተነተኑበትን
> የተለያዩ ዘዴዎች የሚያቅፍ አጠቃላይ ስያሜ ነው፡፡ እንዲህ
> ያለ ትንተና በአብዛኛው፣ የተወሰኑ ቃላት፣ ሀረጋት፣ ገበ
> ዎች የሀሳብ መገለጫዎችና መሰሰሉት፣ በሰነዱ ውስጥ ስንት
> ጊዜ እየተደጋገሙ እንደሚመጡ ለማወቅ የሚያስችሉትን ሰቆ
> ያሉ ስሌታዊ ዘዴዎችን ሁሉ ይይዛል/ረበር፣ 1985፡152/

ይህን ገለፃ እንደመነሻ አድርገን ስንመለከተው የይዘት ትንተና በርካታ ርዕስ ጉዳዮችን ለመመርመርና ምንነታቸውን፣ አገልግሎታቸውን፣ ጥቅም ጉዳታቸውን ለማወቅ የሚረዳን የምርምር ስልት ነው፡፡

ከመዝገበ ቃሉ ገለፃ አለፈን በምርምር ሥልትነቱ ምንነቱን በሰፋት ከገለፁትና ካስረዱት መካከል የክሪፔንደርፍን ገለፃ እናገኛለን፡፡ እንደሳቸው አባባል

> የይዘት ትንተና የተሰበሰበውን መረጃ በራሱ አውድና በሌላም
> የትንታኔ ስልት ቢተነተን ተገቢና አስተማማኝ ድምዳሜ ላይ
> ሊያደርስ የሚያስችል የምርምር ስልት ነው፡፡/ክሪፔንደርፍ፣
> 1984፡21/

የሚል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ሆልስቲ የተባሉ ተመራማሪ በበኩላቸው ፡-

> የይዘት ትንተናን በልዩ ልዩ የእውቀት መስኮች ለሚነሱ
> አያሌ የምርምር ችግሮችን ለመፍታት ጠቃሚነት ያለው
> መሠረታዊ የምርምር መሣሪያ አድርጎ የመቁጠር አዝማሚያ
> ጎልቶ ይታያል /ሆልስቲ፣ 1969፡3/

.../30

በማለት በሰምንነቱ በአጠቃላይ አይማሩ ያበረክላሉ::

ከላይ የቀረቡት ሃሳቦች ስለይዘት ትንተና ምንነት አጠቃላይ ፍንጭ የሚሰጡን ሲሆን ከትምህርት ምርምር ሙያ ጋር በተያያዘ /በተዛመደ/ መስኩ ደግሞ ሉኬበ ከውል የተባሉ ተመራማሪ በገላጭ የምርምር ዘዴ ሥር ይመድቡታል:: እንዲሁም ከታሪካዊ የምርምር ዘዴ ጋር ዝምድና ያለው መሆኑን ጭምር እንደሚከተለው ያቀርቡታል::

> የይዘት ትንተና የመልዕክቱን ወይም የሰነዱን ይዘት በአይነት በአይነቱ በመመደብ፣ በማስላትና በማነፃፀር ላይ ስለሚያተኩር አንዳንድ ጊዜ ሰነዳዊ፣ መረጃዊና ድርጊታዊ እየተባለ ይጠቀሳል:: የመልዕክት ሰውውሉ በኦፊሴላዊ መገለጫዎቹ /የህዝብ ቁጠራ፣ የሰደተ፣ የወንጀል ትምህርት ቤት፣ የድርጅትና የግል/ ወይም ማንኛውም የተጻፈ ወይም የታተመ ማዘዣ ወይም ስዕላዊ መገለጫ የሚያጠቃልል ሊሆን ይችላል/ክውል1993:415/::

ሉኬበ ከውል እንደሚሉት በመዝገብ የሰፈረ፣ በሥዕል መልክ የተቀመጡ፣ የታተሙ ሆኑ ያልታተሙ ሰነዶች፣ የንግግር ቅጂዎች ሁሉ በዚህ በይዘት ትንተና ሥልት ሊጠኑ ሊመረመሩና ሊታወቁ ይችላሉ::

ከአጠቃላይ ጉዳዮች አልፈን ወደትምህርት ምርምር ስንመጣ፤ የመርሀ-ትምህርት ትንተና፣ የማስተማሪያ መጻሕፍት ይዘት ቀንብርና ገፅታ ትንተና፣ የትምህርት አቀዱ፣ የተለያዩ ት/ቤቶች፣ ተቋማትና ኮሌጆች አቋምና የወደፊት ተስፋ ሁሉ በዚህ ስልት ምርምር ግንዛቤ ሊገኝበት ይችላል /ዝኒከማሁ/

## 2.2.2. የይዘት ትንተና አገልግሎት

ከላይ የይዘት ትንተናን ምንነት ስንገልፅ የተለያዩ ርዕስ ጉዳዮችን ለመመርመር እንዲያገለግል ጠቅሰናል:: ለተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች መመርመሪያና መተንተኛ ያገለግላል ስንልም፤ በትምህርት ቤት ውስጥ ለተወሰነ ክፍል በማስተማሪያ መጽሐፍትነት የሚውሉ መጻሕፍትን ይዘት መርምሮ ለመርዳት፣በሌላ የምርምር ዘዴ አማካይነት የተደረገ ምርምር ካለ የምርምሩን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንደ አንዱ የማመሳከሪያ ስልት (Cross validate) ያገለግላል:: መላምቶችን

ለመረዳትና ገዲሬ ሃሳቦችን ለመፈተን ይጠቅማል:: /ብርገ እናጋል 1989፣522/

የይዘት ትንተናን ገልጋሎት አላይ ካየነው መጠነ-ሰፊ መስክ በመመለስና በጣየበበ በትምህርታዊ ምርምር ውስጥ ለንገለገለበት እንችላለን:: ሉኬሽ ኮውል /1993: 413-415/ እንደጠቀሙት፣ የይዘት ትንተና በትምህርታዊ ምርምር ውስጥ የሚከተሉትን ገልጋሎቶች ይሰጣል::

ሀ. <u>የትምህርት ዓላማን ሥርዓተ ትምህርትንና የትምህርት ይዘትን ቀንጅት ለመመርመር ይረዳል::</u>

በትምህርት ቤት ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች ተግባራዊ የሚሆኑ የአንድ ሥርዓተ ትምህርት የተለያዩ የትምህርት ይዘቶች ከአጠቃላዩ የትምህርት ዓላማ አንፃር ሊተነተኑ ለመረመሩና ሊገመገሙ ይችላሉ:: መምህራንም ገለፀ ያልሆነላቸውን የሥርዓተ ትምህርት አካል በይዘት ትንተና ሥልት አማካይነት ተንተነው ምላት ጉድለቱን ለረዳና የጎደለውን ሊያሟሉ ይችላሉ:: የመማሪያ መጻሕፍትን፣ የጠቀላላ ዕውቀት መረጃዎችን መጽሔቶችንና ጋዜጦችን በመመርመር ለአጠቃላይ ሥርዓተ ትምህርት ሊጠቅሙ /ሊያገለግሉ/ የሚችሉበትን ሁኔታ ሊያመቻቹ ይችላሉ::

ለ. <u>የይዘት ትንተና ሌላው ገልጋሎቱ በምዘና በኩል ነው::</u>

ሥርዓተ ትምህርቱ ከዋናው ዓላማ ጋር መጣጣም አለመጣጣሙን ለማወቅ፣ የተማሪውን ዕውቀትና ችሎታ ለመለካት የሚያስችሉ የመመዘኛ መሣሪያዎች /ፈተናዎች፣ መለመኛዎች/ ለማስናዳት ያገዛል::

ሐ. <u>የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ደረጃ ለመረዳት የይዘት ትንተና ሚና አለው::</u>

ተማሪዎች እንዲማሩበት በቀረበው መጽሐፍ ውስጥ ያለው የትምህርት ይዘት ከተማሪዎቹ የመገንዘብ ችሎታ ጋር የተጣጣመ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ የይዘት ትንተና ሥልት ያገለግላል::

ጠ. <u>ሀብረተሰብ ስለት/ቤት ያለውን አመለካከት ለማግኘት ይጠቅማል፡፡</u>

የትምህርት ባለሙያዎች ሀብረተሰቡ ስለትምህርት ቤት ያለውን አስተሳሰብ ለማወቅ ቢፈልጉ በተለይ የአሳብ ማሰባሰቢያ /መርጃ መለኪያ/ ስልቶች /መጠይቅ፣ ቃለመጠይቅ/ በመጠቀም መረጃ ሰብስበው ይዘቱን በመተንተን የሀብረተሰቡን አስተሳሰብ ሊያውቁ ይችላሉ፡፡

ሠ. <u>ማህበራዊ ቅኝት አካሄድ የት/ቤትን ሚና ለመገንዘብ ይበጃል፡፡</u>

ሀብረተሰቡ ከት/ቤት ምን እንደሚፈልግና ት/ቤትም በማህበራዊ ወቸት ውስጥ ያለውን ሥፍራ ለመረዳት ያገለግላል፡፡ የዜጎችን የመማር ፍላጎት በማጥናት የወደፊቱን ትውልድ የትምህርት ዕድል በመወሰን ረገድ በሚደረግ ጥረት ውስጥ በፍንጭ ሰጭ ስለትነቱ ይጠቅማል፡፡

ማህበራዊ ቅኝት ለማድረግ የሚነሳ በይዘት ትንተና ሥልት የሚገለገል ተመራማሪ የምርምር መረጃዎችን በተለይ ዘዴዎች /ቃለመጠይቅ፣ መጠይቅ፣ የጊዜ ሰሌዳ፣ የመዘና ስኬሎች፣ ቀጥታ ምልከታ፣ ስታትስቲካዊ መረጃዎችን፣ የአካባቢ ጥናቶች ሁሉ/ ሊጠቀም ይችላል፡፡ በነዚህ መሣሪያዎች ያገኘውን መረጃ ይዘት በመተንተን ለሀብረተሰቡ የሚያስፈልገውን ነገር ለመጠቆም እንደሚችል ተመራማሪዎች ያስገነዝባሉ፡፡

የይዘት ትንተናን፣ በሰነድ ትንተና ነት የሚመለከቱት አሬይ /1985/ ይዘት ትንተና ከተራ ቁጠራ አልፎ በርካታ ማህበራዊ ጉዳዮችን ለመመርመር የሚያገለግል መሆኑን እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> አንዳንድ ጊዜ እንደ ይዘት ትንተና የሚቆጠረው የሰነድ ትንተና፣ ሰነዶችን በተናጠል በመቁጠር ላይ ብቻ ሳይወሰን ሌሎች ሽንደማህበራዊና ሥነልቦናዊ ጉዳዮችንም ለማጥናት ያገለግላል /አሬይና ሌሎች 1985:327/፡፡

የሆነ ምርጫ ማድረግ አይኖርበትም:: እና የሚጓጓዙበትን እቃ ይመጥነዋል እንደሚባለው ለስራው የሚችለውን መጠን እና አስተማማኝ መረጃ ሊያስገኝለት የሚችለውን ናሙና መምረጥ ይኖርበታል:: ለምሳሌ፤ አንድን መጽሐፍ ሙሉ በሙሉ ወስዶ በውስጡ ያሉትን ርዕሰ ጉዳዮች ሁሉ ከመተንተን ይልቅ፤ የመጽሐፉን አንድ ወይም ሁለት ምዕራፎች፣ ወይም ጥቂት መሰመኛዎቹ፣ አንድ ወይም ሁለት ምንባብ ... የመሳሰሉትን ወስዶ በመተንተን በለመጽሐፉ አጠቃላይ ግንዛቤ ሊያገኝ ይችላል::

በአጠቃላይ ይዘት ትንተና በተመረጠ የምርምር ርዕሰ ነገር ባህርይ መሠረትና የምርምር ዓላማ ላይ ተመሥርቶ የማመሳከሪያ ንድፈ ሃሳቦችን በመመርኮዝ አንዳች እውነት የሚፈለገበት የምርምር ሥልት መሆኑን ለመረዳት ይቻላል::

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የጥናቱ አሠራር ዘዴና የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች

### 3.1 የአሠራር ዘዴ

የዚህ ጥናት አጠናን ዘዴ ከገለፃዊ የምርምር ዘዴ ውስጥ የይዘት ትንተናን ሥልት የሚከተል መሆኑ ቀደም ሲል ተገልጿል:: የጥናቱ ዋና ዓላማ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የዲፕሎማ ወርሀ ግብር የሚሰጡትን ዐቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት መተንተንና መገምገም መሆኑ ተጠቅሷል:: የኮርሶቹን ይዘት ለመገምገም ደግሞ የኮርሶቹን አጠቃላይ ዓላማና የትኩረታቸውን ርዕሰ ጉዳይ መርዳት ያስፈልጋል:: ይህንን ለማድረግ ሁለት የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅመናል:: አንዱና ዋነኛው ከላይ የተጠቀሰው የይዘት ትንተና ሥልት ነው:: ሁለተኛው ዘዴ የጽሑፍ መጠይቅ ነው:: መጠይቁ በይዘት ትንተና ሥልት ከተገኘው መረጃ በተጨማሪ አንዳንድ ያልታዩ ጉዳዮች ካሉ እነሱን ለማውጣጣት የተጠቀምንበት ዘዴ ነው::

የይዘት ትንተናን ስናካሂድ ከዝግጁ ጽሁፎች ቀኘተና ትንተና ውስጥ ያውጣጣናቸውን የሚከተሉትን መስፈርቶች ይዘን ነው::

መስፈርቶቹ፦

1. የተሟላ የቋንቋ ችሎታ መኖር
2. የቋንቋ ባህሪና ሥነ–ልሣንን ግና መረዳት
3. የቋንቋን አገልግሎት/ጠቀሜታ/ መገንዘብ
4. የቋንቋን ማስተማር ዘዴዎች መያነት
5. የቋንቋን ፈተና አዘገጃጀት መረዳት
6. ተጓዳኝ/ደጋፊ/ መስኮችን መዳሰስ

የሚሉት ናቸው::

በእነዚህ መሥፈርቶች ሥር የሚጠቃለሉትን ይዘቶች ለመምረጥ፣ ለመወሰንና ለመተንተን አንጓዎችን የልዩ ልዩ ሰነዶችን ይዘት ተመልክተናል:: እነሱንም በሚከተለው ዓይነት በየመለኪያቸው እና ቀርባለን::

## 3.2 የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች

### 3.2.1 ሰነድ ምርመራ

ሰነድ ምርመራ ስንል ከጥናቱ ጋር ዝምድና ያላቸውን ማንኛቸውንም በጽሁፍ የሠፈሩ መረጃዎችን ሁሉ መመርመርን ያጠቃልላል፡፡ የኮርሶቹን ዓላማና ዝርዝር ቢጋር የያዘ ሠነድ፣ የተማሪዎች ማስታወሻ ደብተር፣ የኮርሱ የመጨረሻ ፈተና ይዘት ምርመራ ሁሉ በዚህ ውስጥ የሚታቀፉ ናቸው፡፡

#### 3.2.1.1 ዓላማና ቢጋር

በዘገባው ጽሑፎች ቅኝት ውስጥ ስለይዘት ትንተና ምንነትና አገልግሎት ሲገለጽ በዋናቸውም መልኩ በጽሑፍ የሚገኙ የመረጃ ምንጮች በሰነድነት ሊታዩ እንደሚችሉ ተጠቁሟል፡፡ በዚሁ መሠረት በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ከተዘጋጀው ካታሎግ /1992/ እና በሥሩ ከሚገኘው ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ ክፍል በተገኘው ሰነድ ውስጥ የሚገኙ ዐበይ ኮርሶች የእያንዳንዳቸው ዓላማና ዝርዝር ቢጋር ግንኙነት /ዝምድናው/ ተተንትኖ ተመዛዝኗል፡፡

#### 3.2.1.2 የተማሪዎች ማስታወሻ ደብተር አመራረጥና ምርመራ

ጥናቱን ዓላማ ገቢ ያስመታሉ ተብለው በቢጋሩ ውስጥ የተዘረዘሩት ዋና ዋና ይዘቶችና ዝርዝሮቻቸው ወደ ተማሪው መተላለፋቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ ይህንኑ ለመረዳት የተማሪዎች ማስታወሻ ደብተር በመረጃ ምንጭነት ተወስዷል፡፡

የሁሉንም ተማሪዎች የማስታወሻ ደብተር በሙሉ ወስዶ ለኮርሶቹ የመዘገቧቸውን ይዘቶች ለመመርመር አመቺ ባለመሆኑ አስተማማኝ ውክልና የሚያስገኝ ናሙና ለመምረጥ ጥረት ተደርጓል፡፡

የተማሪዎቹን የማስታወሻ ደብተር ለመምረጥ በቅድሚያ የተማሪዎቹን ቁጥርና ደረጃ ማወቅ አስፈላጊ በመሆኑ የሁለተኛ ዓመት የሚገኙ ተማሪዎች ብቻ በጥናቱ ውስጥ እንዲታቀፉ ተደርጓል፡፡ ይህ የተደረገው፣ 1ኛ. ካሉት 14 ኮርሶች ውስጥ ዘጠኙን ሙሉ በሙሉ በመማራቸው ተገቢ ግንዛቤ አግኝተዋል ተብሎ ስለታሰበና፣

25ኛ. የተፈታ 5 ክርክሮች ቢሆኑ እስከ ግንቦት መጀመሪያ ሳምንት ድረስ ስለ ተማሪዎቹ ቢያገበ 2/3ኛውን ያህል ደረጃ እንደሚያገኙ በመተማመን ነው።

በዚሁ መሠረት የሁለተኛ ዓመት የሚኙሉማ ተማሪዎች የ1986 ዓ.ም. የመጀመሪያ ሴሚስተር በተገቢው ነጥብ አጠቃለው ወደ ሁለተኛ ሴሚስተር የተዛወሩትና አሁን በመማር ላይ የሚገኙት ጠቅላላ ቁጥር 18 መሆኑ ከኮሌጁ ሪኮርድ ማዕከል ተገኝቷል። ከነዚሁ ውስጥ 7/ሰባቱ/ ዓይነ ስውራን በመሆናቸውና እነርሱ የወሰዱትንም ማስታወሻ /ካሴ/ በመመርመር የተለየ ችሎታን ስለሚጠይቅ በጥናቱ ውስጥ አልተጠቃለሉም። በቀሩት 11/አስራአንዱ/ ተማሪዎች ውስጥም የስድስቱ ደብተር ብቻ በናሙናነት ተወስዷል። ይህ አሃዝም ከጠቅላላዎቹ 18 ተማሪዎች አንፃር ሲሰላ 1/3ኛውን ይሸፍናል።

አሥራ አንዱን ተማሪዎች በውጤታቸው ቅደም ተከተል መሠረት ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ከደረደርን በኋላ ከዝቅተኞቹ ሁለቱን፣ ከመካከለኞቹ ሁለቱንና ከከፍተኞቹ ሁለቱን በመውሰድ ሥርዓታዊ የናሙና አመራረጥ ሥልትን ተከትለናል።

ለእያንዳንዱ ትምህርት የስድስት ተማሪዎች ደብተር የተመረጠው መምህሩ ዝርዝር ቢጋሩን ተከትለው፣ የሚገልጹትን፣ የሚያስረዱትን፣ የትምህርት ይዘት ተማሪዎቹ በማስታዎሻቸው ላይ ሲመዘግቡ በማዳመጥ ችሎታ፣ በፍሬ ነገር ምርጫ፣ በአመዘጋገብ ፍጥነት መለያየት የተነሣ ሊፈጠር የሚችለውን የማስታወሻ አወሳሰድ ችግር ለማጥበብ እና አንዱ የሰጠውን ሌሎቹ ይመዘግቡት ይሆናል በሚል ግምት ነው።

ከኮሌጁ ካታሎግና ከትምህርት ክፍሉ በተገኘው ሰነድ ውስጥ በቀረቡት ዝርዝር ቢጋሮች ውስጥ የተጠቀሱት ዋና ዋና ሀሣቦችና ዝርዝሮቻቸው በተማሪዎቹ ማስታዎሻ ደብተር ውስጥ መገኘት አለመገኘታቸው ተመርምሯል። አመዘጋገቡም በቅደም ተከተል ሆኖ በመጀመሪያው ተማሪ ማስታዎሻ ውስጥ የተገኙት ዝርዝር ርዕስ ጉዳዮች ከተመዘገቡ በኋላ ሁለተኛው ይቀጥላል። ከሁለተኛው ተማሪ የሚወሰዱት በመጀመሪያው ተማሪ ማስታወሻ ውስጥ ያልተገኙ አዳዲስ ጉዳዮች ብቻ ናቸው። ከሶስተኛው ተማሪ ማስታወሻ የሚወሰደው እንደዚሁ አንደኛውና በሁለተኛው ተማሪ ማስታወሻ ውስጥ ያልተገለጹ ነጥቦች ካሉ ነው። በዚህ ዓይነት በቀደሙት ተማሪዎች

ማስታወሻዎች ውስጥ ያሉ ተገኙት እየተመዘገቡ ሙሉ በሙሉ ከተጠናቀቁ በኋላ የተገኘውን ይዘት ከኮርሱ ዓላማና ዝርዝር ቢጋር ጋር ለማመሳከር ተሞክሯል::

### 3.2.1.3 የመጨረሻ ፈተና

የትምህርቱ ዓላማ ቢጋሩና የተማሪዎቹ ማስታወሻ ደብተር ሙሉ በሙሉ ከተገናዘበ በኋላ በዚያ ውስጥ የተገኙት የኮርስ ይዘቶች እርግጥ መምህሩ የተናገሯቸውና ያስረዷቸው፤ ተማሪዎቹ አክፍል ውስጥ አዳምጠው የመዘገቧቸው/ወይም መምህሩ ባመቸው መለኩ ተማሪዎች የራሣቸውን ማስታወሻ እንዲያስናቅ አድርጉ ከሆነ/ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የመጨረሻ ፈተናዎች ያካተቷቸው ይዘቶች ተመርምረዋል:: ከዓላማውና ከዝርዝር ቢጋሩ ጋርም ተገናዝበዋል::

### 3.2.2 የጽሑፍ መጠይቅ

በዚህ ምርምር ውስጥ የታቀፉት ዐሥሩ መምህራን በሥልጠና ላይ እያሉ የማስተማር ሙያ ልምምድ በየደረጃው አካሄደዋል:: በክፍል ውስጥ የእርስ በእርስ የማስተማር ልምምድ እና በአቅራቢያ ሁለተኛ ደ/ት/ቤቶች ለአራት ሣምንታት የማስተማር ልምምድ አካሄደዋል:: በነዚህ የማስተማር ልምምድ ወቅት ቀደም ሲል የወሰዷቸው ዐቢይ የአማርኛ ኮርሶች ምን ያህል እንደረዷቸውና ለወደፊቱ ዋና ሥራቸው ምን ያህል እንዳዘጋጇቸው ለመረዳት እንዲቻል የጽሁፍ መጠይቅ ቀርቦላቸዋል::

መጠይቁ፣ ሦስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ የመጀመሪያው ክፍል የተማሪዎቹን ዕድሜ፣ ፆታና ልምድ የሚጠይቅ ነው:: ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከዐቢይ ኮርሶች ይዘት ጋር የተዛመዱ 16 ጥያቄዎችን ይዟል:: እነዚህም ጥያቄዎች ከ4-0 በሚደርሱ /4- በጣም እስማማለሁ፣ 3 እስማማለሁ፣ 2- በመጠኑ እስማማለሁ፣ 1- አልስማማም፣ 0- በጣም አልስማማም/ አማራጮች ቀርበዋል:: መጠይቁ የተዘጋጀው ከሚመረጠው ቁጥር ግርጌ ምልክት ለማድረግ እንዲያመች ሆኖ ነው:: በሦስተኛው ክፍል 3 ጥያቄዎች ቀርበዋል:: የጥያቄዎቹ አቀራረብ፣ ተማሪዎቹ አስተያየታቸውን እንዲጽፉ የሚጠይቅ ነው:: እነዚህ ጥያቄዎች የተዘጋጁበት ዋና ምክንያት በክፍል

ሁሉት ውስጥ ያልተነሷና ምናልባትም ተማሪው የዐቢይ ክርክሩን ይዘት በማመልከት የሚሰጠው ተጨማሪ አስተያየት ካለ ለማግኘት ይረዳ ዘንድ ነው።

በአጠቃላይ በመጠይቁ ውስጥ የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች ስለ ዐቢይ ክርክራቸው ይዘቶች ያላቸውን ግንዛቤ ለመቃኘት የሚያስችሉ፤ ይህ በዛ፣ ይህ ጎደለ፣ ይህ ቢጨመር፣ ይህ ቢቀር በማለት የሚሰነዝሩት አስተያየት ካለ ለመረዳት በሚያስችል መልክ የተዘጋጁ ናቸው።

መጠይቁ የተበተነው ከዐይ ኮሥዉራቱ በስተቀር፣ ለተቀሩት አሥራአንዱም ተማሪዎች ሲሆን፣ በሙሉ ተመልሶ ተሰብስቧል። የተሰበሰበውም ሀሳብ ተጠናቅሮና ተጠቃሎ በትንታኔው ውስጥ ገብቷል።

## ምዕራፍ አራት

### 4. የአቢይ ኮርሶች ይዘት ትንተናና ግምገማ

#### 4.1 የይዘት ትንተናና ግምገማ—ጠቅላላ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በዲፕሎማው መርሀ-ግብር የሚሰጡትን ዐቢይ የአማርኛ ኮርሶች ከኮሌጁ መምህራን የማሰልጠን ዓላማ ጋር በማስተያየት ይዘታቸውን መተንተንና መመዘን መሆኑ በመግቢያችን ውስጥ በ1.2 ላይ ተገልጿል:: የየኮርሶቹን ይዘት መተንተንና ጥንካሬና ድክመታቸውን መመዘንና አንዳንድ እንደ ድክመቶች የሚቆጠሩ ካሉ የሚሻሻሉበትን መንገድ መጠቆም ደግሞ ዝርዝር ዓላማዎችን መሆናቸውን አመልክተናል::

ከዚህ አንፃር የጥናቱ ዋና ጉዳይ ወደሆነው ወደ ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ስንሸጋገር፣ የኮሌጁን ተግባራት የሚያመለክቱ የሚከተሉትን ዋና ዋና አላማዎች እናገኛለን፡፡

1ኛ/ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መምህራንን ማሰልጠን

2ኛ/ በተለያዩ የትምህርት መስኮች ዕውቀትን ማስፋፋትና የትምህርት ቀንም ሥርዓት ለማሳደግ የሚያግዝ ምርምር ማድረግ

3ኛ/ የአገሪቱን ፍላጎት የሚያሟሉ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት

4ኛ/ በመንግሥትም ሆነ በኮሌጁ አባላት የሚፈለጉና የሚታመንባቸውን ልዩ ልዩ የሥልጠና ትምህርቶች ማካሄድ/ካታሎግ 1992/::

ከላይ ከተገለፁት የኮሌጁ ዋና ዋና ዓላማዎች፣ በተ.ቁ. 1. የተጠቀሰውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ፣ ኮሌጁ ከዘረጋቸው የመምህራን ሥልጠና መርሃ-ግብሮች መካከል፣ የአማርኛ ዕጩ መምህራንን የሚያሰለጥነው የዲፕሎማው መርሃ-ግብር ይገኝበታል፡፡ ኮሌጁ በዚህ መርሀ ግብር ለሠልጣኞቹ ዕጩ መምህራን የሚያቀርባቸው ኮርሶች ሥርጭት የሚከተለውን ይመስላል፡፡

## 4.2 የኮርሶች ሥርጭት

### 4.2.1 የሊንጓ መርሀ-ገበር ኮርሶች ስርጭት

በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሊንጓ መርሀ-ገበር ለዐው የአማርኛ ደንቋ መምህራን የሚቀርቡት ኮርሶች በቁጥር 28 ሲሆኑ በክሬዲት 74 ናቸው:: ኮርሶቹ በሙሉ በሚያተኩሩባቸው ርዕስ ጉዳዮች ዓይነት /ይዘት/ ሲደለደሉ፣ በጠቅላላ ኮርስ 8 /23 ክሬዲቶች/ 31.08 % በማስተማር ሥነ-ዘዴ 6 /13 ክሬዲቶች/ 17.57 % እንዲሁም ዐቢይ ኮርሶች 14 /በክሬዲት 38/ 51.35 % ይሆናሉ::

ሠንጠረዥ 1 የሊንጓ መርሀ-ገበር ኮርሶች ሥርጭት

| ኮርሶች በተኩረት ነጥብ | ቁጥር | ክሬዲት | % |
|---|---|---|---|
| የጠቅላላ/የጋራ/ዕውቀት ኮርሶች | 8 | 23 | 31.08 |
| የማስተማር ሥነ-ዘዴ/ጠቅላላ/ | 6 | 13 | 17.57 |
| አቢይ/ሙያዊ/ኮርሶች | 14 | 38 | 51.35 |
| ድምር | 28 | 74 | 100 |

በጥናቱ መግቢያ ላይ እንደተገለፀው፣ የጥናቱ ዋና ዓላማ ዐቢይ የአማርኛ ኮርሶችን ይዘት መተንተንና መገምገም በመሆኑ፣ አጠቃላይ ኮርሶችን እና የማስተማር ስነ-ዘዴ ኮርሶችን በተመለከተ በዚህ ጥናት ውስጥ ትኩረት አልተደረገም::

### 4.2.2 የዐቢይ ኮርሶች ስርጭት

ዐቢይ ኮርሶች በቁጥር 14 በክሬዲት 38 መሆናቸውን ከላይ ገልፀናል:: የእነዚህን ኮርሶች ይዘት ለመተንተንና ለመገምገም እንዲረዳንም በዝግጅ ጽሑፎች ቅንት አማካይነት የመመዘኛ መስፈርቶች አውጥተናል:: አቢይ ኮርሶቹን፣ በመስፈርቶቹን መሰረት ስንመድባቸውም ስርጭታቸው የሚከተለውን ይመስላል::

ሀ. <u>የተግባ የቋንቋ ችሎታ መናር</u>

በዚህ ሥር የሚመደቡት የቋንቋ ክሂሎች የሚባሉትን ማዳመጥ፣መናገር፣ ማንበብ፣ መፃፍን የሚያመለክቱ ኮርሶች ናቸው:: ነገር ግን በዚህ ጥናት ውስጥ ከታቀፉት 14 ኮርሶች ውስጥ ከእነዚህ ክሂሎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ወይም እነርሱን ርዕስ ጉዳይ ያደረገ ኮርስ አላጋጠመንም:: ሆኖም፣ ማንበብና መፃፍን ከሌላ ርዕሰ–ጉዳይ ጋር አዛምዶ የያዘ ኮርስ በመኖሩ፣ እርሱን እዚህ እንመድበዋለን:: ይህም ኮርስ፣ በሚከተለው የኮርስ ርዕስ የሚጠራ ነው::

ሂሣዊ ንባብና የዘገባ አፃፃፍ 3ክሬዲት

ለ. <u>የቋንቋን ባሕርያትና የሥነ–ልሣንን ዒና የሚያስገነዝቡ</u>:–

በዚህ ዋና መሥፈርት ሥር የሚካተቱት ኮርሶች የቋንቋን ምንነትና ተፈጥሮአዊ ባሕርይውን የሚያስረዱ የአማርኛን ድምፅ ልሣናት፣ ሥነ–ምዕላዳት፣ ሥነ–መዋቅርና ሥነ፣ አገባብ የሚያስገነዝቡና እንዲሁም በኢትዮጵያ የሚገኙ ቋንቋዎችን ቤተሰቦችና ሥርጭታቸውን የሚያሳዩ ናቸው:: በመርሀ–ገብሩ ውስጥ ለሠልጣኝ ዕጩ መምህራኑ የቀረቡት ኮርሶችም የሚከተሉት ናቸው::

| | | |
|---|---|---|
| የቋንቋ ሥነልሣን መግቢያ | I/II | 3/3 ክሬዲት |
| የአማርኛ ሰዋሰው | I/II | 3/3 ክሬዲት |
| የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ቅኝት | | 3 ክሬዲት |
| | | ድምር 15 ክሬዲት |

ሐ. <u>የቋንቋን አገልግሎት /ጠቀሜታ/ ማስገንዘብ</u>

በዚህ መስፈርት ሥር የሚታቀፉት ኮርሶች ቋንቋ፣ በሥነ–ጸሁፍ፣ በመገናኛ ብዙኃንና በአጠቃላይም በሕብረሰቡ ውስጥ የሚሰጠውን አገልግሎት የሚያስገነዝቡ ናቸው:: ይሁን እንጂ በዐብይ ኮርሶች ዝርዝር ቢጋር ውስጥ ትኩረት የተሰጠው፣ ከቋንቋ አገልግሎቶች አንዱ ገፅታ ለሆነው ለሥነ–ጸሁፍ ብቻ ነው:: ሥነ–ጸሁፍን ጉዳያቸው ያደረጉ ኮርሶችም የሚከተሉት ናቸው::

| | |
|---|---|
| የሥነ-ጽሁፍ መሠረታዊያን | 3 ክሬዲት |
| የአማርኛ ሥነ-ግጥም | 3 ክሬዲት |
| ድራማ /ተውኔት/ | 2 ክሬዲት |
| | 8 ክሬዲት |

ወ. የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የሀሚቆች

አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር እንዲችል ተማሪው በክፍልና በአቀራቢያ ሁለተኛ ደ/ት/ቤቶች የሚደረገውን የማስተማር ልምምድ፣ እንዲሁም በቋንቋ ማስተማር ታሪክ ውስጥ የታዩትን የአፍ መፍቻና የሁለተኛ ቋንቋ ማስተማር ዘዴዎች ዓይነቶችና ባህርያት፣ የሚመለከቱ ኮርሶች በዚህ መሥፈርት ሥር የሚመደቡ ናቸው:: በተጨማሪም፣ አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር በሚደረገ ዝግጅት የትምህርት ዕቅድ አነዳደፍ፣ የማስተማሪያ ማፅሐፍት አዘገጃጀትና መረጣ፣ የመርሃ-ትምህርት ምንነትና ከማስተማሪያ መፅሐፍት ጋር ያለው ዝምድና እና የቋንቋ ማስተማሪያ መሣሪያዎች አጠቃቀም ሁሉ በማስተማር ዘዴ ሥር ሊጠቃለል ይችላል:: በዚህ ረገድ፣ በኮሌጅ ዐበይ የአማርኛ ኮርሶች ቢጋር ውስጥ የሚካተቱት ኮርሶች ተጠቃለዋል::

| | | |
|---|---|---|
| አማርኛን የማስተማር ልዩ ዘዴ | I/II | 3/2 ክሬዲት |
| የማስተማር ዘዴ ሴሚናር | | 2 ክሬዲት |
| | ድምር | 7 ክሬዲት |

ሠ. ተጓዳኝ መስኮችን የሚዳስሱ

በዚህ መሥፈርት ሥር የሚመደቡ ኮርሶች ከላይ ከሀ-ወ ከተገለጹት ርዕሠ-ጉዳዮች ውጪ ሆነው፣ ነገር ግን አማርኛን ለማስተማር ደጋፊ መረጃዎችን ሊሠጡ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ናቸው::

| | | |
|---|---|---|
| የትርጉም መግቢያ | | 2 ክሬዲት |
| የመጀመሪያ ደረጃ ግዕዝ | | 3 ክሬዲት |
| | ድምር | 5 ክሬዲት |

ከፍብለን የተመለከትናቸው 14 /38 ክሬዲቶች/ ዐበይ ኮርሶች በመሰረርተነት ከአወጣናቸው ሰድስት ነጥቦች በአምሥት ሥር ተጠቃለዋል:: በቀረቡበት መልክ ብቻ ሲታዩ፣ የተሟላ የቋንቋ ችሎታ መኖርን የሚያሣይ አንዱ ኮርስ ሲሆን፣ በክሬዲት ሲሰላ 3 ክሬዲት ብቻ ነው /ይህም፣ ኮርስ መሰረር ቀን ሙሉ በሙሉ ያሟላል ለማለት ያዳግታል::/ ኮርሱ ከሥርጭቱ አንፃር በመቶኛ ሲሠላ 7.9 % ይሆናል:: የቋንቋን ባሕርያትና የሥነ-ልሣንን ጫና የሚያስገነዘቡ ኮርሶች በቁጥር 5 ሲሆኑ በክሬዲት ደግሞ 15 ናቸው:: ከአጠቃላይ ስርጭት አንፃር በመቶኛ ሲታሰቡም 39.47 % ያክል ይሆናሉ:: 3 ኮርሶች የቋንቋን አገልግሎት /ጠቀሜታ/ የሚመለከቱ ሲሆኑ፣ በክሬዲት 8 በመቶኛ ሲሠሉ ደግሞ 21.05 ይሆናሉ:: የቋንቋን ማስተማር ዘዴ አስመልክተው የተቀረፁት ኮርሶች በቁጥር 3 በክሬዲት ስባት ሲሆኑ፣ በመቶኛ ሲታሰቡ 18.42 ይሆናሉ:: ተጓዳኝ መስኮችን የሚዳስሱ ኮርሶች በቁጥር 2 በክሬዲት ደግሞ 5 ሲሆኑ በመቶኛ 13.6 የሚሆነውን ስርጭት ይሸፍናሉ::

ሠንጠረዥ 2 የአቢይ ኮርሶች ሥርጭት

| ተራ ቁጥር | መሥፈርት | የኮርሱ ርዕስ | መለያ ቁጥር | ክሬዲት | መቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | የተሟላ የቋንቋ ችሎታ መኖር | 1/ ሂሣዊ ንባብና የዘገባ አፃፃፍ | ኢትሳ 211 | 3 | 7.9 |
| | | ድምር | | 3 | |
| ለ | የቋንቋን ባህሪያትና የሥነ ልሣንን ግና የሚያስገነዝቡ | 1/ የቋንቋና ስነልሣን መግቢያ I/II | ኢትሳ141/142 | 3/3 | |
| | | 2/ የአማርኛ ሰዋሰው I/II | ኢትሳ241/242 | 3/3 | |
| | | 3/ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ቅኝት | ኢትሳ 244 | 3 | 39.47 |
| | | ድምር | | 15 | |
| ሐ | የቋንቋን አገልግሎት/ጠቀሜታ/ ማስገንዘብ | 1/ የሥነ-ፅሁፍ መሠረታዊያን | ኢትሳ 122 | 3 | |
| | | 2/ የአማርኛ ሥነ-ግጥም | ኢትሳ 221 | 3 | |
| | | 3/ ድራማ/ተውኔት/ | ኢትሳ 222 | 2 | 21.05 |
| | | ድምር | | 8 | |
| መ | የቋንቋ ማስተማር ዘዴ፣ [illegible] | 1/ አማርኛን የማስተማር ልዩ ዘዴ I/II | ኢትሳ131/132 | 3/2 | |
| | | 2/ የማስተማር ዘዴ ሴሚናር | ኢትሳ 232 | 2 | 18.42 |
| | | ድምር | | 7 | |
| ሠ | ተጓዳኝ መስኮችን የሚዳስሱ | 1/ የትርጉም መግቢያ | ኢትሳ 212 | 2 | |
| | | 2/ የመጀመሪያ ደረጃ ግዕዝ | ኢትሳ 143 | 3 | 13.6 |
| | | ድምር | | 5 | |
| | | ጠቅላላ ድምር | | | 100 |

## 4.3 የዐቢይ ክርክሮች ይዘት ትንተና

ከዚህ በላይ አቢይ የአማርኛ ክርክሮችን በሚያተኩሩበት ርዕስ–ጉዳይ /የሙያ መስክ/ በመመደብ ስርጭታቸውን አመልክተናል:: ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ይዘታቸውን ለመመርመር እንሞክራለን::

### 4.3.1 የተግባር የቋንቋ ችሎታ መናገር

#### 4.3.1.1 የሰነዱ ትንተና

ለቋንቋ መምህርነት የሚሰለጥን መምህር የሚሰለጥንበትን ቋንቋ ክሂሎች በሚገባ የሚያውቅና በብቃት የሚገለገልባቸው መሆን ይጠበቅበታል:: ቋንቋን ማዳመጥ ሲባል ቢያንስ ሌሎች የሚናገሩትን አዳምጦ ፍሬ ነገሩን ለይቶና አጣርቶ መረዳትን ይጠይቃል:: በተለያዩ ሁኔታዎች፣ ማለትም፣ በእርስ በርስ ንግግር፣ በውይይት፣ በጉባኤ ንግግር፣ በመገናኛ ዘዴዎች /ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን/ በመሣሠሉት ሁሉ የሚነገሩ መልዕክቶችን አዳምጦ መረጃ ለማስቀረት መቻልን ያጠቃልላል/ፍውለር 1965፡ 76/::

መናገር ሲባል ጠቅለል ባለ አነጋገር፣ ሀሣብን፣ በግልጽና በማያሻማ መንገድ በቃሉ ለሌሎች ጠቃል ለማስተላለፍ መቻል ነው:: የንግግር ክሂልን ማዳበርም፣ አድማጭን ሊያዝናኑ /ገር ሊያሰብሉ/ የሚችሉ የሥርዓተ ድምፆችም ሆነ የቃላት አጠቃቀም መዛባት ሣይኖር፣ የቋንቋው ተናጋሪ ሕብረተሰብ በሚገባበት መልክ ሀሣብን ለማስተላለፍ ያስችላል:: /ተክሌ ሸዋዬ፣ 1981/

ማንበብ፣ ከተፃፈ ነገር ላይ መረጃ ለማግኘት የሚያስችል ክሂል ነው:: ይህ ክሂል፣ የተነበበ ጽሁፍ ፍሬ ነገርን መረዳት፣ መገመት፣ ከሌሎች ተመሣሣይ ጉዳዮች ጋር ማመሣከር፣ ብስል ከቀሊል የሆነውን መምረጥ፣ እንዴት? ለምን? ምክንያቱ? እያሉ ጠይቆና አገናዝቦ መገንዘብን በመሠረታዊነት ይይዛል/ዊልያምስ፣ 1984 10-12/::

መፃፍ የፊደላን ቅርፅ በወረቀት ላይ ከማስፈር የላቀ ክሂል ነው:: ይህ ክሂል፣ ሃሣብን አፍልቆ፣ በቀላልና በማያሻማ መንገድ በጽሁፍ አማካይነት መልዕክት የማስተላለፍ ችሎታን ያጠቃልላል:: በሌላ አባባል፣ መፃፍ ስንል

ህብረተሰቡ በሚገለገልበት የቋንቋ አጠቃቀም መሠረት የህፃን አመሠራረትና አደራደርና አቀነባበር፣ እንዲሁም የቃላት አመራረጥና የአገላለጸንም ሥልት አጢርቶ በመጠቀም ህፃኑን፣ ወረኛን ለሌሎች /ለአንባቢያን/ ማስተላለፍን ይይዛል /ፍውለር 1965: 133/::

በዚህ ረገድ ለመምህርነት የሚሰለጥን ዕጩ መምህር ቢያንስ ከሚያስተምራቸው ተማሪዎች የተሻለ ክሂል ሊኖረው ይገባል:: ይህን መገደርደሪያ በማድረግ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሚሰጡት ዐቢይ የአማርኛ ኮርሶች በቋንቋ ክሂል በኩል ያላቸውን ትኩረት እንመለከታለን::

በአበይ ኮርሶች ውስጥ፣ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች በተናጠል ወይም በአጠቃላይ በቀጥታ የሚጠቅስ ወይም የሚያለማምድ ዝርዝር ይዘት አላገኘንም:: ነገር ግን፣ እነዚህ ክሂሎች በሌሎች ኮርሶች ውስጥ ተካምረው/ተናጅተው ቀርበው እንደሆነ በማለት ፍተሻ ተካሂዷል:: በዚህም መሠረት ከንባብና ከጽሕፈት ክሂሎች የተውጣጡ ንዑሳን ክሂሎች ተካምረው በአንድ ኮርስ ውስጥ ተገኝተዋል:: ይህም <u>ሂሣዊ ንባብና የዘገባ አፃፃፍ</u> የተሰኘው ባለሦስት ክሬዲት ኮርስ ሲሆን፣ ዋነኛ ትኩረቱ ስለዘገባ ባሕርይና ቅርጽ፣ ስለዘገባና ምርምር ጉዳዮች፣ መፃሕፍትን አንብቦ በመተንተንና ሂስ በመስጠት እንዲሁም የቃላትን አማራጮችና ፍካሬያዊ ፍቺ ዘይቤያዊ አነጋገሮችን በመረዳት ላይ ነው::

ይህንኑ ዓላማ መሠረት አድርጎ የተዋቀረው ቢጋርም፣ ስለዘገባ መሠረታዊ ባሕርያት፣ ይዘትና ቅርፅ ይዘረዝራል:: የዘገባንና የምርምርን ጉዳዮች ያነሣል:: የምርምርን ባሕርያት፣ ዓይነቶችና ዘዴዎችም ይጠቅሣል:: ከእነዚህ አስከትሎም፣ የሂስ አፃፃፍ መርሆዎች፣ የጥቅስ አቀማመጥ፣ የአማራጮችና ፍካሬያዊ ፍቺዎች አጠቃቀምና ዘይቤያዊ አነጋገሮች ተዘርዝረዋል::

በኮርሱ ቢጋር ውስጥ ከተነሱት እነዚህ ነጥቦች መካከል፣ ዘገባንና ምርምርን አስመልክቶ የተጠቀሱት ዝርዝር ነጥቦች እንዲሁም የሂስ አፃፃፍ መርሆዎችና የጥቅስ አቀማመጥ ህገጋት በቀጥታ በጽሕፈት ክሂል ውስጥ የሚካተቱ ንዑሳን ክሂሎችን የሚመለከቱ ናቸው::

በተጨማሪም፣ በዚሁ ኮርስ ይዘት ዝርዝር ቢጋር ውስጥ ከንባብ ክሂል ውስጥ የሚመደቡ ንዑሳን ክሂሎች ተጠቅሰዋል:: ከእነዚህም፣ አንዱን ጽሑፍ በጥልቀትና በርጋታ አንብቦ መገንዘብ፣ ተገንዝቦም፣ አጠቃላይ የጸሐፊን ቀዝበር፣ የቋንቋውን አጠቃቀም፣ የሀሣቡን ብስለት፣ አንድነትና ተያያዥነት አስመልክቶ በባለሙያ አይን የመገምገምና የመመዘን ችሎታን ለማለማመድ የታቀደ የንባብ ንዑስ ክሂል አስበሉ ማለት ይቻላል::

ከዚህም ሌላ፣ የቃላትን አማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ አጠቃቀምና ዘይቤያዊ ንግግሮችን መረዳት፣ በአንድ ጽሁፍ ውስጥ የሚይዙትን ትርጉም /ፍቺ/ መገንዘብ መቻል ሌላው የዕጩ መምህራኑን የንባብ ክሂል ለማዳበር የቀረበ ንዑስ ክሂል ነው ብሎ መገመት ይቻላል::

ከ <u>ሂሣዊ ንባብና ዘገባ አፃፃፍ</u> ኮርስ በተጨማሪ፣ አማርኛን የማስተማር ልዩ ዘዴ በሚባለው ኮርስ ዓላማና ቢጋር ውስጥ ንባብ እንደ አንድ ንዑስ ርዕስ ቦታ ተሰጥቶታል:: አገላለጹም ከነ-ዝርዝር ነጥቦቹ ቀርቧል/አባሪ4/ ከዚህ ውጭ ግን በማንኛውም ኮርስ አላማም ሆነ ቢጋር ውስጥ፣ የቋንቋ ክሂሎችን አስመልክቶ የቀረበ ይዘት አላጋጠመንም:: ለማስተማር ልዩ ዘዴ በተዘጋጀው ሬትና ውስጥም ስለንባብ የተነሳ ነጥብ የለም::

የማስተማሪያ ዘዴ ሴሚናር ለሚለው ኮርስ ተማሪዎች ከወሰዱት ማስታወሻ ውስጥ ግን በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የቋንቋ ክሂሎች ትምህርት እንዴት እንደ ሚከናወን የሚያመለክት ጥናት ሠርተው እንዲያቀርቡ መጠየቃቸውን ለማግኘት ተችሏል::

የተማሪ የቋንቋ ክሂልን በተመለከተ ከሠነዱ ምርመራው የተገኘው ውጤት ከላይ የቀረበው ሲሆን ይህንኑ ርዕስ ጉዳይ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለመፈለግ ሲባል ለተማሪዎች በቀረበው መጠይቅ ውስጥ ትኩረት ተሰጥቷል:: በመጠይቁ ውስጥም 6 ያህል ጥያቄዎች ቀርበው ነበር:: ለጥያቄዎቹ የተሰጠው ምላሽም ተጠቃሎ ቀርቧል::

### 4.3.1.2 የቋንቋ ክሂሎችን የሚመለከቱ ከመጠይቁ የተገኙ መልሶች ትንተና

በቀረበው መጠይቅ ውስጥ፣ የቋንቋ ክሂሎች በተመጣጠነ ቅንብር መገኘታቸውን ለማወቅ ለ11 ተማሪዎች መጠይቅ ታድሎ፣ ማዳመጥን፣ መናገርንና ማንበብን በተመለከተ ሁሉም ተማሪዎች አስተያየታቸውን ሲሰጡ መጻፍን በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ መልስ ያልሰጠ አንድ ተማሪ አጋጥሟል:: ይሁንና ለእያንዳንዱ ክሂል የተሰጠው ምላሽ አማካይ ነጥብ ሲታይ ለማዳመጥ 3.91 አግኝቷል:: ይህም አሀዝ ተማሪዎቹ በጣም መስማማታቸውን ያመለክታል::

መናገርን በተመለከተ 3.18 በሆነ አማካይ ነጥብ ተማሪዎቹ እስማማለሁ በማለት መልሰዋል:: ማንበብን በተመለከተ የተገኘው ምላሽ በጣም እስማማለሁ የሚል ሲሆን አማካይ ነጥቡም 3.73 ነው:: መጻፍን በተመለከተ ግን መጠይቁ ከተበተነላቸው 11 ተማሪዎች ውስጥ አንዱ መላሽ ምልክት ባለማድረጉ አሥሩ ተማሪዎች የሚሰጡትን ምላሽ ብቻ ስናሰላው 3.5 በሆነ ነጥብ ወደ በጣም እስማማለሁ የተጠጋ ምላሽ አስገኝቷል:: ከዚህ በላይ በቀረበው መግለጫ መሠረት ለጥያቄው የተሰጠው ምላሽ የቋንቋ ክሂሎችን በተመለከተ የተመጣጠነ አቀራረብ አለ ከሚል ማጠቃለያ የሚያደርስ ነው::

በአብይ የአማርኛ ኮርሶች ውስጥ ተገቢው ትኩረት ያልተሰጠው ክሂል ካለ ተብሎ ለቀረበ ጥያቄ ማዳመጥን በተመለከተ 3.64 በሆነ አማካይ ነጥብ በጣም እስማማለሁ የሚል ምላሽ ተገኝቷል:: መናገርን አስመልክተው የሰጡት ምላሽ አማካይ ነጥብ 3.36 በመሆኑ እስማማለሁ ወደሚለው አማራጭ ይጠጋል::

ማንበብ ተገቢው ትኩረት አልተደረገበትም ብለው ምላሽ የሰጡት ደግሞ 3.64 በሆነ አማካይ ነጥብ በጣም እስማማለሁ ወደሚለው መልስ አድልቷል:: ለመጻፍ ክሂል የተሰጠው ምላሽ 3.27 በመሆኑ እስማማለሁ የሚለውን ሀሣብ ያመለክታል::

በቋንቋ ክሂል ላይ ተገቢው ትኩረት ያለመደረጉን በተመለከተ የተገኙት ምላሾች እንደሚያሣዩት ከሆነ ሁሉም በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙ መሆናቸውን ነው::

ይህ ማለት ደግሞ መጀመሪያ የድጋፍ ክህሎትን በተጨባጭ ቅንብር አቀርበውልናል ከሚለው ጋር የሚቃረን ይመስላል:: መጠይቁን የሞሉት መላሾች በሁለቱ ጥያቄዎች መካከል ያለውን ልዩነት ተገንዝበው የመለሱት አይመስልም:: በመጀመሪያው ጥያቄ ላይ የደገፉትን በሌላ ጥያቄ ሲያፈርሱት ታይተዋል::/ሠንጠረዥ 2 ይመልከቱ/

ሠንጠረዥ 3 የድጋፍ ክህሎትን የሚመለከቱ በመጠይቁ የተገኙ መልሶች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 | ያልመለሱ | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በክፍሉ ውስጥ የተማርኳቸው አቢይ የአማርኛ ኮርሶች የሚከተሉትን የድጋፍ ክህሎች በተጨባጭ ቅንብር አቀርበውልናል:: ሀ- ማዳመጥን | 10 | 1 | | | | | 3.91 |
| | ለ- መናገርን | 4 | 5 | 2 | | | | 3.18 |
| | ሐ- ማንበብን | 9 | 1 | 1 | | | | 3.73 |
| | መ- መጻፍን | 8 | 1 | | | 1 | 1 | 3.50 |
| 6 | በአቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ውስጥ ተገቢው ትኩረት ያልተሰጠው ሀ- ማዳመጥ ነው | 7 | 4 | | | | | 3.64 |
| | ለ- መናገር ነው | 6 | 3 | 2 | | | | 3.36 |
| | ሐ- ማንበብ ነው | 8 | 2 | 1 | | | | 3.64 |
| | መ- መጻፍ ነው | 7 | 3 | | | 1 | | 3.27 |
| 13 | በአቢይ ኮርሶች ማጠቃለያ ላይ የሚቀር ብልያ ፈተና የሚያመዝነው ሀ- በምርጫ ጥያቄዎች ላይ ነው | | | 4 | 5 | | 2 | 1.44 |
| | ለ- ባዶ ቦታ በመሙላት ላይ ነው | | 3 | 3 | 3 | | 2 | 2.00 |
| | ሐ- አዛምዶ በመመለስ ላይ ነው | | 3 | 3 | 3 | 1 | 1 | 1.80 |
| | መ- እውነት ውሸት ላይ ነው | 1 | 1 | 3 | 3 | 2 | 1 | 1.60 |
| | ሠ- አጭር የጽሁፍ መልስ በመጠየቅ ላይ ነው | 3 | 6 | 1 | | | 1 | 3.20 |
| | ረ- ሰፋ ያለ ማብራሪያ በመጠየቅ ላይ ነው | 5 | 3 | 2 | 1 | | | 3.09 |
| 14 | በአማርኛ ኮርሶች ሂደት ውስጥ በሬ የጥናት ርዕስ/የሰሚናር ወረቀት/ ተሰጥቶዎት ሰርተው ለመምህርዎ አስረከበው ያውቃሉ? | 2 | 2 | 4 | 1 | 2 | | 2.09 |
| 15 | የሰሯት የሰሚናር ወረቀት ታርሞ ተመልሶልዎታል:: | 1 | 2 | 3 | 2 | 2 | 1 | 1.80 |
| 16 | ወረቀቱ ታርሞ ከተመለሰልዎ አርማቱ የሚያተኩረው ሀ- በፍሬ ነገር ላይ | | 3 | 1 | 2 | 2 | 3 | 1.63 |
| | ለ- የድንጋጌው ቅንብር ጥምር ይታረማል | 2 | 3 | 1 | 1 | 1 | 3 | 2.50 |

ይሁንና ይዘታቸው በተተነተነው ዐበይ ኮርሶች ውስጥ በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆን ማዳመጥን የሚመለከት ትምህርት የተሣበት ቦታ አላጋጠመም:: መናገርም ቢሆን በጨረፍታ ከመነካካት በስተቀር ይህ ነው የሚባል አርእስተ ጉዳይ/ይዘት/ ሆኖ አልተገኘም:: ማንበብና መፃፍን በተመለከተ ግን ሂሣዊ ንባብና የዘገባ አፃፃፍ በተባለው ኮርስ ውስጥ ንባብና ጽሕፈት በከፊል የሚተባበሩባቸው በመሆናቸው እና ማንበብ እንደ አንዱ ንዑስ ርዕስ ሆኖ በአማርኛ የማስተማር ልዩ ዘዴ ውስጥም ስለሚገኝ፣ ከሌሎቹ ጋር ሲነፃፀር የተሻለ አቀርቦት አለው:: ከማለት ያለፈ ደጋፊ ሀሣብ ለመስጠት ያዳግታል:: ከሌሎች መረጃዎች አንፃር ሲታይ የክሂሉ ክፍሎች ተገቢው ትኩረት አልተደረገባቸውም የሚለው ሀሣብ ተቀባይነት ያለው ይመስላል::

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የፅሁፈትን ክሂልም በተመለከተ የጎላ በትምህርትነት መቅረብ አለበት ብሉ ከመጠየቅ አለፈን ተማሪዎች ሀሣባቸውን በጽሁፍ የሚገልጹባቸውንና ፅሁፈትን የሚጠይቁትን ነገሮች በንመረምርስ ብለን ፈተናንና የሰሚስተር ወረቀትን የተመለከቱ ጥያቄዎች አቀርበን ነበር:: ለነዚህ ጥያቄዎችም የተሰጡት መልሶች የሚከተለውን ይመስላሉ::

የጽሕፈትን ክሂል በተመለከተ በቀረቡት ሌሎች ጥያቄዎች ውስጥ የሰሚስተር ወረቀት ተሰጥቶ ለመምህራቸው ማስረከባቸውን የሚመለከት ይገኝበታል:: ለዚህ ጥያቄ ከሰጡት ምላሽ 2.09 በመሆኑ አማካይ ነጥብ በመጠኑ እስማማለሁ ማለታቸውን መረዳት ይቻላል:: የሠራችሁት የሰሚስተር ወረቀት ታርሞ ተመልሶላችኋል ወይ ለሚለው ጥያቄ ምላሽ 1.80 የሆነ አማካይ ነጥብ ተገኝቷል:: ወረቀቱ ታርሞ ከተመለሰልዎት እርማቱ የሚያተኩረው በፍሬ ነገር ላይ ብቻ ነወይ? ለሚለው ጥያቄ የተገኘው መልስ 1.63 አማካይ ነጥብ ነው:: ይህም ከፍሬ ነገርም በላይ እርማቱ ሌሎች ጉዳዮችን እንደሚያካትት ያመለክታል:: በዚሁ ዓይነት እርማቱ የቋንቋውም ቅንብር ጥምር ይመለከታል ለሚለው 2.50 በሆነ አማካይ ነጥብ ምላሽ ተሰጥቶበታል:: ይህም በመጠኑ እስማማለሁ ከሚለው በላይ እስማማለሁ የሚጠጋ ነው::

የሰሚስተርን ወረቀት አስመልክቶ በወጡ ጥያቄዎች የተገኘው ምላሽ የሚጠቀመን አጠቃላይ ግንዛቤ የሰሚስተር ወረቀት በመስጠትና አርሞ በመመለስ በኩል የሚደረገው ጥረት ዝቅተኛ መሆኑን ነው:: ለዚህ ተግባር የተሰጠው ትኩረት መሻሻል ያለበት መሆኑን ለመረዳት ይቻላል:: ተማሪዎቹ ሊማሩ የሚችሉት በሚሠሩት ሥራና ሥራቸውን አስመልክቶ መምህራን ከሚሰጧቸው አርማቶች/ምክር፣ ትችት፣ማስተካከያ ምስጋና.../ በመሆኑ የተማሪዎችን ትጋትና የሚያሳድጉ ተግባራት ሊቀርቡላቸው ይገባል::

በአበይ የአማርኛ ኮርሶች ማጠቃለያ ላይ የሚቀርቡትም የማጠቃለያ ፈተናዎች ትኩረት በምርጫ ጥያቄዎች ላይ ነውን? ለሚለው ጥያቄ 9 ተማሪዎች ብቻ መልስ ሰጥተዋል:: ከዘጠኙ ውስጥ 1.44 በሆነ አማካይ ውጤት በጣም አልስማማም የሚል መልስ ተሰጥቷል:: ባዶ ቦታ መሙላትም 2:00 ብቻ በማግኘት በመጠኑ እስማማለሁ የሚል ምላሽ ቀርቧል:: አዛምዶ መመለስና እውነት ውሸት የሚሉት የፈተና ዓይነቶችን በተመለከተም 1.80 እና 1.60 የሆነ አማካይ ነጥብ በማግኘታቸው ብዙም የማይቀርባቸው ናቸው ማለት ይቻላል:: በዐበይ የአማርኛ ኮርሶች መጨረሻ ላይ የሚቀርቡት የፈተና አይነቶች አጭር የጽሁፍ መልሶችን የሚጠይቁ መሆናቸውን 3.20 በማግኘት የእስማማለሁ ምላሽ ተገኝቷል:: ሰፋ ያሉ ማብራሪያዎች የሚጠይቁም ጥያቄዎች መቀረባቸውን 3.09 ያገኘው እስማማለሁ የሚል መልስ ያረጋግጣል::

የማጠቃለያ ፈተናዎችን አቀራረብ በሚመለከት ከተገኘው ምላሽ የምርጫ ጥያቄዎች አዛምዶ መመለስና እውነት/ውሸትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ብዙም ትኩረት የማይደረግባቸው መሆናቸውን ለመረዳት ይቻላል:: ባዶ ቦታ መሙላት የሚለው አማራጭ ደግሞ በመሀከል ላይ ይገኛል:: አጭር የጽሁፍ መልስና፣ ሰፋ ያለ ማብራሪያን የሚጠይቁ ጥያቄዎች በመጨረሻ ፈተናዎች ውስጥ እንደሚቀርባቸው ከመጠይቁ የተገኘው መረጃ ያመለክታል:: ይህም ምናልባት በተዘዋዋሪ መንገድ የተማሪዎችን የፅሁፈት ክሂል ለማዳበር ያግዝ ይሆናል ብሎ ለመገመት ይረዳ ይሆናል::

### 4.3.2 የቋንቋ ባሕይርይና የሥነ-ልሣን ሚና

#### 4.3.2.1 የስነዱ ትንተና

በተዘማጅ ጽሑፎች ቅኝት ውስጥ የቋንቋን ባሕርይና የሥነ-ልሣንን ሚና መገንዘብ ለቋንቋ መምህር አስፈላጊ መሆኑን/በመረጃ ክፍሎች 2.፩ ላይ/ገልፀን ነበር።

በሕብረተሰቡ ውስጥ ቋንቋን አስመልክተው የሚንፀባረቁ አመለካከቶችና አስተያየቶች ሁሉም ዘመናዊና ትክክለኛ ናቸው ማለት ስለማይቻል፣ ወደ ሥልጠና ተቋም የሚገባ ዕጩ መምህር የህብረተሰብ አካል እንደመሆኑ ስለቋንቋ ምንነትና አገልግሎት ያለው አመለካከት የተዛባ ሊሆን ይችላል። ቀደም ሲል በቁጥር /2.፩ / ጠቅለል ተደርጉ እንደተገለፀው ይህ ቋንቋ ከዚህኛው ጥሩ ነው፣ ይህ መጥፎ ነው፣ ይህ ደስ ይላል፣ ያደገም ደስ አይልም፣ ይህኛው ቋንቋ ቀላል ነው፣ ያኛው ቋንቋ ከባድ ነው ለመማርም ያስቸግራል የሚሉና የመሣሠሉ አመለካከቶችን ሊያንፀባርቁ ይችላል። እነዚህን የመሣሠሉ ግምቶች ለማስወገድና በዘመናዊ የሥነ-ልሣን ሣይንስ የተገኙትን የቋንቋን ተፈጥሮና ባሕርይ የሚያስገነዝቡ መረጃዎችን ለመስጠት የሥነ-ልሣን ዕውቀት ለሰልጣኙ እጩ መምህር መስጠቱ አስፈላጊም፣ ተገቢም ነው /ሻው፣ 1987/።

የሥነ-ልሣን ትምህርት አስፈላጊነቱ ስለቋንቋ ምንነት፣ ተፈጥሮና ባሕርይ ለመረዳት ብቻ ሣይሆን የቋንቋንና የሰው ልጅን ግንኙነት ለማወቅ፣ የቋንቋን መለመኛ እድሜና የአለማመዱን ሁኔታ ለመለየት፣ የቋንቋን ልዩ ልዩ ገጽታዎች /ዘዬዎች የአካባቢ፣ የከተማ፣ የገጠር አማርኛ እንዲሉ/ እንዲሁም የአገልግሎታቸውን መጠን/ሥፋት/ጥበት/ ለመረዳት፣ አንዱ ቋንቋ ከሌላ ቋንቋ ጋር ባለው ግንኙነት የተነሣ የሚጨምረውንና የሚቀንሰውን ጉዳይ ወይም የሚያሣየውን ለውጥ /መወራረስ፣ መዋዋስ፣ መጥፋት/ ለመገንዘብ የሚረዳ ሣይንሣዊ መረጃ በመስጠቱ ነው።

ከእነዚህም ሌላ፣ የስነ ልሣን ትምህርት ስለ ቋንቋው ልዩ ልዩ አካሎች /ድምፅ፣ ምዕላድ፣ ሥነ መዋቅር/ የተፃፉ የምርምር ውጤቶችን ለመቃኘትና ጠንካራና ደካማ ጐናቸውን ለመገንዘብ ይጠቅማል /ዊደውሰን፣ 1991: 74-75/።

የሥነ-ልሣን ትምህርት ለሰው አገልግሎቱ፣ በትምህርትነት የቀረበውን ቋንቋ ለትምህርት በሚያመች መልኩ ለመከፋፈልና፣ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከነጠላ ወደ ውስብስብ፣ ደረጃ በደረጃ ለማዘጋጀት የቋንቋውን ልዩ ልዩ ክፍልፋዮች አስናድቶ በአገልግሎት ደረጃቸውና በሚያሣዩት የመስለየ እርከን ለማዘጋጀትና የሥርዓተ ትምህርቱን ዓላማ ተከትሎ መርሀ-ትምህርት ለመንደፍ እንዲሁም፣ የማስተማሪያ ማፀሕፍት ለማዘጋጀት፣ የትምህርት አርእስተ ጉዳይ ለመምረጥ ሁሉ ይጠቀማል/ ተከፋዩ፣ 1981/፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው የቋንቋ ባሕርይና የሥነ-ልሣን ግና ማበራሪያ መሠረት በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሚሰጡትን የሥነ-ልሣን ኮርሶች ይዘት ሥንመለከት የሚከተለውን ዕውነታ እናገኛለን፡፡

ከጠቅላላ 38 ክሬዲቶች ውስጥ በስነ-ልሣን ምድብ የሚካተቱ 15 ክሬዲቶች እንደሆኑ ከላይ ከቀርጭቱ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ማለት 39.47% በመሆኑ ከሌሎቹ ሲነፃፀር አብዛኛውን እጅ እንደሚይዝ መረዳት ይቻላል፡፡

የኮርሶቹን ዓላማና አነርሱን ተመርኩዞ የተዘጋጀውን ዝርዝር ቢጋር ስንመረምርና የተማሪያቹንም የማስታዘሻ ደብተሮችና የመጨረሻ ፈተናዎች ይዘቶች ስንመለከት በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ የሚሰጠው የሥነ ልሣን ኮርስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

የቋንቋ ታሪክ የቋንቋ ምንነት፣ የቋንቋ ባሕርያት፣ የቋንቋ አገልግሎትና ስለቋንቋ የተሰጡ ልዩ ልዩ አስተያየቶችን በመዘርዘር አስፍሯል፡፡ በቋንቋዎች መካከል የሚደረግ ግንኙነትና ንክኪ የሚያስከትለውን ሁኔታ፣ የቋንቋና የህሣብን የቋንቋንና የህብረተሰብን፣ የቋንቋንና የባሕልን ቁርኝት ለማሣወቀም ታቅዷል፡፡ ቋንቋ በጊዜ ውስጥ እንደሚለወጥና እንዲሁም የቋንቋን አለማመዱና፣ ቋንቋን የመማር ሂደትን አዛምዶ ግንዛቤም ያስጨብጣል/ዝርዝሩን ከአባሪ ይመለከቱ/

አጠቃላይ ከሆነው የቋንቋ ታሪክ፣ ምንነትና ባሕርይ አለፍ ወደ ዝርዝር ጉዳዮች በመግባትም፣ ከሥነ-ድምፅ እስከ ሥነ-ምዕላድ ያሉ የቋንቋ አካላትን ምንነትና ባሕርይ አተቷል፡፡ የድምፆች ምንነት ሲባልም፣ ከንግግር ድምፆች የአናባቢና የተነባቢ ድምፆችን አፈጣጠርና ባሕርይ፣ የሚፈጠሩበትን ቦታና አባላት ልሣናት፣

የሚኖራቸውን ባሕርይ ሁሉ ይመለከታል:: የድምፆችን ሥርዓት በተመለከተም፣ አንድ ድምፅ ከሌላ ድምፅ ጋር ያለውን የሥርዓት ባሕርይ ተነፃፃሪነት ወይም ተለዋዋጭነት አስመልክቶ ነጥቦችን ያነሣል::

በሥነ-ምዕላድ ረገድ የምዕላድን ውሱኑ፣ ባሕርያትና ከቃል ጋር ያላቸውን ተመሣሣሎና ልዩነት አቅፏል:: የምዕላድ አይነቶችን /ነፃና እስር/ የምዕላድ ክፍሎችን /ዘረ-ምዕላድ፣ ንጥረ ምዕላድ/ ጠቅሷል:: በምዕላዶች ውስጥ የሚኖሩ የለውጥና የውህደት አይነቶች ሁሉ አቅርቧል::

በቃላት ረገድም፣ በመነሻ፣ በመካከልና በመድረሻ ላይ ስለሚከሰቱ ቅጥያዎችና አይነቶች ያብራራል:: የቃላትን ርባታ፣ የቅጥያ ምዕላዶችን ድርሻ/ቃል ለዋጭ በማድረግና በማርባት/ ያተታል:: ተማሪዎቹ በንጥረ-ድምፅ እና በንጥረ ምዕላድ አፃፃፍ እየፃፉ ልምምድ እንዲያደርጉ ዕድል ይሰጣል በዓላማውና በቢጋሩ ላይ የቀረቡት ዝርዝር ጉዳዮች በተማሪዎቹ ማስታወሻ ደብተርም ላይ ታይተዋል:: ዋና ዋናዎቹ ሀሳቦችም በፈተናው ውስጥ ተካተዋል::

ከዚህ በላይ የቀረበው ጠቅላላ የሥነ-ልሣን መግቢያ መሠረት በማድረግ የቀረበው ሌላው የሥነ-ልሣን ኮርስ ደግሞ የአማርኛ ሠዋሠው ነው::

በዓላማው ላይ እንደተገለፀው ይህ ኮርስ ትኩረቱ የአማርኛን ሥነ-ድምፅ እና ሆሄ መተንተን፣ የአማርኛን ቃላት መዋቅሮች ማስረዳት አገባባዊና ቃላዊ ክፍሎችንም መለየት ነው:: በዚሁ መሠረት፣ የአማርኛን ሥነ ድምፅና የሆሄ ሥርዓት በክለሣ መልክ አቅርቦ ወደ ቃላት ምሥረታ ይሸጋገራል:: ከዚያም ርባታን፣ ማጣመርንና ቃል መለወጥን፣ እንዲሁም ቃላዊና አገባባዊ ክፍሎችን እንደሚያነሣ በቢጋሩ ላይ ሰፍሯል::

በዓላማውና በቢጋሩ ላይ የቀረቡትን ርዕስ ጉዳዮች በመንተራስ ለተማሪዎቹ የቀረበባቸውን ዝርዝር ይዘት ከማስታወሻ ደብተራቸው ስንመለከት፣ ደግሞ፣ ከሥነ-ድምፅ ጀምሮ ተነባቢና አናባቢን እንዲሁም ሆሄን ከሥነ-ምዕላድ እስከ ሥነ-መዋቅር የሚደርሱ ልዩ ልዩ የአማርኛ ቋንቋ ገጽታዎችን ያነሣል:: የአማርኛን ቋንቋ መዋቅር በማስረዳት ከሌሎች መለየቱን ያመለክታል:: የአማርኛን መዋቅር ከሆሄያት አወቃቀር [illegible]

በማስረዳት ትርጉም የሚሸከሙ ሆሄያትን ሁሉ ይገልፃል፡፡ ቃሉ የሚመሠረትባቸውን መንገዶች ከፋፍሎ ያሣያል፡፡ የፈተናው ይዘት ዋና ዋናዎቹን የሰዋሰው ክፍሎች የሚመለከት ርዕስ ነገሮችን የሚጠይቅ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>በአማርኛ ሰዋሰው ክፍል</u> ውስጥ ደግሞ በአሳማው ላይ የተጠቀሰው የአማርኛን ሀረግ መዋቅር መተንተንና ነጠላና ድርብ ሀረጋትን ለይቶ ማጤንን የሚመለከት ነው፡፡ በኮርሱ ቢጋር ላይ ደግሞ የሀረግ መዋቅር፣ ነጠላ ገባሽ ሐረግ፣ ድርብ ገባሽ ሀረግ፣ ጥገኛ ሀረግ፣ አዛማጅ ሀረጋት / [illegible] ስማዊ ሀረጋት መዋቅርን የሚመለከት ይዘት ለተማሪዎች እንደሚቀርብ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ይኸው በዓላማውና በቢጋሩ ላይ የቀረበው ዝርዝር ይዘት በተማሪዎች ማስታወሻ ደብተር ላይም እንዲሁ የአማርኛን የቃል ክፍሎች ስም፣ ግስ፣ ቅፅል መስተዋድድ... በማለት ያነሣሣል፡፡ በዚህ ውስጥ ቃላት የማገናኛቸውም የአማርኛ ሀረጎች መሠረቶች መሆናቸውን ያስረዳል፡፡ የቃላን ክፍል መወሰኛ መንገዶችንም ያሣያል፡፡ በዓይነታቸውም በስማዊ ሀረግ፣ ግሳዊ ሐረግ፣ ቅጽላዊ ሐረግና መስተዋድዳዊ ሐረግ መሆናቸውን አሳይቷል፡፡ ከአይነታቸው በተጨማሪ ባሕርያቸውም ተተንትኗል፡፡ በሀረግ ውስጥ ያሉት ልዩ ልዩ ክፍሎች /የሀረግ መሪ፣ መሙያ፣ አጎላማሽ/ ሁሉ ተጠቅሰዋል፡፡

ለትምህርቱ በተሰጠው አጋጣሚ ሴሚስተር ፈተና ላይም ከላይ የተጠቀሱት ዋና ዋና ሀሣቦች ቀርበዋል፡፡ ይህም የአማርኛ ሰዋሰው ኮርስ ይዘቶች በትክክል መቅረባቸውን ያመለክታል፡፡

በዚህ ክፍል የተመደበው ሌላው ኮርስ <u>የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ቅኝት</u> ነው፡፡ የዚህ ኮርስ አላማዎች የታሪካዊና ንጽጽራዊ ሥነ-ልሣንን ምንነት በማብራራት፣ በቋንቋ ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ ለውጦችን በማመሳከት፣ ቋንቋን በዓይነትና በዘር ግንድ የመከፋፈያ ዘዴዎች አማካይነት፣ በንጽጽራዊ ዘዴና ቋንቋን መልሶ በማዋቀር መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያል፡፡ የኢትዮጵያን ቋንቋዎች አከፋፈልና ቤተሰባዊ ዝምድናቸውን ያመለክታል፡፡

ይህ ተመርኩዞ የወጣው ዝርዝር ቢጋር የታሪካዊና ንጽጽራዊ ሥነ-ልሣንን ምንነት፣ የቋንቋን ውጫዊና ውስጣዊ ለውጦች፣ የቋንቋን ሥነ-ምድራዊ አከፋፈል፣ የቋንቋን ቤተሰባዊ ክፍፍል፣ የመልሶ ማዋቀር ዘዴ የቋንቋን ምዕላዶች — የመሣሠሉትን ያነሣል፡፡ እንዲሁም በአፍሪካ ቋንቋዎች ላይ የተደረጉ ጥናቶችና አከፋፈ[illegible] ኩሻዊ፣ ላቸውን ይቃኛል፡፡ ከዚያ በኋላ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ኢትዮ ሴማዊ፣ ኢትዮ ኩሻዊ፣

ኦሞአዊ ቋንቋዎችና በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚገኙ አበይ ሷሕራዊ ቋንቋዎች ካነሱ በኋላ ከእያንዳንዱ ቅርንጫፍ ተወካይ ቋንቋዎችን በመውሰድ ገለፃ ያቀርባል ይላል::

ስለዚሁ ኮርስ ከተማሪዎቹ ማስታወሻ የተገኘው መረጃ ደግሞ ቋንቋ ምንድነው ብሎ በመጀመር በሥነ-ልሣን መግቢያ ውስጥ የተነሱትን ሀሳቦች በድጋሚ ያቀርባል:: የቋንቋንና የህብረተሰብን ግንኙነት፣ የቋንቋን አጠቃቀም ገጠር፣ ከተማ፣ የተማረ፣ ያልተማረ፣ ፆታ፣ እድሜ የሥራ ቦታ በማለት ልዩ ልዩ ገፅታዎችን ያስረዳል::

ሥነ-ልሣንን በሁለት በመከፈል አጠቃላይና ውስን /macro and micro/ በማለት ያቀርባል:: ከሥነ-ልሣን ክፍሎች /ዐይነቶች/ ውስጥ ገላጭ ስነ-ልሣንን ታሪካዊ ስነ-ልሣን፣ ንፅፅራዊ ሥነ-ልሣንን፣ በይዘቱ ውስጥ አስገብቷል:: ከዚህ ጋር የቋንቋ ለውጥ የሚመጣባቸውን ምክንያቶች አመልክቷል:: ቋንቋ ከህብረተሰብ ዕድገት ጋር የተያያዙ መሆኑን የኢኮኖሚና የሥርዓተ ማህበር ለውጦችም ተፅእኖ ሊያደርጉበት እንደሚችሉ አብራርቷል::

ይህ ኮርስ በአሁኑ ሲሚስተር የሚሰጥ በመሆኑ በቢጋሩ ውስጥ ተጠቅሰው በተማሪዎች ማስታወሻ ውስጥ ያልተገኙ ጉዳዮች በቀሪው ጊዜያት ይሸፈኑ ይሆናል የሚል ግምት አለን::

የቋንቋንና ሥነ-ልሣንን ባሕርያት የሚመለከቱ አበይት ኮርሶች ይዘት ዓላማቸውን፣ ቢጋራቸውን እንዲሁም የተማሪዎችን ማስታወሻ ደብተሮችና ለኮርሱ የቀረቡ መልመጃዎችን /ፈተናዎችን/ ይዘት በመመርመር ለቋንቋ መምህር ሊቀርብለት የሚገባውን ቋንቋና ሥነ-ልሣን ነክ መረጃ ጠለቅና ሰፋ ካለ ማብራሪያ ጋር የቀረበ መሆኑን ተረድተናል:: ይሁንና ሥነ-ልሣን የቋንቋን ባሕርይ በማስረዳት ብቻ ሳይወሰን በቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ ሌሎች ጉዳዮችንም የሚያጠቃልል በመሆኑ ሥነ-ልሣን ለቋንቋ ማስተማር የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ የሚመለከት ይዘት ቀርቦ እንደሆነ ለማረጋገጥ ለተማሪዎቹ መጠይቅ ቀርቧል:: በተማሪዎች ኳለቶ የተገኘው ምላሽም በሠንጠረዥ 4. ላይ ተጠቃሎ ቀርቧል::

4.3.2.2 የመጠይቅ ትንተና

ሠንጠረዥ 4 ስለስነ-ልሣን ግና ከመጠይቅ የተገኙ መልሶች

| ተ.ቁ. | ጥያቄ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 | ድምሩ | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | በአበይ ኮርሶች አማካይነት ሥነ-ልሣን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሚጠቀሙበትን ግና በሚገባ ተረድቻለሁ፡፡ ሀ- የቋንቋ አጠቃላይ ባህርይ በሚመለከት | 9 | 2 | | | | | 3.82 |
| | ለ- የአማርኛን ድምፀችና ምዕላዶች በሚመለከት | 8 | 2 | 1 | | | | 3.64 |
| | ሐ- የአማርኛን ሰዋስዋዊ መዋቅርን በሚመለከት | 5 | 3 | 2 | 1 | | | 3.09 |
| | መ- ሥነ-ልሣን የማስተማሪያ መሣሪያን ለመምረጥ የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | | 2.82 |
| | ሠ- ሥነ-ልሣን ለመርሀ-ትምህርት /ለነደ ትምህርት/ አዘገጃጀት ያለውን አስተዋፅኦ | 4 | 4 | 2 | 1 | | | 3.00 |

ከሠንጠረዥ እንደምንረዳው የቋንቋ አጠቃላይ ባሕርይ በሚመለከት የቀረበው ጥያቄ ተማሪዎች ሲመልሱ፣ "የቋንቋ አጠቃላይ ባሕርይ በሚመለከት ሥነ-ልሣን የሚጠቀሙበትን ግና በሚገባ መረዳታቸውን" 3.82 በሆነ አማካይ ነጥብ በጣም እንደሚስማሙ ገልፀዋል፡፡

የአማርኛን ድምፀችና ምዕላዶች በሚመለከትም ተገቢ ግንዛቤ ያገኙ መሆኑን 3.64 በሆነ አማካይ ነጥብ በጣም የሚስማሙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የአማርኛን ሰዋስዋዊ መዋቅር የሚመለከተውን ጥያቄ ደግሞ 3.09 በሆነ ውጤት እስማማለሁ ብሉ መልሰዋል፡፡ "ሥነ-ልሣን የማስተማሪያ መሣሪያ ለመምረጥ የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ" አስመልክቶ የተገኘው ምላሽ 2.82 የሆነ አማካይ ውጤት ነው፡፡ "ሥነ ልሣን ለመርሃ ትምህርት አዘገጃጀት ያለውን አስተዋፅኦ" በመረዳት ረገድ ያላቸው ግንዛቤ 3.00 የሆነ አማካይ ውጤት ነው፡፡ ተማሪዎች ለሁሉም የሰጡት ምላሽ የተቀራረበ ሲሆን መስማማታቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

ከላይ በሰነዱ ምርመራ ውስጥ ማለትም በዓላማ፣ በቢጋር፣በተማሪዎቹ ማስታወሻና በማጠቃለያ ፈተናዎች ይዘቶች ውስጥ ስነልሣን የማስተማሪያ መሣሪያነትም ሆነ መርሀ–ትምህርትን ለመምረጥና ለማዘጋጀት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ የሚያመለክት ይዘት አላገኘንም፡፡ ተማሪዎቹ በሞሉት መጠይቅ ደግሞ ተገቢ ገንዛቤ እንዳገኙ ተስማምተዋል፡፡ እዚህ ላይ የተማሪዎቹ መልስ ከምን እንደመነጨ ተጨባጭ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ምናልባት በግል እንዲያነቡ ከታዘዟቸው መጽሐፍት ተረድተው የመለሱት ነው ብሎ መገመት ይቻላል፡፡ ወይም፣ ተማሪዎቹ ሣያገናዝቡ ጥያቄውን መልሰውታል ማለት ይቻላል፡፡

ተማሪዎቹ ከየትም ያገኙት ከየት በእነርሱ መልስ ላይ ተመርኩዞ በቻ የትምህርት ይዘቱ ቀርቧል ለማለት አያስደፍርም፡፡

### 4.3.3 የቋንቋን አገልግሎት/ጠቀሜታ መገንዘብ

#### 4.3.3.1 የሰነዱ ትንተና

ከዝግጅ ጽሁፎች ቅኝት ውስጥ የቋንቋን አገልግሎት መረዳት ለመምህሩ እንደሚጠቅመው ገልፀናል፡፡ በዚሁ መሠረት ሥር ሊካተቱ የሚችሉ አበይ ክርክሮችም ሦስት ናቸው፡፡ እነሱም፣ የሥነ–ጽሁፍ መሠረታዊያን፣ ሥነ–ግጥም እና ተውኔት/ድራማ/ ናቸው፡፡

ዕጩ መምህሩ ከስልጠና በኋላ ሠጥቶ የሚያስተምረውን የቋንቋ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች መገንዘብ ይኖርበታል፡፡ ለምን አገልግሎት እንደሚያውለው የማያውቀውን መሣሪያ የያዘ ሰው ትርፉ ሸክና እንደሚሆን ሁሉ ለቋንቋ መምህርነት የሚሰለጥን ዕጩ መምህርም፣ የሚሰለጥንበትን ቋንቋ አገልግሎት የማያውቅ ከሆነ ትርፉ ድካም ከመሆን አያልፍም፡፡ ሰልጣኙም ሆነ አሰልጣኙ ሁለቱም በከንቱ የሚደክሙ ይሆናሉ፡፡

የቋንቋ ልዩ ልዩ አገልግሎት ስንልም፣ ቋንቋው በህብረተሰቡ ውስጥ ያለው የመግባቢያነት ደረጃ ማለትም፣ ለሥራ ግንኙነት፣ ለትምህርት ለፍርድ ቤት፣ ለመገናኛ ብዙሃን፣ ለሥነ–ጽሁፍ ገልጋሎት መዋል አለመዋሉን የመሣሠሉትን ያጠቃልላል፡፡ ቋንቋው በታሪክ ውስጥ ያለፈባቸውን ሂደቶችና ከዚሁ ጋር ተያይዞም ሥፋትና ጥበቱን፣ በሥነ–ጽሁፍ ቋንቋነቱ የደረሰበትን የዕድገት ደረጃ ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ከዚሁ ባሻገር፣ ለአገሪቱ ህዝቦች [illegible] ደረጃም [illegible] ውስጥ ይገባል፡፡

በዚህ አንፃር፣ ከኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ አበይት የአማርኛ ኮርሶችውስጥ ከላይ የጠቀስናቸው ሦስቱ ኮርሶች /8 ክሬዲት/ ሙሉ ትኩረታቸው በሥነ-ጽሁፍ ምንነትና ዘርፎች ላይ የተመሠረተ ነው::

የየኮርሶቹ ዓላማዎች ውስጥ የተጠቀሱት ዋነኛ የትኩረት ነጥቦች የሥነ-ጽሁፉን ዘርፎች ባጠቃላይና የአማርኛን ሥነ-ጽሁፍ በተለይ የሚመለከቱ ናቸው:: ይህም በመሆኑ የሥነ-ጽሁፍን ዘርፎች መተንተን፣ የረጅምና የአጭር ልቦለድን ተመሣሣይነት ልዩነት ማመልከትን፣ የሥነ-ጽሁፍን ሥራዎች መገምገምን፣ የግጥምን ምንነት፣ አጀማመርና ባህርይ እንዲሁም ቋንቋውን የሚመለከት መረጃ በመስጠት ማስረዳትና በተወሰኑ ግጥሞች ላይ ሂሣዊ ግምገማ ማካሄድን ያጠቃልላሉ:: በተጨማሪም ስለ ተውኔት ጽንሠ ሃሳብና የኢትዮጵያ ባህላዊና ዘመናዊ ተውኔትን መመርመር ከተውኔት ሥራዎች ውስጥ አንዳንዶቹን መተንተንና ተውኔትን ማንበብን የሚሉት የሚተኮርባቸው ናቸው::

ከላይ የተገለጹትን ርዕስ ጉዳዮች መሠረት ከዳረጉት ኮርሶች አንዱ <u>የሥነ-ጽሁፍ መሠረታውያን</u> የተባለው ኮርስ ነው:: በዚህ ኮርስ ዝርዝር ቢጋር ውስጥ፣ ስለ ሥነ-ጽሁፍና ሥነ-ጽሁፍ ጥናት፣ ሥለ ስነ-ጽሁፍ ዋና ዋና ዘርፎች ማለት ሥለ ሥነ-ግጥም፣ ተውኔት፣ አጭርና ረጅም ልቦለድ ምንነትና ባሕርያት ጠቅለል ያለ መግለጫ ይሰጣል:: የአጭር ልቦለድንና የረጅም ልቦለድን የጋራ ባሕርያትም ለመግለጽ ይሞክራል:: በተመረጡ የአማርኛ አጭርና ረጅም ልቦለድ አስመልክቶ ትንታኔ ከተሰጠ በኋላም በተወሰኑ የሥነ-ጽሁፍ ሥራዎች ላይ/አጭርና ረጅም ልቦለድ/ ሂሣዊ ትንተና እንደሚቀርብ ዝርዝር ቢጋሩ ይጠቁማል::

እንዲሁም ሥነ-ግጥም በተሰኘው ኮርስ ቢጋር ውስጥ <u>የሥነ-ግጥም</u> አጀማመርና ክፍሎች እንዲሁም አይነቶችና የሥነ-ግጥምኛ ቋንቋ ይመረምራል:: የሥነ-ግጥም ዋና ዋና አላባውያን ምት፣ /ዜማ/፣ የቤት አመታት፣ ዘይቤያዊ ቋንቋ ተምሣሌታዊነት፣ ቅኔያዊነት ይብራራሉ:: ሥነ-ግጥምን አንብቦ መረዳት፣ በአንዳንድ ግጥሞች ላይ ሂሣዊ ግምገማ ማቅረብና የአገጣጠም ተግባራዊ ትምህርት ማካሄድ እንደሚገባም ያስረዳል::

<u>የድራማ/ ተውኔት</u>/ ኮርስ ቢጋር ዝርዝር ይዘት ስንመለከት ደግሞ ስለ ተውኔት ጠቅላላ መግቢያ ከቀረበ በኋላ የኢትዮጵያን ተውኔት ባሕል ይቃኝና የተውኔትን አላባውያን ይዘረዝራል:: ስለ ተውኔትና ትያትር፣ ስለ ተውኔት አዘገጃጀትና የተውኔት ገበብ ማብራሪያ ይሰጣል:: የኢትዮጵያ ተውኔት ላይ የሚደረግ መለስተኛ ጥናታዊ ጽሑፍም በተግባር እንደሚቀርብ ይገልፃል::

ከላይ በየኮርሱ ዝርዝር ቢጋርና አላማ ላይ የተነሱትን ነጥቦች ለመቃኘት እንደሞከርነው ሁሉ፣ እነዚህ ይዘቶች ለተማሪው መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የተማሪዎችን ማስታወሻ ደብተር ተመለከትናል:: በተማሪዎቹም የማስታወሻ ደብተሮች ውስጥ በየኮርሱ ዝርዝር ቢጋሮች የቀረቡት ይዘቶች ከሞላ ጎደል ተንፀባርቀዋል::

<u>የሥነ-ጽሁፍን መሠረታውያን</u> በተመለከተ ተማሪዎቹ የወሰዷቸው ማስታወሻዎች የሥነ-ጽሑፍን ጠቀሜታና ዘርፎቹን አላባውያኑን፣ በሥነ-ጽሁፍ ውስጥ የቃላትን አጠቃቀም፣ ገፀ-ባሕርያት፣ ጭብጥ፣ የጽሁፍን ዓይነቶች /መዘርዝራዊና ኪነታዊ/ አንፃርን፣ ስለ ትልም፣ ሂስና ድምፀት አካትተዋል:: ስለ ድራማዊ ልቦለድና ገፀ-ባሕርያት፣ ዜና መዋዕል፣ አጭር ልቦለድ፣ ግጥም ተውኔትና ልቦለድ በጥቂቱ አንስተዋል:: በመጨረሻውም ፈተና ላይ እነዚህ ጉዳዮች ከሞላ ጎደል ቀርበዋል::

የአማርኛን ሥነ-ግጥም በተመለከተም በተማሪዎቹ ማስታወሻዎች ውስጥ የሥነ-ግጥም ምንነት ባለምጣኔ ስለመሆኑ፣ ስለ ስሜት ቀስቃሽነቱና በምርጥ ምርጥ ቃላት ምርጥ በሆነ አደራደር የሚቀርብ መሆኑ ተወስቷል:: ሥነ-ግጥም በዜማውና በዘይቤው ቀንበር የተነሣ ተምሳሌታዊነት ያለው ምናባዊ የሆነና አፁረሲነት /ዘለአለማዊነት/ ያለው መሆኑ ተገልፁአል:: ሥነ-ግጥም በምርጥ ቃላትና በዜማ በመፀፉ ስሜትን የሚኮረኩር፣ የሚያብሰለስልና ቀስቃሽ ሥነ-ጽሁፍ ዘርፍ መሆኑ ተብራርቷል:: እንዲሁም ሥነ-ግጥም ሲነሣ አብሮ የሚሄደው ቅኔ ከነአይነቶቹ /ሰምና ወርቅ፣ ኅብርና ምርምር ቅኔ/ ቀርቧል:: በፈተናውም ውስጥ እነዚህ ጉዳዮች ከሞላ ጎደል ተካተዋል::

በተውኔት/ድራማ/ ኮርስ ረገድም፣ የተውኔት ምንነት፣ አቀራረቡና ዓላማው ተገልፁአል:: በተውኔት ውስጥ የሚካተቱ ጥበቦች/አላባውያን/ ተዘርዝረዋል:: የትያትርና የድራማ አንድነትና ልዩነት ተገልፁአል:: ድራማ ከጥንት ከግሪክ የአማልዕክት አከባበርት ጀምሮ ወደ ዘመናችን እንዴት እንደደረሰ የሚያመለክት ይዘት ተገኝቷል:: ዋና ዋና የሆኑት የተውኔት አይነቶች ትራጀዲና ኮመዲ መሆናቸውና፣ ለተውኔት መታያ ተገቢ እስከሆነው የሰዓት ርዝማኔ ድረስ ያሉት ዝርዝር ነጥቦች ተነስተዋል:: ልዩ ልዩ ምሳሌያቸውም ቀርበዋል:: ከዚህ ሌላ ግን ይህ ኮርስ በአሁኑ ሰሚስተር የሚሰጥ በመሆኑ የመጨረሻው ፈተና አልታየም::

## 4.3.2.2 የመጠይቅ ትንተና

ይህንኑ የቋንቋ አገልግሎት በሚመለከት ለተማሪዎች መጠይቅ ቀርቧል:: የቀረበላቸውም ጥያቄ በተ.ቁ.4 የተመለከተው፣ "አብይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ውስጥ የአማርኛን ቋንቋ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ተገንዝቤያለሁ የሚለው ነው፣ በሥሩ ለተዘረዘሩት ዝርዝሮች ተማሪዎች መልስ ሰጥተዋል /ሰንጠረዥ 5/ የሥነ-ጽሁፍን ዘርፎችና አገልግሎት በመረዳት በኩል የተማሪዎቹ መልስ 3.82 በሆነ አማካይ ውጤት በጣም እስማማለሁ ሲሉ መልሰዋል:: በመገናኛ ብዙሃን በኩል ያለውን የቋንቋውን አገልግሎት በመረዳት በኩልም በቂ ግንዛቤ እንዳገኙ 3.4 አማካይ ነጥብ ተስማምተዋል:: የአማርኛ ቋንቋ በህብረተሰቡ ውስጥ ስለሚሰጠው የመግባቢያ አገልግሎት ደግሞ 3.00 በሆነ አማካይ ነጥብ እስማማለሁ ሲሉ መልሰዋል::

ሠንጠረዥ 5 የአማርኛ ቋንቋ ልዩ ልዩ አገልግሎት

| ተ.ቁ. | ጥያቄ | 4 | 3 | 2 | 0 | 1 | ያልመለሱ | አማካይ /ሚን/ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | ለአብይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ውስጥ የአማርኛን ቋንቋ ልዩ ልዩ አገልግሎት ተገንዝቢያለሁ | | | | | | | |
| | ሀ- በሥነ-ጽሁፍ ዘርፎች | 9 | 2 | | | | | 3.82 |
| | ለ- በመገናኛ ብዙሃን | 6 | 2 | 2 | | | 1 | 3.40 |
| | ሐ- በህብረተሰቡ ውስጥ ስሚሰጠው የመግባቢያ አገልግሎት ረገድ | 5 | 4 | | 1 | 1 | | 3.00 |

በኮሌጅ የሚሰጠው የሥነ-ጽሑፍ ኮርስ ሥለ ሥነ-ጽሑፍ ዘርፎችና ባሕርያቸው የሚያቀርበው ይዘት ይኑር እንጂ በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ምን እንደሆነ የሚጠቁም ነገር/አማርኛን ማስተማር ልዩ ዘዴ ላይ ከመነሳቱ በስተቀር/ ከዋናዎቹ የሥነ-ጽሁፍ ኮርሶች ዓላማ ጋር በሚያመች መልኩ ተጠምሮ አልተገኘም::

ሥነ-ጽሁፍ በቋንቋ ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎቹን የመማር ፍላጎት በመቀስቀስ፣ የቋንቋውን ባሕላዊ ዓራ በማስገንዘብ፣ ቋንቋን ለመለመድ በመገፋፋት፣ የተማሪዎችን ግንዛቤ በማሳደግ እንዲሁም የማስተንተን ችሎታቸውን በማዳበርና በአጠቃላይም የተሟላ ሰብዕን በመገንባት ረገድ አገዝ ያደርጋል፣ በማለት የሥነ-ጽሁፍንና የቋንቋን [illegible] ማስተማር [illegible] የሚመለከተው [illegible] /1995 [illegible]::

አስገንዘበዋል፡፡ ከርተርና ሉንግ /1991/ የተካሉ ባለሙያዎቻቸው ሥነ-ጽሁፍ ቅኝቶች የቋንቋና ገሃዊ መሻሻልን የሚያስገኝ ዋና ነው ሲሉ አበራር ተውታል፣፡

በኮተኬ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሚሰጠው የሥነ-ጽሁፍ ኮርስ ስለ ሥነ-ጽሁፍ ዘርፎችና ባሕርያቸው የሚያስገነዝቡ ይዘቶች ይኑሩ እንጂ ሥነ-ጽሁፍ በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚያበርከታቸው ሳዛር /1993/ ካርተርና ሉንግ /1991/ ያነሷቸውን ጥቅሞች የሚያመለክቱ ዓላማዎች አለተነደፉበትም፡፡

በይዘቶችም ውስጥ የተነሱት ነጥቦች ሥነ-ጽሁፍን የሚያመለክቱ ቢሆኑም፣ ሥነ-ጽሁፍ ቋንቋን በማስተማር ረገድ በገለጽ የሚያነሳቸው ጉዳዮች ባለመኖራቸው ሰልጣኙ መምህር በማስተማር ሙያ ሊሰማራ እንዴት እንደሚገለገልባቸው ለመገንዘብ የሚያዳግተው ይመስላል፡፡

### 4.3.4 አማርኛ ቋንቋን የማስተማር ዘዴ

#### 4.3.4.1 የሰነድ ትንተና

የቋንቋ ትምህርት ራሱን የቻለ ትምህርት በመሆኑ የራሱ የሆኑ ባሕርያት አሉት፡፡ እነዚያ ባሕርያቱ በትምህርት አሠጣጥ ዘዴው ላይ ይንፀባረቁና ለየት ያለ አቀራረብን ይጠይቃሉ፡፡

የአማርኛን ቋንቋ የማስተማር ዘዴዎች ስንመለከትም ቋንቋ በአገሪቱ ውስጥ በአፍ መፍቻነት የሚናገሩትና የሚማሩት አሉ፡፡ በሁለተኛ ቋንቋነትም የሚናገሩትና የሚማሩት አሉ፡፡ ስለዚህም ሁለቱን አይነት ተማሪዎች የማስተማር ሥልቶችና ዘዴዎች የተለያዩ ናቸው፡፡

ከዚህ አንፃር በኮተኬ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሚሰጠው ዐቢይ የአማርኛ ኮርሶች አካል የሆነው የአማርኛን የማስተማር ልዩ ዘዴ I እና II እና የማስተማር ዘዴ ሴሚናርን ስንመለከት በየአላማቸውም ሆነ በየቢጋሮቻቸው ውስጥ ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳቦች ጋር የሚዛመዱ ይዘቶችን እናገኛለን፡፡

ኮርሶቹ የአማርኛ ትምህርት ዓላማዎችን መንደፍ፣ ስለ ቋንቋ መለመድና መማር- ያሉ ልዩ ልዩ ንድፈ ሃሳቦችን መረዳትን፣ በተማሪዎች መካከል ስላለሉ ገሃዊ ልዩነቶች ግንዛቤ መጨበጥን፣ ለተወ■ኑ ሁኔታ የሚስማማ የማስተማሪያ ዘዴ መቀየስን፣ በአማርኛ ትምህርት ሂደት የንባብን ሚና ማሳለየት፣ የዐቅድን አነዳደፍና የማስተማሪያ መሣሪያ ና ዝግጅትን ያጠቃልላሉ፡፡ በገጠር የማስተማር ልምምድና በአቅራቢያ ት/ቤቶች መደበኛ [illegible] የማስተማር ልምምድ ማድረግን፣ የፈተናዎችን አይነትና አዘገጃጀትን የሚያመለክቱ ይዘቶች

ተነስተዋል:: የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ሥርዓተ ትምህርትንና የማስተማሪያ መጻሕፍትን መገምገም፣ የቀኒት ትምህርት ዝግጅትና በማስተማር መማር ሂደት ላይ ጥናታዊ ጽሁፍ ማቅረብ የሚሉት ናቸው::

እነዚህ ዓላማዎች መሠረት በማድረግ የተዘጋጀው ቢጋር ያቀረባቸው ዝርዝር ይዘቶች ከአላማው ጋር የተሣሰሉ ናቸው/ለዝርዝሩ አባሪ / በአላማዎቹ በቢጋሩ በተመሣሣይ ሁኔታ የታየውን ይዘት ከተማሪዎቹ ደብተር ስንቃኝ ደግሞ የሚከተለውን እናገኛለን:: የቋንቋንና መለመዱና መማር ምንነት፣ ከመጠየቅ ጀምሮ በመማርና በማስተማር ጊዜ የሚከናወኑ ነገሮችን፣ የቋንቋ ችሎታን አስፈላጊነትንና መለኪያዎችን፣ ስለአገርኛ ቋንቋ አስፈላጊነት፣ በቋንቋ አለማመድ ንድፈ ሀሣብ አካባቢ ያሉ ጉዳዮችን ያነሣል:: በተጨማሪም አካባቢ ለህፃናት የሚሰጠው አገልግሎት፣ የቋንቋ መማርና ማስተማር አጠቃላይ ባሕርይ፣ ቋንቋን የመማር ገብና የቋንቋ ችሎታን የተለያዩ ሁኔታዎች መጠቀም መቻል፣ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች፣ የሁለተኛ ቋንቋና ዕድሜ፣ የመርሀ ትምህርት ዓይነቶችና በያይነታቸውን ቀርበዋል::

ከእነዚህ በተጨማሪም እላይ እንደታየው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የንባብ አገልግሎት ከነዝርዝር ነጥቦቹ ቀርቧል:: ሥነ-ጽሁፍንም ለቋንቋ ማስተማር እንዴት እንጠቀምበታለን በሚል መነሻነት ሥነ-ጽሁፍ ቋንቋን በማስተማር ረገድ ለልዩ ልዩ አገልግሎት እንደሚውል ጠቃሚ ፍሬ ነገር ተገኝቷል:: የዐለት ትምህርት ዝግጅት፣ የንዑስ ማስተማር ልምምድ፣ ሁለተኛ ዙር የማስተማር ልምምድ ተከናውኗል:: በዚህ ልምምድ ወቅት ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ በንድፈ ሀሣብ ደረጃ የተገነዘቧቸውን የትምህርት ይዘቶች በድርጊት ለመለማመድ ዕድል እንዲያገኙ ረድቷል:: /መጠይቅ ሰንጠረዥ 6 ላይም ይኸው ሀሣብ ተደግፏል::/

ከተማሪዎች ደብተር የተገኘው ሌላው የትምህርት ይዘት ደግሞ ተማሪዎቹ በመማሪያ መጽሐፉ፣ በሥርዓተ ትምህርቱና በተወሰኑ ክፍሎች ላይ የአራቱን የቋንቋ ክሂሎች የትምህርት አሰጣጥ በተመለከተ ጥናት እንደሚያደርጉ ይጠቁማል:: በተጨማሪም ንግግርን መማር፣ማስተማር፣ የንግግር አስፈላጊነትና፣ አንድን ምንባብ አንብቦ ለመረዳት የሚያገለግሉ ሥልቶችና የተመለከተ ጥናት እንደሚያካሄዱ የሚጠቁም ይዘት አለ:: የተማሪዎቹ ጥናት በጥቅሉ ሲታይ የሚያተኩረው በሥርዓተ ትምህርቱ፣ በማስተማሪያ [illegible] የመማር ማስተማር ሂደትና [illegible] መከተል እንዳለባቸው በሚመለከት ላይ ነው:: ዓሬ ግን የኮርሱ ዋና አላማ ቋንቋን

የማስተማር ዘዴን ማስተማር ሆኖ ሳለ፣ የቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴዎች በማስገንዘብ ላይ ብቻ አተኩሯል:: ማዳመጥን መናገርን ማንበብንና መፃፍን መማርና ማስተማርን የሚመለከት ጉዳይ በቢጋሩም ሆነ በተማሪዎች ማስታወሻዎች ውስጥ አላገጠመም::

ሲዋር በማስተማር ዘዴዎች በሚለው ኮርስ ቢጋር ውስጥ ከዓላማው ጋር ግንኙነትና ቀጥተኛ ዝምድና የሌለው "የስብሰባ አመራር መርሆዎች" የሚል ርዕስ ጉዳይ ይገኛል:: ይህ ርዕስ ጉዳይ ስምን በቢጋሩ ውስጥ እንደገባ የሚያመለክት ምክንያታዊ መነሻ በአላማው ውስጥ አልተገኘም:: እንዲህ ያለውን ግንኙነት የሌለውን ነገር ማውስ ወገዱ አለበለዚያም ለጠቃሚነቱ ማረጋገጫ የሚሆን መነሻ በሚገባ ማቅረብ ተገቢ ይሆናል::

4.3.4.2 ከመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ቋንቋን በማስተማር የሚሰለጥን ዕጩ መምህር የሚሰለጥንበትን ቋንቋ እንዴት እንደሚያስተምረው የሚያመሳክተው ብልሃት ሊቀርብለት እንደሚገባ ቀደም ሲል አትተናል:: በዚሁ መሠረት በዐቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ውስጥ የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የሚመለከት ይዘት መቅረቡን አመልክተናል:: ይህንኑ ተማሪው/ሰልጣኙ/ አካል እንዴት እንደሚመለከተው መጠይቅ ቀርቦለታል:: መጠይቁ ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች በዝርዝር እናያቸዋለን::

በመጠይቁ ተ.ቁ.2 የቀረበው ጥያቄ፣ "በዐቢይ ኮርሶች ይዘት ውስጥ የሚከተሉት የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር በቂ ልምምድ አገኝቻለሁ" ይላል:: ዝርዝሮቹም ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ ናቸው:: የተሰጡት ምላሾችም በዚሁ ቀደም ተከተል 3.64፣ 3.18፣3.64፣3.27 በሆነ አማካይ ውጤት የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር በቂ ልምምድ መገኘቱን ለመረዳት ተችሏል:: ቀደም ሲል የቋንቋን ክሂሎች አቀራረብና ስርጭት በተመለከተ ባቀረብነው ትንታኔ ውስጥ የቋንቋ ክሂሎች በተሟላ መልኩ እንዳልቀረቡ አይተናል:: ይሁንና እዚህ ደግሞ ክሂሎችን ለማስተማር በቂ ልምምድ አገኝተናል የሚል ምላሽ ተገኝቷል:: መሠረታዊ ከሆነው የሰነዱ ምርመራ ውስጥ በቂ ትኩረት ያልተደረገበትን የቋንቋ ክሂል ለማስተማር በቂ ልምምድ አገኝተናል ብሎ ማሰብ መሠረታዊ መነሻ የሌለው ከመሆኑም ሌላ መላሾቹ ለጥያቄው ተገቢ ትኩረት አላደረጉበትም ወይም አላገናዘቡም ወደ ማለት ያደርሳል::ይህንንም ሀሳብ /አለመገንዘባቸውን/ ለከፍት ጥያቄዎች/17,18,19/ የሰጧቸው መልሶች ያስረዳሉ የጥያቄዎቹ ትንታኔ በዚሁ ምዕራፍ ማጠቃለያ ላይ ይገኛል::

በተራ ቁጥር 5 ላይ የቀረበው ሌላው ጥያቄ ደግሞ በዐበይ የአማርኛ ክፍሎች ይዘት ውስጥ አማርኛን የማስተማሪያ ዘዴን ተረድቻለሁ የሚል አጠቃላይ ጥያቄ ሲሆን ዝርዝሮቹ የተገኙትም ምላሾች የሚከተሉት ናቸው:: በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለመቆጣጠር ለሚለው 3.27፣ በአማርኛ እና የሬ ቀተገና ያለፈ ቀትን በተለያየ ዘዴ ለማስተማር ለሚለው 3.50፣ በተማሪዎች መካከል የሚኖር ግላዊ ልዩነቶችን ለማገናዘብ የሚያበቃ ዘዴ አገኝቻለሁ ለሚለው ደግሞ 3.27 በሆነ አማካይ ውጤት እስማማለሁ የሚል መልስ አግኝተዋል::

በማስተማር ልምዱ ወቅት/ጥያቄ ቁ.7/ የአበይ ክፍሎችን አስተዋፅኦ በተመለከ 6 ያህል ነጥቦች ቀርበው ነበር:: በእነዚህ ነጥቦች ማለትም የዕለት ትምህርት ለማዘጋጀት ለሚለው 3.82 በጣም እስማማለሁ የሚል አማካይ ውጤት ተገኝቷል:: የትምህርት ይዘትን በመምረጥ 3.45፣ ከማስተማሪያ መጽሐፉ ጋር በመተዋወቅ ረገድ 3.27፣ ከመርሀ ትምህርት ጋር በመተዋወቅ፣ 3.45 የክፍል ውስጥ የተማሪ አስተማሪን ቱክቦ በማስገንዘ ረገድ 3.27 እንዲሁም በመለመጃ/ፈተና አዘገጃጀት 3.00 በሆኑ አማካይ ነጥቦች እስ ማማለሁ የሚሉ መልሶች ተገኝተዋል::

ሠንጠረዥ 6 <u>የቋንቋ ማስተማርዘዴን የሚመለከት ከመጠይቅ የተገኙ</u>

<u>መልሶች</u>

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 | ያልመለሱ | አማካይ /ሚን/ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | በዐበይ ኮርሶች ይዘት ውስጥ የሚከተሉትን የቋንቋ ክሂሎች ለማስተማር በቂ ልምምድና ዝግጅት አገኝቻለሁ:: | | | | | | | |
| | ሀ- ማዳመጥን ለማስተማር | 7 | 4 | | | | | 3.64 |
| | ለ- መናገርን ለማስተማር | 6 | 3 | 2 | | | | 3.18 |
| | ሐ- ማንበብን ለማስተማር | 8 | 2 | 1 | | | | 3.64 |
| | መ- መጻፍን ለማስተማር | 7 | 3 | | | 1 | | 3.27 |
| 5 | በአበይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ውስጥ አማርኛን የማስተማሪያ ዘዴ ተረድቻለሁ | | | | | | | |
| | ሀ- በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደትን ለመቆጣጠር የሚያስችለኝን ሥልት አውቄያለሁ | 7 | 3 | | | 1 | | 3.27 |
| | ለ- በአማርኛ አፍ የፊቶትንና ያለፊቶትን በተለያዩ ዘዴ ለማስተማር የሚጠቅም ሥልት ተገንዝቤያለሁ | 5 | 5 | | | | | 3.36 |
| | ሐ- በተማሪዎች መካከል የሚኖረውን ግለሰባዊ ልዩነት ለማገናዘብ የሚያስችለኝን ዘዴ አገኝቻለሁ | 4 | 6 | 1 | | | | 3.27 |
| 7 | በአቀራረቢያ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የማስተማሪ ልምምዴ ወቅት የአበይ ኮርሶች አስተዋፅዖ ከፍተኛ ነበር | | | | | | | |
| | ሀ- የዕለት ትምህርት በማዘጋጀት ረገድ | 9 | 2 | | | | | 3.82 |
| | ለ- የትምህርት ይዘትን በመምረጥ ረገድ | 7 | 3 | 1 | | | | 3.45 |
| | ሐ- ከማስተማሪያ መጽሐፍት ጋር በመተዋወቅ ረገድ | 6 | 3 | 1 | 1 | | | 3.27 |
| | መ- ከመርሀ-ትምህርት ጋር በመተዋወቅ ረገድ | 6 | 4 | 1 | | | | 3.45 |
| | ሠ- የክፍል ውስጥ የተማሪ አስተማሪን ተራክቦ በመገንዘብ ረገድ | 5 | 4 | 2 | | | | 3.27 |
| | ረ- ፈተና/መለመኛ/በማዘጋጀት ረገድ | 6 | 2 | 1 | 1 | 1 | | 3.00 |
| 8 | በማስተማር ልምምዴ ወቅት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ለማሟላት የአበይ ኮርሶች ይዘት ረድቷል | | | | | | | |
| | ሀ- የዕለት ትምህርት ርዕስ ጉዳይን በመምረጥ | 8 | 3 | | | | | 3.73 |
| | ለ- ለክፍል ውስጥ ሥነ-ሥርዓት አጠባበቅ | 5 | 3 | 1 | 1 | 1 | | 2.91 |
| | ሐ- ከተማሪዎች የሚነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ | 9 | 1 | | | | | 3.64 |
| | መ- የተማሪዎችን ፍላጎት ለመረዳት | 3 | 6 | 1 | | | | 3.00 |
| | ሠ- የተማሪዎችን ችሎታ ለመለየት | 3 | 6 | 1 | | | | 3.00 |

በ8ኛ ተራ ቁጥር ላይ የቀረበው ሌላው በቋንቋ ማስተማር ዘዴ ውስጥ የሚገ ተተው ነበር፣ "በማስተማር ለዋዋጭ ወቅት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ለማሟላት የአቢይ ክርሶች ይዘት ረድቷል"፡፡ የሚለው ነው፡፡ ሁኔታዎም ሲዘረዘር፣ የዕለት ተዕለት ርትን ርዕስ ጉዳይ በመምረጥ ረገድ በሚለው 3.73 በሆነ አማካይ ነጥብ በጣም እስማማለሁ ሲሉ የክፍል ውስጥ ሥነ-ሥርዓት አጠባበቅን ደግሞ 2.91 በሆነ አማካይ ነጥብ እስማማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ ከተማሪዎቹ የሚነሱ ጥያቄዎችን በመመለስ ደግሞ የአቢይ ክርሶች ይዘት በጣም የረዳቸው መሆኑን 3.64 በሆነ አማካይ ነጥብ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የተማሪዎችን ፍላጎትና ችሎታ ለማመለከት የአቢይ ክርሶች ይዘት ረድቷል ያሉት ከሰጡት ምላሽ የተገኘው አማካይ ነጥብ 3.00 ሲሆን ይህም መስማማ ታቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

የቋንቋን ማስተማር ዘዴ በተመለከተ ከየክርሶቹ ዓላማዎች ቢጋሮችና ከተማሪዎቹ ማስታወሻ እንዲሁም የመጨረሻ ፈተናዎች ይዘት ላይ ቋርመን ያገኘናቸውን የትምህርት ይዘቶች ከመጠይቁ ውጤት ስናመሳክረው የተሟላ የቋንቋ ክሂልና ፈተናን ማዘጋጀት ከሚለው በስተቀር በአጅጉ የተጣጣመ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

4.3.5 <u>ቋንቋን መፈተን</u>

4.3.5.1 <u>የስነዱ ትንተና</u>

የክፍል ውስጥ የማስተማር ክንውን ፈተና/መለመኝ የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ሀሪስንን/1983/ ጠቅሰን ቀደም ሲል አስገንዝበናል፡፡ ፈተና ደረጃን ለመወሰን፣ ችሎታን ለመረዳት፣ በትምህርት ሂደት ውስጥ ገንዘቤ ያገኘውንና ያላገኘውን ፍሬ ነገር ለመለየት እና ከመዛሥሉት ጉዳዮች ማጠሪያነትና ያለፈ ሥራን ገምገሞ የወደፊትን የትምህርት ሂደት ለማቀድ የሚያስችል መሣሪያ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት በአቢይ የአማርኛ ክርሶች ይዘት ውስጥ ይህንኑ አገልግሎቱን ለዕጩ መምህራን በማሣወቅ ረገድ የተሰጠው ቦታ ካለ መመርመሩ አስፈላጊ በመሆኑ በጥናታችን ውስጥ ከታቀፉት የ14 ክርሶች ይዘት ምርመራ ውስጥ እንዲ አድርገን ወስደነዋል፡፡

የፈተና አዘገጃጀትና አቀራረብ በ14ቱ ዐቢይ የአማርኛ ክርሶች ውስጥ በዋናነት ተነስቶ ዓላማ ተነድፎለት ይዘት ተመርጦለትና ቢጋር ተዘጋጅቶለት አልተገኘም፡፡ ነገር ግን አማርኛን <u>የማስተማር ልዩ ዘዴ</u> ክርስ ውስጥ "የተለያዩ ፈተናዎችና መለመኛዎችን ማዘጋጀት" በሚል ንዑስ ርዕስነት በዓላማውና በቢጋሩ ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ሆኖም፣ ይህ ንዑስ ርዕስ በምን በምን ጉዳዮች ላይ የቋንቋ ፈተና ዓላማ፣ ማዳ·ነቀጥይዘት ላይ እንደሚያተኩሩ፣ [illegible] ዘዴ [illegible] በተማሪዎቹ ማስታወሻ ውስጥ እንደሌሎቹ ንዑሳን ርዕሶች ትኩረት ተሰጥቶት አልተገኘም፡፡

### 4.3.5.2 የመጠይቅ ትንተና

ቋንቋን የመፈተን ጉዳይ በዐበይ ኮርሶች ውስጥ መገኘት አለመገኘቱን ተጨማሪ መረጃ በተደገፈ ውሳኔ ላይ ለመድረስ እንዲቻል ለተማሪዎች በቀረበው መጠይቅ ውስጥ የሚረጋገጡ ጥያቄዎች ተካተዋል፡፡ የተገኙ ምላሾችም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ሠንጠረዥ 7 የቋንቋ ፈተናን የሚመለከቱ ከመጠይቅ የተገኙ መልሶች

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 | ያልመለሱ | /አማካይ ዉጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | በአበይ የአማርኛ ኮርሶች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ለማዘጋጀት የሚያስችል ልምድ ተካትቷል<br>ሀ- በክፍል ውስጥ ቋንቋን የመፈተን ዓላማ በመረዳት ረገድ | 1 | 8 | 1 | 1 | | | 2.82 |
| | ለ- በቋንቋ ፈተና ውስጥ የሚካተቱ የቋንቋ ፈተና ይዘቶች በመምረጥ ረገድ | 3 | 5 | 2 | | 1 | | 2.82 |
| | ሐ- ልዩ ልዩ የቋንቋ ፈተና ዓይነት ዓይነቶች መኖራቸውን በመገንዘብ ረገድ | 3 | 4 | 2 | 1 | 1 | | 2.64 |
| | መ- የቋንቋ ፈተና ለመማር ማስተማሩ ሂደት የሚያበረክተውን አስተዋፅዖ በመረዳት ረገድ | 5 | 3 | 2 | | 1 | | 3.00 |

በመጠይቁ 10ኛ ጥያቄ፣ "በዐበይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ውስጥ የአማርኛ ፈተና ለማዘጋጀት የሚያስችል ልምምድ ተካቷል" የሚል ዝርዝር ነጥቦችን የያዘ መሪ ዐ.ነገር ቀርቧል፡፡ በዝርዝር ነጥብነት የሚያተኩርባቸውም ጉዳዮችና ተማሪዎች የሰጡትም ምላሽ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ "በክፍል ውስጥ የመፈተን ዓላማን በመለከት ረገድ" እንዲሁም፣ በቋንቋ ፈተና ውስጥ የሚካተቱ የቋንቋ ፈተና ይዘቶችን በመምረጥ ረገድ፣ "በአበይ ኮርሶች ልምምድ በሚመለከት ለሁለቱም ጥያቄዎች ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ 2.82 በሆነ አማካይ ነጥብ ነው፡፡ ልዩ ልዩ የቋንቋ ፈተና ዓይነቶችን

ወኖራቸውን በመገንዘብ ረገድ ለሚለው 2.64 የሆነ አማካይ ነጥብ ሲገኝ፣ የቋንቋ ፈተና ለመማር ማስተማር ሂደት የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ በመረዳት ረገድ የሚለው ደግሞ 3.00 አማካይ ነጥብ በማግኘት እስማማለሁ የሚል ውጤት አስገኝቷል::

ከነዚህ የተማሪዎቹ ምላሾች የምንረዳው የማጠቃለያ ግንዛቤ ቋንቋን የመፈተን ዓላማና ዝርዝር አቀራረቡ ሁሉ በክፍል ትምህርት ውስጥ ተካቷል የሚል ነው:: ይሁንና በአንድ ኮርስ ንዑስ ርዕስነቱና፣ ንዑስ ቢጋር አካልነቱ የተገኘ መሆኑንና በተማሪዎቹ ማስታወሻና በመጨረሻ ፈተናዎች ውስጥ ደግሞ አለመገኘቱን ተመልክተናል:: በተማሪዎቹ ማስታወሻ ውስጥ ሳይገኝ እንዴት ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት ዓላማውንና ልዩ ልዩ አገልግሎቱን ተምረናል ሊሉ ቻሉ? የሚል ጥያቄ ሊያስነሣ ይችላል:: ነገር ግን፣ ከአማርኛ ዐበይ ኮርሶች ትኩረቶች ውጭ ባሉ በጠቅላላ ኮርሶች ውስጥ፣ "/Measurement and Evaluation/ የሚል ከፈተና አዘገጃጀት፣ አቀራረብና አስተራረም ጋር ቀጥተኛ ዝምድና ያለው ኮርስ በመኖሩ ምናልባት ተማሪዎቹ በዚህ ኮርስ ውስጥ ከጨበጡት ክሂልና እውቀት በማዛመድ መልሰው ይሆናል በማለት አርቆ መገመት ይቻላል::

4.3.6 ተጓዳኝ መስኮች

4.3.6.1 የሰነዱ ትንተና

ተጓዳኝ መስኮች የምንላቸው ሰልጣኝ ዐጩ መምህሩ በቋንቋ ማስተማር ሂደት ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ልዩ ልዩ ቋንቋ ነክና ማህበራዊ ችግሮችን መፍታት እንዲችል የሚያዘጋጁትን የትምህርት መስኮች ነው:: እነዚህም የትምህርት መስኮች ለአማርኛ ቋንቋ መምህርነት የሚሰለጥን ዐጩ መምህር የሕብረተሰቡን ቋንቋ ነክ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉትን ንድፈ ሀሣባዊ መረጃዎችን የሚጠቁሙ ኮርሶችን የሚመለከቱ ናቸው:: በዚህም ሥር ምርምርን ጉዳያቸው ያደረጉ ኮርሶችንና እንደማህበራዊ ሥነ-ልሣን ያሉትን ኮርሶች ማሰብ ይቻላል እንዲሁም የቋንቋ ማስተማሪያ መሣሪያን ለመምረጥ የመነሻ ሀሣብ የሚያስገኙና የመማር ማስተማርን ሂደት የሚያነሱ ጠቃሚ መረጃዎች /ሠነዶች/ በአማርኛ ተጽፈው ስለማይገኙ መምህሩ ትርጉም ለመጠቀም ይችል ዘንድ የሚረዳውን የትርጉም ትምህርት ያካትታል::

የአማርኛ ቋንቋ ከግዐዝ ቋንቋ ጋር ባለው ታሪካዊ ዝምድና የተነሣ በርካታ ቃላትን እና ሀረጋትን ከግዐዝ ተውሶ ሲሠራባቸው መቆየቱና ለአዲስ አሳቦች መግለጫ ከግዐዝ ቃላት እየተዋሰ ሲጠቀም መኖሩ የታወቀ ነው:: ስለዚህም መምህሩ

በአማርኛ ውስጥ የሚገኙ የግዕዝ ቃላትንና ሀረጋትን መዋቅርና አገነባብ፣ ሥነ-ድምፃዊና ሥነ-ምዕላዳዊ ባሕርያትና ርባታዎች ጠንቅቆ ያውቅ ዘንድ የግዕዝን አበይት ባሕርያት በሥልጠናው ወቅት ማጥናትና መገንዘብ ይበጀዋል የሚል እምነት አለ::

ከዚህ በላይ በቀረበው መንደርደሪያ ተነስተን ወደ አበይ ኮርሶች ይዘት ገጸታ ስንመጣ ለአማርኛ ትምህርት ደጋፊ ሁኔታዎችን ሊያመቻቹ የሚችሉ ሁለት ኮርሶችን እናገኛለን:: እነርሱም፣ <u>የትርጉም ትምህርት መግቢያ</u> እና <u>የመጀመሪያ ደረጃ ግዕዝ</u> ናቸው::

እነዚህ ኮርሶች በተናጠል ሲታዩ፣ በግዕዝ ኮርስ ዓላማ ውስጥ የግዕዝን ግሶች ማርባት፣ ቃላትን መመሥረት፣ የግዕዝን ሰዋሰዋዊ ክፍሎች/ምድቦች/ መተንተን፣ ዐ. ነገሮችን ማዋቀር፣ የግዕዝን ጽሁፍ አገባብ መረዳት፣ ከግዕዝ ወደ አማርኛ መተርጐምን የሚያመለክቱ ርዕስ ጉዳዮች ቀርበዋል::

እነዚህ ርዕስ ጉዳዮች፣ የግዕዝን ተውላጠ ሥሞችንና፣ የአማርኛን ሙያዊ ቃላት ችግሮች በማቃለል ረገድ የግዕዝ ሚና ከሚሉ ሁለት ተጨማሪ ርዕሶች በስተቀር በዓላማው ውስጥ ከቀረቡት መልክ እጅግም ሳይለዩ በቢጋሩ ውስጥ ሰፍረዋል:: በተማሪዎቹ ማስታወሻም ላይ ተውላጠ ሥሞች፣ የግሥ እርባታዎችና የመተርጐም ጥያቄዎች ቀርበዋል::

የግዕዝ ግሥ ርባታ አካሄድ ለአማርኛም ግሥ እርባታ መሠረታዊ መነሻ እንደሚሰጥ የሚያመለክቱ ጠቃሚ መረጃዎች ግን አልተገኙም:: የአማርኛን ሙያዊ ቃላት ችግርም ለመፍታት ግዕዝ እንዴት እንደሚያግዝ የሚያመለክት ፍንጭ በተማሪዎቹ ማስታወሻ ላይ አልተገኘም:: ፈተናውም ቢሆን በቃላት ርባታና በትርጉም ሥራ ላይ ብቻ የሚያተኩር ነው::

ትርጉምን የሚመለከተው የትርጉም መግቢያ የተባለው ኮርስ በውስጡ የያዛቸው ዓላማዎች፣ የትርጉምን ጽንሠ ሃሣብና አስፈላጊነት መረዳት፣ በትርጉም ሥራ የሚከሰቱ ዋና ዋና ችግሮችን መፍታት፣ መሠረታዊ የአተረጓጐም ብልሃቶችን በሥራ ላይ ማዋል እና ጽሑፎችን ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ መተርጐም የሚሉ ናቸው::

በግምገማው ውስጥ የተጠቀሱት እነዚህ ጉዳዮች በቢጋራም ውስጥ በተዋረድ መንገድ ተዘርዝረዋል:: በጥናቱ መግቢያ ውስጥ እንደተገለጸው ይህ ኮርስ የሚሰጠው በዚህ በያዝነው ሲሚስተር በመሆኑ ከተማሪዎች ማስታወሻ ያገኘነው መረጃ እስከ ግንቦት ወር የመጀመሪያ ሣምንት የተማሩትን ብቻ የሚመለከት ነው:: በተገኘው መረጃ መሠረትም፣ ከትርጉም ምንነት ጀምሮ እስከ ቴርጓሚ ችግሮች ድረስ ያሉት ይዘቶች በተማሪዎች የማስታወሻ ደብተሮች ውስጥ ተካተዋል/አባሪ ይመልከቱ/

የትርጉምን ኮርስ ይዘት በተመለከተ ሲሚስተሩ ባለማለቁና የመጨረሻም ፈተና ባለመሰጠቱ ይህ ተሰርቷል፣ ይህ አልተሠራም ለማለት እንዲህ ቢሆን የተሻለ ነበር የሚል የማበረታቻ ሀሣብ ለመሠንዘር አልተቻለም::

4.3.6.2 <u>የመጠይቁ ትንተና</u>

ከተማሪዎች አስተያየት ለመሰብሰብ ሲታቀድ ተጓዳኝ መስኮችን የሚመለከት ጥያቄ ቀርቦ ነበር::

ሠንጠረዥ 8 <u>ተጓዳኝ መስኮችን የሚመለከቱ ከመጠይቁ የተገኙ መልሶች</u>

| ተ.ቁ. | ጥያቄ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 | ያልመለሱ | አማካይ /ሚን/ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | ዐቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማር አጋዥ /ደጋፊ/ የሆኑ መረጃዎችን በመጠቀም ረገድ ተገቢ ትኩረት ሰጥቷል:: ሀ– በምርምር በኩል | 4 | 5 | 1 | | | 1 | 3.3 |
| | ለ– ትርጉምና አገልግሎቱን | 1 | 5 | 1 | 2 | 2 | | 2.9 |
| | ሐ– ግዕዝና ለአማርኛ የሚሰጠውን ድጋፍ | 3 | 1 | 4 | 1 | 2 | | 2.18 |

ጥያቄውም በዐቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ውስጥ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማር አጋዥ/ደጋፊ/ የሆኑ መረጃዎችን በመጠቀም ረገድ ተገቢ ትኩረት ተሰጥቷል? የሚል ነበር:: በዚህ ጥያቄ ሥርም ምርምርን፣ ግዕዝንና ትርጉምን የሚመለከቱ ዝርዝሮች ተካተዋል:: ለእነዚህ ዝርዝሮች በተማሪዎች የተሰጠው ምላሽ፣ ምርምር በአማካይ ነጥብ 3.3 እስማማለሁ የሚለውን ድጋፍ ሲያገኝ፣ ትርጉምና አገልግሎቱ እና ግዕዝ ለአማርኛ የሚሰጠው ድጋፍ የሚሉት በቅደም ተከተል 2.9 እና 2.18 [illegible] አማካይ

ነጥቦች በመጠኑ አስማማለሁ የሚለውን ሀሣብ ያመለክታሉ:: ይህም ደጋፍም ሆነ ተቃውሞው እኩል መሆኑን ያመለክታል::

የትርጉም ክርስ ባለመጠናቀቁ የሚኖረን የማጠቃለያ ሀሣብ ባይኖርም፣ የግዕዝ ክርስ ግን እንደሚጠበቀው ወይም በአሳማኙና በቢጋሪ ውስጥ እንደቀረበው ለተማሪዎቹ አለመድረሱ፣ ከማስታወሻ ደብተራቸው ይዘት ውስጥ አለመገኘቱ ቀደም ሲል በትንታኔው ውስጥ ያሰፈርነውን ይዘን አሁን በመጠኑ አስማማለሁ ከሚለው መልስ ጋር ስናስተያየው የትምህርቱ ይዘት በተገቢው መንገድ አልቀረበም ወደሚል አስተያየት ይመራናል::

ከግዕዝና ከትርጉም ትምህርት ይልቅ ምርምር የተሻለ ትኩረት የተደረገበት መሆኑን ከመጠይቁ የተገኘው 3.3 የሆነው አማካይ ነጥብ ያመለክተናል:: በክርሶች ይዘት ውስጥ ምርምርን በቀጥታ የሚያነሳ ክርስ አልተገኘም:: ይሁንና ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ ደግሞ ከዚሁ የተለየ ነው:: ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ ምንአልባት በ<u>ሂሳዊ ንባብና በዘገባ አፃፃፍ</u> ክርስ ውስጥ የቀረቡትን የምርምር መሠረታዊ ባሀርያት፣ ዓይነቶችና ዘዴዎች የሚሉትን ርዕስ ጉዳዮች ተንተርሰው <u>በማስተማር ዘዴ ዎች ስሚናር</u> ውስጥ የምርምር ዘዴዎችና መርሆዎች እንዲሁም ዓይነቶች ከለሰ ውስጥ የሚነሱትን ነጥቦች ይዘው ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለ::

## 4.4 <u>አበይ ክርሶችን በጠቅላለው የሚመለከቱ ከመጠይቁ የተገኙ መልሶች ትንተና</u>

### 4.4.1 <u>የጥያቄ 9 እና 12 መልሶች ትንተና</u>

በተ.ቁ. 9 ላይ የቀረበው ጥያቄ በዐበይ የአማርኛ ክርሶች ይዘት ውስጥ ተገቢው ትኩረት ያልተደረገባቸውን ርዕስ ነገሮች የሚያመለክት ነው:: የተዘረዘሩት ርዕስ ጉዳዮች የቋንቋው ክሂል፣ የሥነ-ጽሁፍ ክፍል፣ የሥነ-ልሣን ክፍል፣ የሥነ-ዘዴ ክፍል እና የቋንቋ ፈተና አዘገጃጀት የሚሉ ናቸው:: ከቋንቋ ፈተና አዘገጃጀት በስተቀር አራቱ ለእየአንዳንዳቸው የተሰጠው መልስ ከአማካይ ተጠጋግቶ ሲታይ 2.00 አካባቢ ላይ የሚያርፍ ነው:: ይህ አማካይ ውጤት ደግሞ ድጋፍም ሆነ ነቀፋን አያመለክትም:: ለቋንቋ ፈተና የተሰጠው ምላሽ ግን 2.5 በመሆኑ አስማማለሁ ወደሚለው ሀሣብ ስለሚሄድ ፈተና ተገቢ ትኩረት እንዳልተደረገበት መገመት ይቻላል::

በዚህ አጠቃላይ ርዕስ ነገርን በሚመለከት ጥያቄ አማካይነት የተገኘው ገንዘቢ ቀደም ሲል ተማሪዎቹ የቋንቋን ፈተና ለማዘጋጀት ተገቢ ልምድ ተገኝቷል በለው የተከማመበትን ጉዳይ እዚህ ያፈረሱት ይመስላል:: ፍሬ ነገሩ ግን ከዋናው ክርሶች ዓላማና ዝርዝር ይዘት ትንታኔ ጋር ሲነፃፀር ከቀደመው የእሁኑ ቋንቋን የመፈተን ጉዳይ ተገቢ ትኩረት አለተደረገበትም የሚለው የሚታመን ይመስላል::

በአጠቃላይ በዐቢይ የአማርኛ ክርሶች ይዘት ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች ያተኮሩት በየትኛው ላይ ነው ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ በአማካይ ነጥብ ሲታይ በቋንቋ ክሂል ላይ 3.09 በሥነ ልሣን ላይ 3.36 በሥነ-ዘዴ ላይ 2.73፣ በተጓዳኝ /ደጋፊ/ መስኮች ላይ 1.64፣ በሥነ-ጽሁፍ ክርሶች ላይ 3.45 እና በሁሉም ላይ የተመጣጠነ ትኩረት ያደርጋል ለሚለው 2.64 የሆነ ምላሽ ተገኝቷል:: ከእነዚህ ውስጥ ተጓዳኝ /ደጋፊ/ መስኮች ዝቅተኛ ትኩረት የተደረገበት መሆኑ መመለከት ይቻላል::

ቀደም ብለን በ4.2.1. ላይ የክርሶችን ሥርጭት ስንመለከት በአበይ ክርሶች ይዘት ውስጥ ሥነ-ልሣን ከፍተኛውን፣ ክሂል ዝቅተኛውን ፈተና ደግሞ ከነጭራሹ በክርስነት የሌለ መሆኑን አይተናል:: ከክሂል ክርስ ይልቅ በተጓዳኝ መስኮች ውስጥ የተመደቡ ሁለት ክርሶች አገኝተናል:: ይህን ይዘን በሰንጠረዥ የተገኘውን የመጠይቅ ምላሽ ስንመለከት መልሶች የሚጋጩ ሆነው ታይተዋል::

ሠንጠረዥ 9 <u>አጠቃላይ አቢይ ይዘቶችን የተመለከተ ከመጠይቅ የተገኙ መልሶች</u>

| ተ. ቁ. | ጥያቄ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 | ያልመለሱ | አማካይ /ሚን/ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | በአቢይ የአማርኛ ክርሶች ይዘት ውስጥ ተገቢው ትኩረት ያልተደረገበት | | | | | | | |
| | ሀ- የቋንቋ ክሂል ነው | 4 | 1 | 1 | 3 | 1 | 1 | 2.4 |
| | ለ- የሥነ-ጽሁፍ ክፍል ነው | 2 | 3 | 3 | 1 | 1 | 1 | 2.4 |
| | ሐ- የሥነ-ልሣን ክፍል ነው | 3 | 1 | 3 | 3 | 1 | | 2.1 |
| | መ- የሥነ ዘዴ ክፍል ነው | 2 | 1 | 3 | 3 | 1 | 1 | 2.0 |
| | ሠ- የቋንቋ ፈተና አዘገጃጀት | 3 | 3 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2.5 |
| 12 | በአጠቃላይ በዐቢይ የአማርኛ ክርሶች ይዘት ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች ያተኮሩት | | | | | | | |
| | ሀ- በቋንቋ ክሂል ላይ ነው | 3 | 6 | 2 | | | | 3.0 |
| | ለ- በሥነ-ልሣን ላይ ነው | 5 | 5 | 1 | | | | 3.3 |
| | ሐ- በሥነ-ዘዴ ላይ ነው | 2 | 6 | 2 | | | 1 | 2.7 |

| ተ.ቁ. | ጥያቄ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 | ያልመለሱ | አማካ /ሚን/ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 12 | ሠ- በተጓዳኝና ደጋፊ መስኮች ላይ ነው | 1 | 2 | 3 | 2 | 2 | 1 | 1.6 |
| | ሠ- በሥነ-ጽሑፍ ክርክች ላይ ነው | 5 | 6 | | | | | 3.4 |
| | ረ- በሁሉም ላይ የተመጣጠነ ትኩረት ያደርጋሉ | 4 | 2 | 3 | 1 | 1 | | 2.6 |

በስነጹ ትንተና ውስጥ ተገቢ ትኩረት ያልተደረገበት የክሂል ክፍል መሆኑ ታትቷል:: የሬተና አዘገጃጀትንም በተመለከተ ትኩረት ያለመደረጉን አመልክተናል:: የሥነ-ልሣን ክፍል ደግሞ ከሁሉም የበለጠ የተቀረበት መሆኑ ታይቷል:: በዚህ ለፀናው ጥያቄ በተሰጠው መልስ ገን ከሬተና አዘገጃጀት በስተቀር ሌሎቹ በተሟሟይ ገንዘቢ ውስጥ ማረፋቸውን ማለትም ከሀ-መ የተዘረዘረት ሁሉ በመጠኑ እስማማለሁ ወደሚል በተጠጋ አማካይ ነጥብ ተመልከተዋል::

ለጥያቄ 12 የተሰጠውን ምላሽ አጠቃለን ስንመለከተው አሁንም ከስነጹ ምርመራውና ከክርክች ሥርጭት ጋር ተቃርኖ አለው። በሠነጹ ምርመራ ውስጥ ሥነ-ልሣንና ሥነ-ጽሁፍ በተከታታይ ደረጃ መገኘታቸውን አይተናል:: እዚህም በነጥብ ሲታዩ ሥነ-ጽሁፍ 3.45 ቀድሞ ሥነ-ልሣን በ3-36 ተከተሉ ይገኛል:: የቋንቋ ክሂል ገን በስነጹ ምርመራ ውስጥ በዝቀተኛ ደረጃ ላይ ሊገኝ ከመጠይቁ በተገኘው ምላሽ ደግሞ 3.09 በማገኘት በ3ኛነት ደረጃ ላይ ይገኛል::

ከዚህ በላይ የቀረቡትን ትንታኔዎች ስንመለከት በመጠይቁ ውስጥ የተሰጡት መልሶች ምንጭ ከክርክቹ ይዘት የመነጨ አይመስልም:: አለበለዚያም መላሾቹ ተገቢ ገንዘቢ ሳይኖራቸው የሞሉት/የሰጡት/ ምላሽ ይመስላል::

## 4.4.2 የከፍተ ጥያቄዎ 17,18,19 መልሶች ትንተና

ዐበይ ክርክችን በተመለከተ የቀረቡ ክፍል ጥያቄዎች ተማሪዎች ነፀ አስተያየታቸውን እንዲያሰፍሩ ሦስት ጥያቄዎች ቀርበው ነበር ጥያቄ 17,18,19:: ለእነዚህ ጥያቄዎች የተሰጡትን መልሶች ከዚህ ቀጥለን አጠቃለን አቀርበናቸዋል:: ጥያቄ 17፡ በዐበይ የአማርኛ ክርክች ይዘት ውስጥ ለአማርኛ ማስተማር አያገለግልም የሚሉት የትምህርት ይዘት ካሉ ከነምክንያቱ ይግለጹ ለሚለው ጥያቄ የተገኘው የተማሪ ያቹ ምለሽ [illegible]

የተርጓም ትምህርት

- በተሟላ ሁኔታ አይሰጥም
- ምንም ገንዘብ አላጨበጥንም
- በአብዛኛው ስለአመጣጡ፣ ስለዘዴውና ስልቀ አይነገረንም።
  ዝም ብሎ ተርጉሙ በቻ
- እና ከምናስተምረው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጋር አይገናኝም

ግዕዝ ክርስ

- ለምን እንደሚያገለግል አላገባኝም

ለ17ኛው ጥያቄ የተሰጡት መልሶች ማዕከላዊ ዝንባሌ በትንተናችን ውስጥ፣ ለአብይ ክርሶች ደጋፊ ናቸው፣ በተለይ አማርኛን ለማስተማር አጋዥ መረጃ ይሰጣሉ ያሉናቸውን ሁለት ክርሶች ይመለከታል። ሚስማማት አለመስማማታቸውን በሚጠይቀው ጥያቄ 12 ላይ ተጢቃን /ደጋፊ/ ክርሶች በዝቀተኛ ደረጃ እንደሚገኙ አይተናል። ሁለቱን ስናገናዝብ ተመሣሣይነት እንዳሳቸው እንረዳለን።

ለ17ኛው ጥያቄ ከተሰጡት አስተያየቶች ለመረዳት እንደሚቻለው፣ በክርሶቹ ላይ ተማሪዎቹ ያደረባቸው ቅሬታ ከአቀራረብ ጉድለት ይመስላል። ምክንያቱም "በተሟላ ሁኔታ አይሰጥም" እና "በአብዛኛው ስለ አመጣጡ፣ ስለዘዴውና ሥልቀ አይነገረንም፣ ዝም ብሎ ተርጉሙ ብቻ ነው።" የሚሉት አስተያየቶች የአቀራረብ ድክመት እንዳለ ይጠቁሙ ይመስለናል።

ጥያቄ 18 "ከአበይ የአማርኛ ክርሶች ውስጥ የበለጠ ይሰፋፋ የሚሉት ካለ ከነምክንያቱ ይግለጹ" ለሚለው ተማሪዎቹ የሰጡት ምሳሌ:-

"ሥነ–ጽሁፍ ይሰፋፋ

- ለበለጼ ለማንበብና ለመፃፍ
- የቋንቋ ጠቀሜታ ስላለው

– የአማርኛ ቋንቋ ሠዋሠው
– ሥነ–ልሣን
– ግዕዝ
– ሁሉም ክርሶች ይሰፋፋ
– "አድቫንስድ ክምፖዚሽን" ይሰጥ:

የሚሉትን ይይዛል:: መልሶቹ ሁሉንም ክርሶች የሚመለከቱ አስተያየቶች የያዙ ቢሆንም፣ የድርሠት ትምህርት ይጨመር የሚል አስተያየት በመገኘቱ በጽሑፍ ከሄሉ በኩል የጐደለ መሠረታዊ ነገር መኖሩን ለመረዳት ይቻላል::

ጥያቄ 19 ዐቢይ የአማርኛ ክርሶች ይዘትን በሚመለከት የሚስነዘሩት ሀሣብ ካለ ያብራሩ /በመጠይቁ ከቀረቡት ጥያቄዎች ውጭ/ የሚል ሲሆን የተሰጡት ምላሾች ሲጠቃለሉ የሚከተሉትን ነጥቦች አስገኝተዋል::

ሀ– ረጅምና አጭር ልቦለዶ ራሳቸውን ችለው እንደክርስ ይሰጡ

- ከጋራ/ከመን/ ክርሶች ይልቅ አቢይ ክርሶች በጥልቀት ቢሰጡን
- ሥነ–ልሳን ከአጠቃላይ ይልቅ ትኩረቱን በአማርኛ ላይ ያድርግ
- ሰዋሰው በበለጠ በሁሉም ሴሚስተር በሩ በሉ ይሰጥ
- የሥነ–ልሳን ትምህርት I/II ወደ አንድ ሴሚስተር ተጠቃሉ ይሰጥ:: ምክንያቱም በዙ ጊዜ ተምረነው ወጥተን ለተማሪዎች የምንናገረው የለም:: እሱ ተቀንሶ አዲስ ትምህርት ይጨመር::
- በአማርኛ ሰዋሰው I ላይ ትኩረት ይሰጥ::
- የአማርኛ ሰዋሰው II ሰፋባለ መልኩ ይቀጥል::

ለ– የግዕዝ ትምህርት ከአሰጣጡ ጉድለት በተጨማሪ የማገናዘቢያ መጽሐፍ ችግር ስላለበት ይሻሻል::

- የግዕዝ ማስተማሪያ ዘዴ ይቀየር
- ድራማ አስፈላጊ ሆኖ ሳለ የትምህርቱ አሰጣጥ ደካማ ነው
- ትርጉም አስፈላጊ ነው ግን አሰጣጡ ደካማ ነው::

ሐ– • የማተርያል ድጋፍ ይምጣልን–በበለጠ ለማስተዋልና ለማገናዘብ እንድንችል
- የግዕዝ ትምህርት የማገናዘቢያ ችግር ስላለበት ይሻሻል

በአጠቃላይ፣ ከላይ በሠንጠረዥ ግራ መደቡን የተመለከትናቸው ለጥያቄ 19 የተሰጡ መልሶች ናቸው:: ለመልሶቹ በለና በሐ የፊደል ተራ አንፃር የተቀመጡት አስተያየቶች ጉዳያችን ከሆነው የይዘት ተንተና ጋር ዝምድና የላቸውም:: በ"ለ" የፊደል ተራ ረድፍ የተጠቀሱት አስተያየቶች ^መቅለላ^ ሥነ–ዘዴን የሚመለከቱ ሲሆኑ፣ በፊደል ተራ "ሐ" አንፃር የተጠቀሱት ደግሞ የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚያግዙ ተጓዳኝ ጉዳዮች ላይ የተነዘሩ አስተያየቶች ናቸው:: ከእነዚህ ውስጥ በ[illegible] የሆር [illegible] [illegible]ጠቀሱት ግን፣ ከዐቢይ ክርሶች ይዘ[illegible] ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ስላላቸው ከበነዱ ተንተና ውስጥ ከተገኙት ሀሳቦች ጋር የሚጣጣሙ ናቸው::

## ምዕራፍ አምስት

### 5. ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሔ ሀሳቦች

#### 5.1. ማጠቃለያ

በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሚገኘው መርሀ ግብር የሚሰጡትን አቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ከኮሌጁ መምህራንን የማሰለጠን ዓላማ አንፃር በማስተያየት መተንተንና መመዘን የዚህ ጥናት ዓላማ መሆኑ ቀደም ሲል የተገለፀ ነው፡፡ ይህንኑ ዓላማ ከግብ ለማድረስ በተደረገው ጥረትና በይዘት ትንተና የምርምር ሥልት የተደረሰባቸው የትንታኔ ውጤቶች እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

ለቋንቋ መምህርነት የሚሰለጥኑ ዕጩ መምህራን ያስተምሩታል ተብሎ የሚሰለጥኑትን ቋንቋ በተሟላ መልኩ አጥርተው ማወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ችሎታቸውም ከሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ችሎታ የበለጠ ሆኖ መገኘት አለበት፡፡ ስለዚህም ለዕጩ መምህራኑ በአራቱም የቋንቋ ክሂሎች የተሟላ ችሎታ የሚያስጨብጡ ኮርሶች በሥልጠናው ወቅት ሊቀርቡላቸው ይገባል፡፡ በሂሳዊ ንባብና የዘገባ አፃፃፍ ኮርስ ውስጥ ከቀረቡት ከንባብና ከጽሁፈት ንዑሳን ክፍሎች በስተቀር የቋንቋ ክሂሎችን በተመለከተ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሚገኘው መርሀ ግብር ተሳታፊ ለሆኑ ሰልጣኞች፣ አቢይ የአማርኛ ኮርሶች የቋንቋ ክሂሎችን በተሟላ ሁኔታ የሚያስጨብጡ ይዘቶችን አቀናጅተው አለመያዛቸው በይዘት ትንተናው ተረጋግጧል፡፡

የሥነ-ልሣንን ዕውቀት በተመለከተ ተማሪዎች ስለቋንቋ ተፈጥሮና ባህርይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ይዘቶች ቀርበዋል፡፡ በዚሁ ክፍል የሚታቀፈው የአማርኛ ሰዋሰው ኮርስ፣ ከአማርኛ ሥርዓተ ድምፅ እስከ ሥርዓተ አገባብ ድረስ ያሉትን ዝርዝሮች አሟልቶ መያዙን በሰነዶችና በመጠይቅ ትንታኔ ውስጥ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሌላ መልኩ ግን ሥነ-ልሣን ቋንቋን በማስተማር በኩል የሚያበረክተው አስተዋፅኦ በአቢይ ኮርሶች ይዘት ውስጥ አልተጠቀመም፡፡ የቋንቋ ትምህርትን ይዘት በመምረጥ፣ በማቀናበርና በማዘጋጀት ረገድ፣ በማስተማሪያ መሣሪያ መረጣ

ረገድ የሚኖረውን አስተዋፅኦ የሚያስገነዝብ ጠቋሚ ነጥቦች በአቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ውስጥ አልተገኙም::

የቋንቋ አገልግሎት ከሚገለጽባቸው ድርጊቶች ውስጥ አንዱ ሥነ-ጽሑፍ ነው:: በአቢይ ኮርሶች ይዘት ውስጥ ይኸው ጉዳይ ተነስቶ ይገኛል:: የሥነ-ጽሑፍን ምንነትና ዘርፎቹን የሚያስረዱ ነጥቦች በየኮርሶቹ ይዘቶች ውስጥ ተዘርዝረዋል:: ይሁንና ሥነ-ጽሑፍ በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ያለውን ጠቀሜታ የሚያስገነዝብ ውል ያለው መግለጫ አልቀረበም::

ከሥነ-ጽሑፍ በስተቀር በአቢይ ኮርሶች ዓላማና ቢጋር እንዲሁም የተማሪዎች ማስታወሻዎችና ፈተናዎች ውስጥ የቋንቋውን አገልግሎት የሚመለከቱ ሌሎች ይዘቶች ማለትም ቋንቋው በመገናኛ ብዙሃንና በሌሎች ማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ የሚያስገነዝቡ መረጃዎች አልተገኙም::

<u>አማርኛን በማስተማር ልዩ ዘዴ</u> I/II ውስጥ በየኮርሶቹ ዓላማዎችና ቢጋሮች ውስጥ የተዘረዘሩት ነጥቦች ለተማሪዎቹ መቅረባቸውን ከየማስታወሻ ደብተሮቻቸው በማመሳከር ለመረዳት ተችሏል:: ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ውስጥም የንባብ ክሂል በርዕስ ነገርነት ቀርቧል:: ይሁንና ዕጩ መምህራኑ የራሳቸውን የንባብ ክሂል የሚዳብሩትንም ሆነ ለተማሪዎቹ የሚያስተምሩበትን ሥልት የሚያስረዱ ዝርዝር ይዘቶች ማግኘት አልተቻለም:: ሌላው በጨረፍታ የተነካው የንግግር ክሂል ነው:: ይህ ክሂል <u>የማስተማር ዘዴ ሴሚናር</u> በሚባለው ኮርስ ውስጥ ለይስሙላ ከመጠቀሱ በስተቀር ንግግርን እንዴት መማርና ማስተማር እንደሚቻል የሚያመለክቱ ይዘቶች አልቀረቡም::

ቋንቋን ለማስተማር የሚሰለጥን ዕጩ መምህር በሚገባ ሊገነዘባቸው ከሚገቡት ጉዳዮች አንዱ፣ ያስተማረውን ትምህርት በተማሪዎቹ ዘንድ ያስገኘውን የባህርይ ለውጥ ለመመዘንና ለመገምገም የሚያስችል ቋንቋን የመፈተን ሥልት ነው:: ይህ ቋንቋን የመፈተን ስልት ለዕጩ መምህራን በዋና የትምህርት ይዘትነትም ሊቀርብ ይገባል:: ነገር ግን በአቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ውስጥ ስለቋንቋው ፈተና ዓይነቶችና ባህርያቸው ግንዛቤ ሊያስጨብጡ የቁጥር ፍሬ ነገሮች አልተገኙም::

አማርኛን የማስተማር ሰ.ቅ ዘዴ ፲ በተባለው ጽሑፍ ውስጥ "የተለያዩ ፈተናዎችና መልመጃዎችን ማዘጋጀት" የሚል ርዕስ ነገር የቀረበ ቢሆንም በተደረገው የሰነድ ፍተሻና ማመሳከር ፈተናን የተመለከተ ጉዳዮች አልተገኙም::

ቋንቋን በማስተማር ሂደት ውስጥ የሚፈጠሩ ቋንቋ ነክ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ ገንቢ ሃሳባዊ መረጃዎችን የሚሰጡ ተገቢ ጽሑፎችን ለሰልጣኞች መምህር በስልጠናው ወቅት ማቅረብ ይገባል:: በዚህ ረገድ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሚገኙትን መርሀ-ገብር በአባይ የአማርኛ ጽሑፎች ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃ ገዐዝ እና የትርጉም መግቢያ የተባሉ ጽሑፎች እንደሚሰጡ (ታውቋል):: ጽሑፎቹም በአላማዎቻቸውና በቢጋሮቻቸው ያነሷቸውን ዝርዝር መረጃዎች መርምረንና ከተማሪዎች ማስታወሻዎችም ጋር አመሳክረን አንዳዋናቸው ሊነሱ የሚገባቸው ነጥቦች ተገቢው ትኩረት ያልተደረገባቸው መሆኑን ለመረዳት ችለናል::

የመጀመሪያ ደረጃ ገዐዝ በተባለው ጽሑፍ አላማና ቢጋር ውስጥ የተጠቀሱት ነጥቦች በተሟላ ሁኔታ በተማሪዎች ማስታወሻና ከፈተናው ውስጥ አልተገኙም:: የትርጉም መግቢያ የተባለው ጽሑፍ ገና በመስጠት ላይ ስላለ የማጠቃለያ አስተያየት ለመስጠት አልቻልም::

## 5.2 መደምደሚያ

በተደረገው የአባይ ጽሑፎች ይዘት ትንተና የተገኙት ዋና ዋና ነጥቦች ከላይ በማጠቃለያው ክፍል ቀርበዋል:: እነሱን መሠረት አድርገን ስንነሳ ተማሪዎች በአጠቃላይ ስለቋንቋ ምንነትና ባህርያት ስለአማርኛ፣ ድምፆችና ምዕላዶች፣ ሀረጎችና ዓረፍተ ነገሮች አወቃቀር ግንዛቤ እንዲያገኙ መደረጉ የተገባ ነው:: የሥነ ጽሁፍን አገልግሎት ለማስገንዘብ በቀረቡት ጽሑፎች ውስጥ ያሉት የሥነ ጽሁፍን ምንነትና ዘርፎችን የሚያመለክቱ ይዘቶች መቅረባቸውም አገባብ ነው::

ከዚህም ሌላ የምርምርን ምንነት የአሰራር መርሆና የዘገባ አፃፃፍን

በሚመለከት ገንዘቡ እንዲያገኙ ጥረት መደረጉ ተሳታፊዎቹ በሥራ ዓለም ሲሰማሩ፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሙያዊና ማህበራዊ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ምርምር እንዲቀከሩ ሊያነቃቃቸው ስለሚችል ተገቢነት አለው::

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚታሰቡ ለየ ለየ ቋንቋን መለመዱና መማር የሚመለከቱ ገደሬ ሃሳቦች መቀረባቸውም በበጐ ጐንነት የሚታይ ነው::

በአንፃሩ ግን በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ዋናዎቹ ጉልህ ሥፍራ ሊሰጣቸው የሚገባቸው የቋንቋ ክሂሎች በተጠናከረ መልክ አልቀረቡም::

ዐው መምህራን ከሥልጠና በኋላ ለተማሪዎቻቸው የሚያስተምሯቸውን ዋና ዋና የቋንቋ ትምህርት አካላት ሳይማሩና ሳይለማመዱ የቋንቋ መምህራን ናቸሁ ብሎ ማስመረቁ ተገቢነቱ አይታይም::

የተሟላ የቋንቋ ክሂሎን በሥልጠናው ውስጥ ሳያካትቱ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በተመለከተ የተነደፉ ገደሬ ሃሳቦችን ማስተማሩ አፍአዊ እውቀት ከመንገር ያለፈ አገልግሎት ያለው አይመስለም::

በሥነ ልሣን ኮርሶች ረገድም ቢሆን ከአጠቃላይ የአበይ ኮርሶች ይዘት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆነውን በዛት የሚሸፍን ከመሆኑ አንፃር ሲታይ ከቋንቋ ምንነትና ባህርያት ያለፈ፣ ሥነ ልሣን በቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ ያለውን ተግባራዊ ሚና አለማሳየቱ የትኩረት አቀባባውን የሳተ አስመስሎታል::

የቋንቋን ገለጋሉት በማስገንዘብም በኩል የሥነ ጽሁፍን ምንነትና ዘርፎች ከማስረዳት አልፎ በቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ የሥነ ጽሁፍ አገልግሎት ምን እንደሆነ አያመለክትም:: እንዲሁም ቋንቋው በመገናኛ ብዙሃንና በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ድርሻ አያስረዳም::

የቋንቋን ፈተና ምንነትና ዓይነት የተመለከተ ይዘት አለመኖሩ አንዱ ችግር ሲሆን በተጓዳኝ መስኮችም በኩል ያለው የትምህርት ይዘት ለአማርኛ ቋንቋ ካለው ደጋፊነት አንፃር አለመቅረቡ ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ ነው::

## 5.3. የመፍትሔ ሀሳቦች

ከጥናቱ ማጠቃለያና ከመደምደሚያው በተገኙ የጥናቱ ሃሳቦች ላይ በመመርኮዝ የሚከተሉት የመፍትሔ ሃሳቦች ቀርበዋል::

1. በአቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ውስጥ የቋንቋ ክሂሎችን የሚመለከቱ ይዘቶች ራሳቸውን ችለው በግልፅ ቢቀርቡ፤
2. ሥነ ልሣንን የሚመለከቱ ኮርሶች አማርኛን በመማርና በማስተማር ላይ ያተኮረ ይዘት እንዲኖራቸው ጥረት ቢደረግ፤
3. የቋንቋን አገልግሎት በተመለከተ የቀረበው የሥነ ጽሑፍ ኮርስ ሥነ ጽሑፍ በቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ ያለው ጠቀሜታ ቢገለጽ እንዲሁም ሌሎች የቋንቋው አገልግሎቶች በውል የሚቀርቡበት ሥልት ቢቀየስ፤
4. በማስተማር ዘዴ ኮርሶች ውስጥ አፋቸውን በአማርኛ የፈቱና ያልፈቱትን ለይቶ ማስተማር የሚያስችል የትምህርት ይዘት ቢቀርብ፤
5. የአማርኛን ቋንቋ ፈተና የሚመለከቱ የትምህርት ይዘቶች በቀጥታ የሚቀርቡበት መንገድ ቢፈለግ፤
6. የተጓዳኝ መስኮች ይዘት አማርኛን ለመማርና ለማስተማር በሚያግዝ መልኩ ቢቀርብ

## ዋቢ መጻሕፍት


ሥርዓተ ትምህርት ገምጋሚና የትም. ምርምር ጥና ክፍል :: 1978 :: በኢትዮጵያ ትምህርት ጥናታዊ ግምገማ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና የመማር ማስተማር ሂደት ጥናት ሪፖርት :: ቅጽ 1 ቁጥር 1 :: አዲስ አበባ ፤ ትምህርት ሚኒስቴር ::

ባህሩ አክሊሉ :: 1986 :: በአማርኛ ቋንቋ ንግግር የማስተማር ልምምድ ውስጥ የተማሪ አስተማሪዎች ይዘትንና የማስተማሪያ ዘዴዎችን ማዛመድ ያቃታቸዋል :: አዲስ አበባ ፤ ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ / ለሴሚናር የተባዛና ያልታተመ /

ተስፋዬ ሸዋዬ :: 1981 :: ስነ-ልሳንና ቋንቋን ማስተማር :: አዲስ አበባ / ተባዝቶ የተጠረዘ/ ::

ትምህርት ሚኒስቴር :: 1983 :: የኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ መምህራን ትምህርት ሥልጠና ጥናታዊ ግምገማ :: አዲስ አበባ ፤ ት.መ.ማ.ማ. ድርጅት ::

ጌታቸው ኃይሉና ኃይሉ ፋሲል :: 1959 :: የአማርኛ ሰዋሰው ትምህርት ::

Secondary School Curriculum Development and ESLC Examination Seminar Final Report. Addis Ababa: Ministry of Education and U.S.I.U. Education Faculty (Mimeographed).

Abraham Hussain. 1990. Secondary Teacher Education in Ethiopia-Progression or Regression: A Comparative Study. Cambridge: Cambridge University. (Mimeographed).

__________. 1991. "A Comparative Study in the Preparation of Senior Secondary School Teachers in Ethiopia: 1962/63-1988-89." The Ethiopian Journal of Education. IER/AAU. Vol. 12 No. 1 (1-40).

Alemayehu G/Mariam. 1985. " The Teaching Practice Program of Kotebe College of Teachers Education: An Investigation Into its Adequacy In Preparing Teachers of English for Secondary Schools." Addis Ababa: AAU. GS. (Thesis).

Ary, Donald, Lucy Cheser Jacobs and Asghar Rasavich. 1985. Introduction to Research in Education. 3rd ed. New York: Holt, Rinehart and Winston.

Borg. Walter, Merdith D. Gall. 1989. Educational Research: An Introduction. 5th ed. New York and London: Longmans.

Bowen, Donald J. 1976. " Teacher Training and Problems of Staffing the Schools." Language in Ethiopia. ed M. L. Bender (etal). London: Oxford University Press.

Brumfit, C.J. and J. J. Roberts. 1983. An Introduction to Language and Language Teaching. London: Bastford Academic and Educational. Ltd.

Brumfit, Christopher. 1987. "Integrating Theory and Practice." Teacher Training. ed. Susan Holden, Hong Kong: MEP. Ltd.

Carter, Ronald and Michael N. Long. 1991. Teaching Literature. Harlow, Essex: Longmans.

Dejenie Leta. 1991. "Language Testing and its Washback Effect on Teaching. The ESLCE English Examination in Focus." Proceedings of the Major Issues Related to the ESLCE and Possible Solutions. Nazareth: IER; AAU.

Duff, Jony. 1983. Focus on the Learner: ed. Susan Holden. Bologna Conference: MEP.

Freeman, Donald. 1989. "Teacher Training, Development and Decision Making: A Model of Teaching and Related Strategies for Language Teacher Education." TESOL Quarterly. Vol. 23 No. 1 (27-45).

Fowler, Mary E. 1965. Teaching Language, Composition and Literature. New York Mcgraw Hill.

Habtamu Wondimu. 1994. Education, Training and Manpower Planning and Policy in Ethiopia. Addis Ababa: Ethiopia (Mimeographed).

Haile Woldemichael. 1976. "Government Schools in Ethiopia." Language in Ethiopia. ed. M. L. Bender (etal). London: Oxford University Press.

Hailom Banteyerga. 1992. Exploration in the Preparation of EFL Teachers: A Learning Centred Approach. Addis Ababa: Higher Education Main Department, Ministry of Education (Mimeographed).

Halliday, M. A. K., Angus McIntosh, Peter Strevens. 1965. The Linguistic Science and Language Teaching. London: Longmans.

Harison, Andrew. 1983. A Language Testing Handbook. ed. Flayell, Roger H. London: Macmillan Press.

Hill, L. A. and M. Dobbyn. 1984. A Teacher Training Course. London: Cassell

Holsti, Ole R. 1969. Content Analysis for the Social Sciences and Humanities. Massachusetts: Addison Wesley Publishing Company.

Hughes, Arther. 1989. Testing for Language Teachers. Cambridge: Cambridge University Press.

Kotebe College of Teachers Education. 1992. Catalogue. KTCE Computer Centre.

Koul, Lokesh. 1988. Methodology of Educational Research. 2nd Rev. ed. New Delhi. Vicas Publishing House Pvt. Ltd.

Krippendorff, Klaus. 1980. Content Analysis, An Introduction to Its Methodology. Beverly Hills: SAGE Publications.

Last, G. C. 1989. Teacher Education and Training: An Overview of Growth and Development and a Synthesis of Professional Experience. Addis Ababa: Ministry of Education.

Lazar, Gillian. 1993. Literature and Language Teaching: A Guide for Teachers and Trainers. Cambridge: Cambridge University Press.

Lewis, Michael and Jimmie Hill. 1990. Practical Techniques for Language Teaching. London: Commercial Colour Press.

Madsen, Harolds. 1983. Techniques in Testing. Hong Kong: Oxford University Press.

Malkova, Z. A. and B. L. Vulfson, (eds). 1988. International Yearbook of Education, Secondary Education in the World Today. Vol. 39. Geneva: UNESCO.

Mariani, Luciano. 1987. "Some Guidelines for Teacher Training Programs." Teacher Training. ed. Susan Holden. Hong Kong: MEP. Ltd.

Mcgrath, Ian. 1987. "Testing: What you need to Know." Teacher Training. ed. Susan Holden. Hong Kong: MEP. Ltd.

Rebert, Arthurs. 1985. Dictionary of Psychology. London: Penguin Books.

Sarason, Seymour B., Kenneths Davidson, Burton Blatt. 1986. The Preparation of Teachers: An Unstudied Problem in Education. (Rev. ed). Cambridge: Bookline Books.

Show, Peter A. 1987. "Handling a Language Component in a Teacher Training Course." Teacher Training. ed. Susan Holden. Hong Kong: MEP. Ltd.

Stern, H. H. 1983. Fundamental Concepts of Language Teaching. London: Oxford University Press.

Strevens, Peter. 1977. New Orientations in the Teaching of English. London: Oxford University Press.

UNESCO. 1973. "The Relationship between Education, Training and Employment with Particular Reference to Secondary Education, Its Aim, Structure and Content." International Conference on Education. Geneva: IBE.

Widdowson, H. G. 1991. Aspects of Language Teaching. Oxford University Press. London.

Williams, Eddie. 1984. Reading in the Language Classroom. Hong Kong: MacMillan Publishers Ltd.

# የተሟላ የቋንቋ ችሎታ መዋቅር

አባሪ 1

የኮርስ ርዕስ የዘገባ አጻጻፍና ሂሳዊ ንባብ ትምህርት

የኮርስ ቁጥር ______

የኮርሱ ዓላማዎች በትምህርቱ መጨረሻ ተማሪው:-

- የዘገባን ባሕርይና ቅርጽ መዘርዘር ይችላል::
- የዘገባንና የምርምርን ልዩነት መለየት ይችላል::
- የዘገባን መሠረታዊ ህጎች /ባህርያት/ መዘርዘር
- የተጻፈን ጽሑፍ መተንተን
- በተወሰኑ መጻሕፍት ላይ ሂስ ማቅረብ

| የኮርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ፈተና |
|---|---|---|
| - የዘገባ መሠረታዊ ባህርያት | - ዘገባ ምንድነው? | - ዘገባና ምርምር |
| - የዘገባ ቅርጽ | - የዘገባ ባህርይ | - ዘዘማዊ ጽሁፍ |
| - የዘገባ አቀራረብ | - ቴክኒካዊ ዘገባ | - የማስታወሻ አገልግሎት |
| - ዘገባና የምርምር ወረቀት | - የዘገባ ርዕስ | - የምርምር ዓይነት |
| - የምርምር ባህርያት | - የመረጃ ጽሁፍ | - መጠይቅ |
| - የምርምር አይነቶች | - የምርምር ባህርያት | - የሥነ-ጽሑፍ አገልግሎት |
| - የምርምር ዘዴዎች | - የምርምር አገልግሎት | - የኪነ-ጥበብ አቀራረብ |
| - ዕማሬና ፍካሬ | - አጥቅስ አቀማመጥ | - ታሪክና ሥነ-ጽሑፍ |
| - የዘይቤ አነጋገሮች | - የሂስ መርሆዎችና ህጎች | - የማስታወሻ አወሳሰድ |
| - የሂስ መርሆዎችና ሕጎች | - የሂስ አገልግሎት | - የሂስ አገልግሎት |
| - በተወሰኑ የአማርኛ መጽሐፍት ላይ ሂስ ማቅረብ | - አንብቦ መረዳት | - ስለ ሂስ ያለ አመለካከት |
| | - ዕማሬና ፍካሬ | - የሂስ ታሪክ |
| | - ዘይቤያዊ አነጋገር | - አንብቦ መረዳት |
| | | - የቃላት አገባብ |
| | | - የምርምር አካሄድ |
| | | - የምርምር ባህርያት |
| | | - የመረጃ ፍንጮች ቅደም ተከተል |
| | | - የመጠይቅ ትንታኔ |
| | | - የዘገባ አቀራረብ |
| | | - የማጣቀሻ አቀማመጥ |
| | | - የሂስ ትኩረት |

## የቋንቋ ባህርይና የሥነ-ልሣን ጥና    አባሪ ፱-፩

የኮርስ ርዕስ የቋንቋና ሥነ-ልሣን መግቢያ 1    የኮርስ ቁጥር ______

የኮርሱ ዓላማዎች ተማሪው በትምህርቱ መጨረሻ:-    ክሬዲት ______

-ቋንቋን መበየንና ባህርያቱን መለየት ናቸው::
-ስለ ቋንቋ ጥንተ አመጣጥ የተሰነዘሩትን ልዩ ልዩ ንድፈ ሀሣቦችንና አስተያየቶችን መለየት
-የቋንቋን አገልግሎት፣ ቅግርቾንና በውስጡ ሊከናወኑ የሚችሉትን ለውጦች መግለጽ:-
-በቋንቋ ሰመዓ ላይ ያሉትን ልዩ ልዩ ንድፈ ሀሳቦች መዘርዘር
-በቋንቋና በሀሳብ፣ በቋንቋና በባህል መካከል ያሉትን ግንኙነቶች መግለጽ:-
-ሥነ-ልሣንን መግለጽና ታሪኩን መዘርዘር ይችላሉ::

| የኮርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ሬተና |
| --- | --- | --- |
| -የቋንቋ ምንነት | -የቋንቋ ጥናት ለምን? | -የቋንቋ ብያኔ |
| -የቋንቋ ባህርያት | -ቋንቋ ምንድን ነው? | -የቋንቋ ድክመቶች |
| -የቋንቋ አገልግሎት | -የቋንቋ ባህርይ-በዘፈቀደ የተገኘ | -የቋንቋ አገልግሎት |
| -ሰብዕና ለመመስረቻ | -አንደበታዊ | -የሥነ ልሣን ትምህርት |
| -ወዳጅነት ለማፍራት | -ሰበዓዊ | ሣይንሣዊነት |
| -ስለተናጋሪው ማንነት ጠቋሚ | -ሰብአዊ | -ቋንቋን መለመድ |
| -ሀሣብ ለማግኘት | -መግባቢያ | -የቋንቋ ባህርይ/ |
| -ለሀሣብ ማስተላለፊያ | -ትዕምርታዊ | የቋዊ መሆን |
| -መዘርዝራዊ | -ባለፍቺነት | -የስነ ልሣን ዕድገት |
| -ማገባቢያ | -አዝናዊነት | /ታሪክ/ |
| -ስሜታዊ | -አዝጋሚነት | -የቋንቋ ጥንተ አመ |
| -ኪነታዊ/ውበታዊ | -አቅጣጫው ይታወቃል | ጣጥ /ሆኬት/ |
| -ሁኔታዊ | -ተለዋዋጭነት | -ቋንቋን መማር |
| -የቋንቋ ድክመቶች | -ውሱንነት | -ቋንቋና ሀሣብ |
| | -ልዩነት አለው | -ቋንቋና ህብረተሰብ |
| -የቋንቋ ጥንተ አመጣጥ | -አፍላቂነት | -የቋንቋ ለውጥ |
| -መለኮታዊ አስተያየት | -ባህላዊነት | |
| -ደመነፍሳዊ " | -የቋንቋ አጀማመር | |
| -የድምጽ ቅጽ " | -መለኮታዊ | |
| -መልስ ማዋቀር " | -የደመነፍስ ንድፈ ሀሣብ | |
| -የሆኬት " | -የቻርለስ ሆኬት ንድፈ ሀሣብ | |
| -የአዝጋሚ ለውጥ " | -የማርክሳዊያን አመለካከት | |
| -የማርክሳዊያን " | -ታሪካዊና ንጽጽራዊ ሥነ-ልሣን | |
| -ቋንቋና ሀሣብ | ምሁራን አመለካከት | |

| የኮርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ፈተና |
|---|---|---|
| —የቋንቋ አለማመድ<br>—የራሽናሊስቶች አስተያየት<br>—የኢምፕሪሲስቶች አስተያየት<br>—የነፒያዤ አስተያየት<br>—ቋንቋና ለውጥ<br>—ቋንቋ በባህልና ህብረተሰብ<br>—የቋንቋና የጽህፈት ታሪክ<br>—የሥነ-ልሣን ምንነት | —የባህርያዊያን ገደፊ ሀሣብ<br>—የቋንቋ ተግባር/አገልግሎት<br>—ማህበራዊ<br>—በለሎች ማስገንዘቢያ<br>—ስብዕና መመስረቻ<br>—ለማሰብ ያስችላል<br>—የሰውን ነገር ያስገነዝባል<br>—መግባቢያ<br>—መዘርዝራዊ/ነጋሪነት/<br>—ስሜታዊ አገልግሎት<br>—ኪነታዊ አገልግሎት<br>—ሁኔታዊ አገልግሎት<br>—የቋንቋ ውሱንነት/ድክመት<br>—የስሜት መናጋት<br>—የተወሳሰቡ አሰራሮች<br>—በከፍተኛ ፍጥነት የሚከናወኑ ነገሮችን አለመግለጽ<br>—አሻሚነት<br>—ቋንቋና ሀሣብ<br>—ቋንቋን መልመድና መማር<br>—የቋንቋ ጥናት ደረጃ<br>—የቋንቋ ለውጥ<br>—ቋንቋና ማህበረሰብ<br>—ቋንቋና ባህል<br>—ቋንቋና መደብ<br>—ስነ-ልሣን ምንድነው? | |

## የቋንቋ ባህርይና የሥነ-ልሳን ጥናት          አባሪ 2-2

**የኮርስ ርዕስ ቋንቋና ሥነ-ልሳን መግቢያ**          የኮርስ ቁጥር ________

የኮርሱ ዓላማዎች በትምህርቱ መጨረሻ ተማሪው:-

- -የቋንቋን ንጥረ ድምፆች መለየትና መመደብ ይችላል
- -ሥነ-ድምጻዊ ለውጦችን ሂደትና ሁኔታ ያመለክታል
- -ሆህያትንና ምዕላዶችን መበየንና መለየት ይችላል::
- -የምዕላዶችን ዓይነቶች መለየትና ሥርጭታቸውን ማመልከት ይችላል::
- -የሥነ-ድምጽ ጥናትን መግለጽና የንግግር ድምጾች አወጣጥ ሂደትን ማስረዳት ይችላል::
- -የንግግር ድምጾችን ቅርጽ ይለያል ይጽፋል::

| የኮርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ሬ ተና |
|---|---|---|
| -ሥነ-ድምጽ ምንድነው? | -ሥነ-ድምጽ - ንበባዊ፣ ሞገዳዊ | -የምዕላድ ብያኔ |
| -ዕዝናዊ ሥነ-ድምጽ | ዕዝናዊ | -ሥርዎ ቃል |
| -ሞገዳዊ ሥነ-ድምጽ | -የአንደበት ክፍሎች | -ንጥረ ድምጽ |
| -ንበባዊ ሥነ-ድምጽ | -አናባቢና ተነባቢ | -ምዕላድና ቃል |
| -አንደበት | -የንግግር ድምጾች አገላለጽ | -ሥነ-ድምጽ |
| -ልዩ ልዩ የአንደበት ክፍሎች | " " አወካከል | -በ ዋሰው ርባታ |
| -የንግግር ድምጾች | / / | -ሥነ ድምጽ ልሣን |
| -ተነባቢያት | -የድምጾች ክምችት | -የምዕላድ ዓይነቶች |
| -አናባቢያት | -ሥነ-ድምጽ-ልሣን | -የቃላት አመሠራረ |
| -የሥነ-ድምጽ ፊደል | -ንጥረ ድምጽና ዘረ ድምጽ | -የቃላት መዋቅር |
| -የሥነ-ድምጽ ፊደል ባህርይ | -ሥነ ድምጽ ልሣናዊ አጻጻፍ | -አናባቢና ተነባቢ |
| -በሥነ-ድምጽ ፊደል | -የድምጾች ሥርጭት | -ቃላትና ቅጥያቸው |
| የመጻፍ ተግባራዊ ልምምድ | -ሳዕለ ድምጽ-ጥብቀት | -የቃላት ፍቺ |
| -ሳዕለ ድምጾች | የድምጽ ቃና | -በንጥረ ድምጽ |
| -ርዝማኔ | ቅምታ | የመጻፍ ልምምዶች |
| -ጫና/ይዘት | ሥነ-ምዕላድ ብያኔ | -የምዕላድ አጻጻፍ |
| -ጥብቀት | -ንጥረ ምዕላድና ቃል | ልምምዶች |
| -የድምጽ አነሣሥና አወዳደቅ | -የቃላት አመሠራረት | -የቀለሞች ጉዳይ |
| -ቅምታ | -ቃል ለዋጭ | /ሆሄ/ |
| -ሥነ-ድምጽ ልሣን | -የዕርባታ ምዕላዶች | -ዘረ-ምዕላዶች |
| -ብያኔ | -የቃል ውስጥ ቅጥያ | |
| -ከሥነ-ድምጽ ጋር ያለው | -ዘረንጥረ ምዕላድ | |
| ልዩነት | -ንጥረ ምዕላድን መለየት | |
| -የንጥረ ድምጽ ምንነት | ዘዴ | |
| -ንጥረ ድምጻዊ | -የጀርሰን ሀኬት ዘዴ | |
| | -የቤለምክስ ዘዴ | |

..../

| የክርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ፈተና |
|---|---|---|
| ተግባራዊ ለምምት<br>—ዘረ ዱምጽ — ብያኔ<br>—የሚገኙበት ሁኔታ<br>—የዱምጸች ሥርጭት<br>—ተደጋጋፊ ስርጭት<br>—ተነጻጻሪ ሥርጭት<br>—ተለዋዋጭ ሥርጭት<br>—ዱምጸች ሲጉራበቱ የሚፈ<br>ጠሩ ለዉጦች—ዉህደት<br>/የቀርብ፣ የሩቅ፣ሙሉ፣ከፊል፣<br>—ለዉነት—ገዴፈት፣ ፈለቃዊ፣<br>ለዉጦች፣ ዱግገጦሽ<br>—ቀለም/ሆሄ/ ምንነትና<br>ጠዋቀር—መነሻ፣ ቀገዴ፣<br>ቡጥ፣ ወደረሻ<br>—ምዕላዱ—ብያኔ<br>—ነጥረ ምዕላዱን የመለየት<br>ዘዴ<br>—የነጥረ ምዕላዱ አይነቶች<br>—ዘረ—ምዕላዱ—ብያኔ<br>—ምዕላዶችን የመለየት<br>ተግባራዊ ልምምዱ | —የሥነ—ምዕላዱ ለዉጦች—<br>ዉህደት ከፊል ዉህደት፣<br>የጠደኋሳ ዉህደት፣<br>የሩቅ ዉህደት<br>—የዱምጽ ገዴፈት<br>—ለዉዉጠሽ<br>—ዱግገጦሽ—ሙሉ ዱግገጦሽ<br>—ከፊል ዱግገጦሽ | |

## የቋንቋ ባህርይና የሥነ-ልሣን ጥናት

አበፅ ፪—፫

የኮርስ ቁጥር ________

የኮርስ ርዕስ አማርኛ ሰዋስው

የኮርሱ ዓላማዎች በዚህ ኮርስ ማጠቃለያ ተማሪው፣
- —የአማርኛን ሥነ—ድምጽና የሆሄያት ሥርዓትይይ ተነትናል
- —በአማርኛ ይናራሉ ተበለው የሚጠቁ የቃላት መዋቅሮችን ይናገራል
- —የቋንቋውን አነባበቢና ቃላዊ ክፍሎች ይለያል

| የኮርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ሬተና |
|---|---|---|
| —የአማርኛ ሥነ—ድምጽ ክለሳ<br>—የአማርኛ ሆሄ ሥርዓት ክለሳ<br>—በአማርኛ የቃላት ምሥረታ<br>—እርባታ<br>—ጥምሬያ/ጥምረት<br>—ቃል ለዋጭ<br>—ቃላዊና አገባባዊ ክፍሎች | —የትምህርቱ አበይት ክፍሎች<br>—ሥነ—ድምጽ<br>. ተነባቢ<br>. አናባቢ<br>. ሆሄ<br>—ሥነ—ምዕላድ<br>—ሥነ—መዋቅር<br>. ሀረግ<br>. ዓረፍተ ነገር<br>—ሥነ—ምዕላድ ትርጉም የለሽ<br>" " ያለሽ<br>—የቋንቋ መዋቅር<br>—የአማርኛ ቋንቋ መዋቅር ከሌሎች ስለመለየቱ<br>—ድምጽ:—<br>—የድምጽ ባህርያት<br>—የቋንቋ ድምጾች<br>—የድምጽ አፈጣጠር<br>—የአማርኛ ተነባቢ ድምጾች ሰንጠረዥ<br>ባህር የንባብና መከናንባብ<br>—የአማርኛ ድምጽ ሥርጭት<br>—በቃል መጀመሪያ የሚገኙ /የማይገኙ<br>—በቃል መሀከል የሚገኙ /የማይገኙ<br>—በቃል መጨረሻ የሚገኙ /የማይገኙ | —አናባቢዎችን መግለጽ<br>—የድምጾችን ባህርይ መግለጽ<br>—ሆያትን መለየት<br>—ምዕላዶችን መለየት<br>—የግሶችን ቁርጽ መለየት<br>—የግሶችን ምድብ መለየት<br>—የቃላትን ባህርያት መለየት<br>—የድምጽ ክምችት<br>—ቃል ለዋጭ ምዕላድ |

| የክርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ፊ ትና |
| --- | --- | --- |
| | — የአማርኛ ሀሄ መዋቅር<br>☰ የአማርኛ ገሥ ቅርጽ<br>— የአማርኛ ገቦች አገር | |

## የቋንቋ ባህርይና የሥነ-ልሳን ጥና

አባሪ 2-4

የኮርስ ርዕስ አማርኛ ሰዋስው

የኮርስ ቁጥር ______

የኮርሱ ዓላማዎች በዚህ ኮርስ መጨረሻ ተማሪው፣

-የአማርኛን ሀረጋዊ መዋቅር ይተነትናል

-የአማርኛ ነጠላና ድርብ ንዑስን ሀረጋትን መዋቅር ያጠናል

| የኮርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ሬተና |
|---|---|---|
| -የአማርኛ ሀረጋዊ መዋቅር<br>-የአማርኛ ነጠላ ንዑስ ሀረግ<br>-የአማርኛ ድርብ ንዑስ ሀረግ<br>-ጥገና ሀረጋት<br>-የአዛማጅ/ዘማዊ ሀረጋት መዋቅር | -የአማርኛ የቃል ክፍሎች ዝኀዊ ግምገማ<br>-ቃላት የሀረግ መሠረቶች<br>-የቃላት ባህርይ<br>-ስም፣ግስ፣ቅጽል<br>-የቃላን ክፍል ለመወሰን እንዴት ይቻላል? በቋንቋው በራሱ፡፡<br>-የቃል ክፍሎች<br>-ስማዊ ሀረግ<br>-ግሳዊ ሀረግ<br>-ቅጽላዊ ሀረግ<br>-መስተዋድዳዊ ሀረግ<br>-የሀረግ ባህርያት<br>-መሪነት<br>-መሙያ<br>-አጉላማሽ<br>-የሀረግ መሪ በታ ቀን/ገራ<br>-ግንኙነት<br>-ተቋራጭነት<br>-የመዊ ሀረግ<br>-መስተጻምር<br>-ጠቋሚ<br>-መጠን<br>-አገናዛቢ<br>-የሀረግ መዋቅር<br>.ትርጉም/ፍች/ ተሸካሚ ሆሄያት<br>.የተጓረዱ/ሁለት እግሮች/<br>.ያልተጓረዱ/ሦስት እግሮች/ | ፡ስዋስዋዊ አገልግሎታዊ ክፍሎችን መለየት<br>.ስለቃል ክፍሎች ራሳቸውን መቻል ማብራሪያ<br>.የአጉላማሽና መሙያ ልዩነት<br>.የሀረግ መሪ<br>.ስማዊ ሀረግና ባህርዩ<br>.ስለ ተውሳከ ግስ<br>.የሀረጎችን መዋቅር ማሳየት |

| የኮርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ፈተና |
| --- | --- | --- |
| | • ያልተጐረጐ ባለአራት አግሮች<br>• ማጥበቅና ማላላት<br>ቃል ምሥረታ<br>• ቃል በሦስት ዓይነት ለመሠራት ይችላል<br>• ውስጣዊ ቅርጹን በመቀየር<br>• በገሀዱ የሚታዩ ቀዳማይና ደኃራይ ቅጥያዎች<br>• በቃላት ጥምረት | |

የቋንቋ ባህርይና የሥነ-ልሣን ጥና　　　ሰዓት 2-5

የኮርስ ርዕስ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ቅኝት　　　የኮርስ ቁጥር ______

የኮርሱ ዓላማዎች　በዚህ ኮርስ መጨረሻ ተማሪው፣　　　ክሬዲት 3

-የታሪካዊና ንጽጽራዊ ሥነ-ልሣንን ምንነትና አድገት ያብራራል::

-በቋንቋዎች ውስጥ ሲኖር የሚቻለውን ለውጥ ይናገራል::

-በታይፖሎጂካልና ጄኔሎጂካል አከፋፈል፣ በንጽጽራዊ ዘዴና መልሶ በመቀቆር ሞዴሎች መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያል::

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን አከፋፈልና ቤተሰባዊ ዝምድና ያበረዓል::

| የኮርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ሪተ |
|---|---|---|
| -ታሪካዊና ንጽጽራዊ ሥነ-ልሣን የቋንቋ ለውጥ<br>-ውጫዊ<br>-ውስጣዊ<br>-የቋንቋዎች ሥነ-ምድራዊ /Topological/ ክፍፍል<br>-የቋንቋዎች ቤተሰባዊ ክፍፍል<br>-ንጽጽራዊ ዘዴ<br>-መልሶ የማቀቆር ዘዴ<br>-የቋንቋ ሞዴሎች<br>-በአፍሪካ ቋንቋዎች ላይ የተደረጉ ጥናቶችና የአፍሪካ ቋንቋዎች አከፋፈል ቅኝት<br>-የኢትዮጵያ ቋንቋዎች<br>-ኢትዮ ሴማዊ ቋንቋዎች<br>-የኢትዮጵያ ኩሻዊ ቋንቋዎች<br>-ኦሞአዊ ቋንቋዎች<br>-በኢትዮጵያ የሚገኙ አባይ ባህራዊ ቋንቋዎች<br>-ከእያንዳንዱ ቅርንጫፍ የተጠከይ ቋንቋዎች ገለጻ | -ቋንቋ ምንድን ነው?<br>-ቋንቋ ማህበረ ሠባዊነት<br>-የቋንቋ ዘረ ቀዓዊነት<br>-የቋንቋ አንደበታዊነት<br>-የቋንቋ ትዕምርታዊነት<br>- " ሥርዓታዊነት<br>- " መግባቢያነት<br>-ቋንቋ ከማህበረሰብ ጋር ያለው ግንኙነት<br>-የቋንቋ አጠቃቀም<br>-የገጠር /የከተማ<br>-የተማረ /ያልተማረ<br>-በጾታ<br>-በእድሜ<br>-በሥራ ቦታ<br>-በአጠቃላይ ሥነ-ልሣን/ Macro Lingustics/<br>-ንዑስ ሥነ-ልሣን /Micro/<br>-የሥነ-ልሣን ክፍሎች<br>-ገለጻዊ ሥነ-ልሣን<br>-ታሪካዊ ሥነ-ልሣን<br>-ንጽጽራዊ ሥነ-ልሣን<br>-የቋንቋ ለውጥ /Language change/<br>-የሥነ-ፍቺ ለውጥ<br>-የሥነ-ድምጽ ለውጥ<br>-ተነባቢ ድምጾች<br>-በባህርይ ንባብ ላይ የሚደረግ መሻሻል | |

.../

| የኮርሱ ቢጋር | የተማሪዎች መስታወሻ | ፈተና |
|---|---|---|
| | -ኢኮኖሚያዊ ለውጥ<br>-የሥርዓተ-ማህበር ለውጥ<br>-የህዝቦች ግንኙነት/ጦርነት፣ ንግድ ወ.ዘ.ተ/<br>-ወረራ<br>-ለውጥ የሚካሄድባቸው የቋንቋ ክፍሎች<br>. ድምፅ ቀጁ<br>. የቋንቋ መዋዋስ<br>-የቋንቋ መከፋፈያ ዘዴዎች<br>. ውጫዊ መረጃ<br>. ውስጣዊ መረጃ | |

## የ[illegible] አገልግሎት

አባሪ 3.1

የኮርስ ርዕስ የሥነ-ጽሑፍ መሠረታውያን

የኮርስ ቁጥር ________

የኮርሱ ዓላማዎች በኮርሱ መጨረሻ ተማሪዎች፦

- የአማርኛ ሥነ-ጽሑፍን ባህርያትና ዓይነቶች መለየት
- በአጭርና በረጅም ልቦለድ ልዩነት ላይ በመመርኮዝ የሌሎችንም ዘርፎች ባህርያት ለይቶ ማመልከት
- በክፍል ውስጥ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎችን መገምገም

| የኮርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ሪተና |
|---|---|---|
| —ሥነ ጽሑፍና የሥነ-ጽሑፍ ጥናት<br>—የሥነ-ጽሑፍ ዋና ዋናዎቹ ገጽታዎች /ዓይነቶች/<br>  —ሥነ-ግጥም<br>  —ድራማ<br>  —አጭር ልቦለድ<br>  —አጭር ልቦለድ<br>—የሥነ-ጽሑፍ መለያ ባህርያት /ገጽታዎች/<br>—የአጭር ልቦለድና የረጅም ልቦለድ የጋራ ባህርያት<br>—የተመረጡ የአማርኛ ረጅም ልቦለዶችን መቃኘትና መተንተን<br>—በአማርኛ አጭር ልቦለድ ወይም ረጅም ልቦለድ ላይ የሴሚናር ወረቀት ማቅረብ | —የሥነ-ጽሑፍ ጠቀሜታ<br>—የሥነ-ጽሑፍ ዘርፍ<br>—የሥነ-ጽሑፍ አላባውያን<br>—የቃላት አጠቃቀም<br>—ገጸባህርያት<br>—ጭብጥ<br>—የጽሑፍ ዓይነቶች<br>—አንጻር<br>—ትልም/ቼሎት/<br>—ሂስ<br>—ድምፀት<br>—ድራማዊ ልቦለድ<br>—ገፀባህርያት ልቦለድ<br>—ዜና መዋዕል<br>—አጭር ልቦለድ<br>—ግጥም፣ ተውኔት፣ ልቦለድ<br>—ሥነ-ግጥም | —የሥነ-ጽሑፍ መለያ<br>— " ዓላማ<br>—የሥነ-ጽሑፍ ዘርፎች<br>—ኪነጥበብና የህብረተሰብ ግንኙነት<br>—የፈጠራ ሥራ ሀሳቡና<br>—የሥነ-ጽሑፍ አገልግሎት<br>—የሥነ-ጽሑፍ ግንዛቤ<br>—የሥነ-ቃል አገልግሎት<br>—የሥነ-ጽሑፍ መልእክት<br>—የገፀባህርያት ምንነት<br>—ሥነ-ጽሑፍና ምናብ<br>—ታሪካዊ ልቦለድና ባህርያቱ<br>—የደራሲያን ስሜት<br>—ሥነ-ምግባርና የፈጠራ ጽሑፎች<br>—የልቦለድ ጽሑፍ ዓላማ<br>—ጭብጥን መረዳት<br>—የሥነ-ቃል ባህርያት |

## የቋንቋ አገልግሎት

አባሪ 5-2

የኮርስ ርዕስ የአማርኛ ሥነ-ግጥም

የኮርስ ቁጥር ________

የኮርሱ ዓላማዎች በዚህ ኮርስ መጨረሻ ተማሪው፣

- የሥነ-ግጥም አጀማመርና ምንነት ይዘረዝራል
- የሥነ-ቃልንና የሥነ-ግጥምን ባህርያት ይዘረዝራል
- የሥነ-ግጥምን ቋንቋ ይመረምራል
- ግጥም አንብቦ መልዕክቱን መተርጐም ይቻላል
- በጥቂት የአማርኛ ግጥሞች ላይ ሂሳዊ ግምገማ ይሰጣል::

| የኮርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ፈተና |
|---|---|---|
| —የሥነ-ግጥም ክፍሎች<br>—የሥነ-ግጥም አጀማመር<br>—የቃልና ጽሁፋዊ ሥነ-ግጥም<br>—የሥነ-ግጥም ቋንቋ<br>—ምትና ዜማ<br>—ዘይቤና ቋንቋ<br>—ተምሳሌታዊነት<br>—ቅኔ<br>—ሥነ-ግጥምን አንብቦ መረዳት<br>—በአንዳንድ ግጥሞች ላይ የግምገማ ጽሁፍ ማቅረብ<br>—አገጣጠምን በተግባር መማር | —ሥነ-ግጥም ምንድነው?<br>—ሥነ-ግጥም በምጣኔ የሚቀርብ ምርጥ ቃላት በምርጥ አደራደር የሚቀርብበት ነው<br>—ዘይቤ<br>• ተምሳሌታዊነት<br>• ምናብ<br>• አይረሴነት—ዘለለማዊ መሆን<br>• ስሜትን የሚነካ<br>• አብሰልሳይ<br>• የማያስቆምጥ/የማያስተኛ<br>—የአማርኛ ቅኔ<br>• የቅኔ ዓይነቶች<br>• ሰምና ወርቅ<br>• ኅብር<br>• ምርምር ቅኔ | —ዘይቤዎችን መለየት<br>—ዓይነታቸውን መናገር<br>—የግጥም ጥበብ ማውጣት<br>—የግጥም ገፀባህርያት<br>—ሥነ-ግጥምና ሥነ-ግጥማዊ ተውኔት<br>—የፈጠራ ሥራን መለየት<br>—የግጥም ተምሳሌት |

## የድጋፍ አገልግሎት  አባሪ 3-3

የኮርስ ርዕስ ተውኔት/ድራማ  የኮርስ ቁጥር ________

የኮርሱ ዓላማዎች በዚህ ኮርስ መጨረሻ ተማሪው፣

- የተውኔትን ደንብ ሀሳብ ይተነትናል
- የኢትዮጵያን ባህላዊ ተውኔት ከዘመናዊው የአማርኛ ተውኔት ማጐዳኘት ይችላል
- ከዘመናዊው የአማርኛ ተውኔት ውስጥ አንዳንድ ሥራዎችን መተንተን ይችላል
- በተውኔት ንባብ ይከፈላል

| የኮርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ፈተና |
|---|---|---|
| —ስለ ተውኔት ጠቅላላ መግቢያ<br>—የኢትዮጵያ የተውኔት ባህል<br>—የተውኔት አሳባውያን<br>—ተውኔትና ትያትር<br>—ተውኔትን ማዘጋጀት<br>—የተውኔት ንባብ<br>—በኢትዮጵያ ተውኔት ላይ የሚደረግ መለስተኛ ጥናታዊ ጽሁፍ | —የድራማ/ተውኔት ምንነት<br>—ትያትር ጥበባዊ<br>—የፈጠራ ድርሰት ስለመሆኑ<br>—በግጥምና በስድ ንባብ ይቀርባል<br>—የድርሰት ዓላማ<br>—ፀይፀት<br>—ባህርያት  መሰል<br>—ገፀባህርያት  ሊሆን ይችላል<br>—በመድረክ ላይ ይቀርባል<br>—ተዋንያኑ በንግግር በድርጊት በመድረክ ላይ ያቀርቡታል<br>—የተውኔት ጥበባቶች<br>.ፀሐፊ ተውኔት<br>.ሃያስ<br>.የመድረክ መሪ<br>.አለባበስ<br>.ጌጣጌጥ<br>.መሣሪያ/የሙዚቃ/<br>.መብራት<br>.ቀለም<br>—ድራማ የሚጠናቀቀው<br>ከጸሀፊተ—አዘጋጅ—ሃያሲ<br>ከሃያሲ—ወደመድረክ ቀርቦ ነው<br>—የድራማ አጀማመር<br>—የድራማ አይነቶች<br>.ትራጀዲና ኮመዲ | |

.../

| የኮርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ፈተና |
|---|---|---|
| | – የድራማ አላባውያን<br>ቋን ቋ፣ ሀሳብ፣ ገፀባህር ያት፣<br>ፕሎት<br>– የድራማ መታያ ሰዓት<br>ረጅም – 3 ሰዓት<br>አጭር – አንድ ገቢር<br>/30 ደቂቃ–1 ሰዓት/<br>የዓንዱው ጨቡጫ ድራማ<br>ግምገማ | |

## የቋንቋ ማስተማር ዘዴ

ስቦሬ 4 -1

የኮርስ ርዕስ አማርኛን የማስተማር ልዩ ዘዴ　　　　የኮርስ ቁጥር

የኮርስ ዓላማዎች ትምህርቱ ሲጠቃለል ተማሪዎች:-

- ተገቢ የሆነ የአማርኛን ማስተማሪያ ዓላማዎች ይነድፋሉ
- ቋንቋን ስለ መለመድ ባህርያት የተሰነዘሩ ንድፈ ሀሣቦችን ይረዳሉ፣ አማርኛን ለማስተማር የሚያገዙ ስልቶች ይቀይሳሉ
- በአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች መካከል ያሉ ግላዊ ልዩነቶችን ላይ ይወጣሉ *
- ለአንድ ሁኔታ የሚስማማ አማርኛን የማስተማሪያ ዘዴ መቀየስ ይችላሉ
- ንባብ አማርኛን ለመማር የሚጫወተውን ሚና ይለያሉ

| የኮርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ፈተና |
|---|---|---|
| - ቋንቋን መማርና ቋንቋን ማስተማር<br>• የመጀመሪያ ቋንቋ ብያኔ<br>• የሁለተኛ ቋንቋ ብያኔ ስለ ቋንቋ ለመዳ የሚያወሱ ንድፈ ሀሳቦች /በጠቅላለ<br>. ባሕርያዊነት<br>. ሜንታሊዝም<br>. አጽምሮታዊ<br>በቋንቋ ተማሪዎች መካከል ያሉ ግላዊ ልዩነቶች<br>. የቋንቋ ችሎታ<br>. ማነቃቂያ<br>. ዕድሜ<br>• የሁለተኛ ቋንቋን ማስተማሪያ ሥልቶች አጭጥር ብያኔ<br>• ሰዋሠዋዊና የትርጉም ዘዴ<br>ቀጥተኛ ዘዴ | • ቋንቋ መማር ምንድነው<br>• ቋንቋ መለመድ<br>• አንድን ቋንቋ ለመማርና ለማስተማር የምናከናውናቸው ነገሮች የትኞቹ ናቸው?<br>• የቋንቋ ችሎታ አስፈላጊነት ምንድን ነው?<br>• የቋንቋ ችሎታ መለኪያዎቹ ምንድን ናቸው<br>• አገርኛ ቋንቋን ለማስተማር ለምን አስፈለገ?<br>• የአፍ መፍቻ ቋንቋ አለማመድ ንድፈ ሀሣብ<br>- በአገርኛ ቋንቋ ትምህርት መስጠት ለምን አስፈለገ<br>= የአነ ስኪነር ንድፈ ዐሣብ<br>- የቾምስኪን ንድፈ ሀሣብ<br>አካባቢ ለሕፃናት ምን ያደርጋል | =. ቋንቋን መማር<br>-. ቋንቋን መለመድ<br>. ቋንቋን ማስተማር<br>- የአፍ መፍቻ ቋንቋ<br>- ሁለተኛ ቋንቋ<br>- አማርኛን የማስተማር አለማወች<br>- የቋንቋ መለመድ ንድፈ ሀሣብና /ፒያዤ/ዕድሜ የስኪነርና ቾምስኪ ንድፈ ሀሣቦች<br>- የሥነ ጽሁፍ ሥራዎች ለቋንቋ ትምህርት ያላቸው ጥቅም<br>- ሁለተኛ ቋንቋን የማስተማር ዘዴዎች ዓይነትና አገልግሎት |

| የኮርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ፈተና |
|---|---|---|
| • አዳምጦ መመለስ<br>•• አዳምጦና አይቶ ማስተማር<br>• አስፖርታዊ ዘዴ<br>• ተግባቦታዊ ዘዴ<br>• የቋንቋን ክሂሎች ማስተማር<br>• ቃላት • ፀሀፊት<br>• ስዋስው • ሥነ ጽሁፍ<br>• ንግግር<br>በቋንቋ መማር የንባብ ጭና<br>• ቀጥተኛ ችሎታ<br>• አስፖርታዊ ችሎታ<br>• ሥነ ጽሁፋዊ ችሎታ | • ባሕርያዊና ተፈጥሮአዊ ንድፈ ሀሣብ<br>• አስፖርታዊያን ተመራማሪዎች<br>• ቋንቋን የመማር ማስተማር አጠቃላይ ባሕርይ<br>– መለመዱንና መማርን /በተለይ አማርኛን የሚማሩ ምና ሊሆኑ ይችላሉ<br>• የቋንቋ መማር ግብ፣ የቋንቋ ችሎታን ከተለያዩ ሁኔታዎች መጠቀም መቻል ::<br><br>የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች<br>• የቋንቋ ማስተማር ታሪካዊ ጉዞ<br>• ስዋስዋዊ የትርጉም ዘዴ<br>• ቀጥተኛ ዘዴ<br>• አዳምጦ መናገር ዘዴ<br>• መስማትና ማየት ዘዴ<br>• አስምርታዊ ዘዴ<br>/ዘዴዎች ተነፃጽረው ቀርበዋል/<br>• የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ዐውዱ<br>– ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ቀጥሎ የሚለመድ መሆኑ<br>– እንደ ደረጃው ለይተን፣ የልጅነት የወጣትነት፣ የጎልማስነት<br>– የአእምሮ አሰራር ቀኙና ግራ<br>• ሲለበስ /ስነደ ትምህርት/ አይነቶችና ብያኔ<br>• የስዋስው ሲለበስ<br>• አካባቢያዊ ሲለበስ<br>• መልዕክት አዘል ሲለበስ<br>/... ተነፃጽረው ቀርበዋል/ | |

<u>የቋንቋ ማስተማር ዘዴ</u>

አባሪ 4-2

የኮርስ ርእስ አማርኛን የማስተማር ልዩ ዘዴ - II

የኮርስ ቁጥር Etl

ክሬዲት

የኮርሱ ዓላማዎች በዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ ተማሪዎች፡ የማስተማሪያ መሣሪያዎ ማዘጋጀትና መጠቀም ይችላሉ ::
የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት ይችላሉ
ትምህርትን መምረጥ፣ ማዘመድና ማዘጋጀት ይችላሉ ::
በናሙና ትምህርት ክፍል የተለያዩ የቋንቋ ማስተማር ዘዴዎችን ተግባራዊነት መሞከር ይችላሉ ::
የተለያዩ ፈተናዎች መለመጃዎችን ማዘጋጀት ይችላሉ
የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ሥርዓተ ትምህርትንና የማስተማሪያ መጻሕፍትን መገምገም ::

| የኮርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ፈተና |
|---|---|---|
| | | |
| የማስተማሪያ መሣሪያዎችን<br>መምረጥ፣ ማዋሀድ<br>/ማዘመድ/ ማዘጋጀት<br>የማስተማሪያ መርጃዎች<br>አጠቃቀም ዘዴ<br>የአማርኛ ሥርዓተ ትምህ<br>ርትንና መጻሕፍትንን<br>መተንተን<br>የትምህርት ዕቅድ<br>ማዘጋጀት<br>የተለያዩ የፈተና<br>ዓይነቶችን ማዘጋጀት<br>የናሙና ትምህርት /ንዑስ<br>ትምህርት/ | በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የንባብ<br>አገልግሎት<br>የቋንቋ ትምህርት ይዘት የተለ<br>ያዩ ጽሑፎችን ማንበብ<br>መደበኛ አጻጻፍ<br>ዘገባ<br>የማስተዋል፡ አንብቦ መረዳት<br>ቀጥተኛ ብልሃት<br>አስምርታዊ ብልሃት<br>ሥነ ጽሁፍን ለቋንቋ ማስተማር<br>እንዴት እንጠቀምበታለን<br>የቃላትን ትርጉም ለማወቅ<br>የቋንቋን ሥርዓት ለመልመድ<br>የሃሳብ ግኝት<br>የአፃፃፍ ቴክኒክ ለማሳያ<br>የዕለት ትምህርት ዝግጅት<br>የባሕርይ ለውጥ ለማምጣት<br>የንዑስ ማስተማር ልምምድ ውይይት<br>የተማሪ አስተማሪው የተሻለ ልምድ<br>እንዲያገኝ<br>በቡድን የማስተማር ጥቅም<br>ከጓደኞቻቸው እንዲማሩ<br>ሀሣብ የማካፈል ችሎታ<br>የቡድን ሀሣብ መስማት<br>ገዜ ይቆጥባል ::<br>ተማሪዎች [illegible]<br>[illegible] ጋር ይነጋገራሉ ::<br>[illegible] ዘር የማስተማር ዘዴ | የማስተማር |

ተጓዳኝ መስኮች

አባሪ 5-1

የኮርስ ርዕስ የመጀመሪያ ደረጃ ግዕዝ

የኮርስ ቁጥር Etl. 143

ክሬዲት 3

የኮርሱ ዓላማዎች በዚህ ኮርስ መጨረሻ ላይ ተማሪው:- የግዕዝን ግሶች ያረባል
ዐ. ነገር ይመሠረታል
ቃላት ይመሰርታል፣ እንዲሁም የግዕዝን ስዋስዋዊ ክፍሎች ይተነትናል
የግዕዝ ፅሁፍ አነባበ ይረዳል
ከግዕዝ ወደ አማርኛ ይተረጉማል ::

| የኮርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ፈተና |
|---|---|---|
| - የግዕዝ ተውላጠ ስሞች<br>- የግዕዝ ግሥ ሥርዐት<br>- ሌሎች የግዕዝ ስዋስዋዊ ምድቦች<br>- ቃላት ምሥረታ<br>- ዐረፍተ ነገር ምሥረታ<br><br>- የአማርኛ ውያዊ ቃላት ችግሮች በማቃለል ረገድ የግዕዝ ሚና<br>- ከግዕዝ ወደ አማርኛ<br>. የሀረገ ትርጉም<br>. ዐ. ነገር መተርጎም<br>. አንቀፅ መተርጎም | - ተውላጠ ሥም<br>-የግሦች ርባታ<br>- በፆታ በቁጥር<br>- በመደብ<br>. በጊዜ<br>-የግሥ ርባታ ዘሮች /መደቦች/<br>የቀተለ<br>ፈተለ<br>ተከለ<br>ነቀለ<br>ቀደሰ<br>-የግሥ ርባታ የሚጠብቁ/ የማይጠብቁ<br>- የግሥ አገሮች<br>ባለ ሁለት<br>ባለ ሦስት<br>- የግዕዝ ዐ. ነገር<br>- የግዕዝ ዐ. ነገር ትርጉም | የግዕዝ ትርጓሜ<br>-የስዋስው ክፍሎች<br>-የግሥ ርባታ<br>ከግዕዝ ወደ አማርኛ መተርጎም<br>ቃላት<br>- ሀረጋት<br>- ዐ. ነገሮች<br>-ከአማርኛ ወደ ግዕዝ<br>- መተርጎም<br>- ሀረጎች |

ተጓዳኝ [illegible] አባሪ 5-2

የኮርስ ርዕስ የትርጉም መግቢያ

የኮ.ስ ቁጥር Etla 212
ክሬዲት 2

የኮርሱ ዓላማዎች በዚህ ኮርስ መጨረሻ ተማሪው:-

- የትርጉም ጽንሠ ሐሣብና አስፈላጊነቱን ይረዳል
- በትርጉም ሥራ የሚከሠቱ ዋና ዋና ችግሮችን ይፈታል
- መሠረታዊ የአተረጓጐም ብልሃቶችን በሥራ ላይ ያውላል
- ጽሁፎችን ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ይተረጉማል

| የኮርሱ ቢጋር | የተማሪዎች ማስታወሻ | ፈተና |
|---|---|---|
| - የትርጉም ፋይዳና አገልግሎት<br>- የትርጉም ዐይነቶች<br>- በትርጉም ውስጥ ሙያ ነክ ቃላት/ተርሚኖሎጅስ/ የሚያስከትሉት ችግር<br>- ሙያዊና ዝርው ትርጉም<br>- የትርጉም ዋና ዋና ችግሮች<br>- ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ጽሁፎችን እየተረጐሙ መማር | ትርጉም ምንድን ነው<br>- ዓላማ<br>- ትርጓሜ<br>- የትርጉም ባሕርያት<br>- የአፃፃፍ ጥበብ ማወቅ<br>- የሁለት ቋንቋዎች ችሎታ<br>- የተርጓሚ ችግሮች<br>  - የቋንቋ<br>- ፍሬነገርን የመረዳት/ያለመረዳት<br>- የቋንቋ ውስጣዊ አደራደር<br>- ቅርጽን አለማወቅ<br>  - ባሕል<br>  - ዘይቤ<br>  - የጊዜ ርቀት | /ፈተናው ኮርሱ ባለማለቁ አለተጠመረም/ |

በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በኢትዮጵያ
ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ የሁለተኛ ዓመት
የዲግሪ ተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ

<u>ውድ ተማሪዎች</u>

የዚህ መጠይቅ ዓላማ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የዲግሪ መርሀ-ግብር ስለ ዐቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት አስተያየት መሰብሰብ ነው:: ጥናቱ የታለመለትን ግብ እንዲመታ ትክክለኛ መረጃ ማሰባሰብ ያስፈልጋል:: ስለዚህ እርስዎም በመጠይቁ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ አስተያየትዎን እንዲገልፁልኝ ስጠይቅ በትህትና ነው::

የትምህርት ጊዜዎን ሰውተው ይህን መጠይቅ በመሙላት ስለ ተባበሩኝ በቅድሚያ አመሠግናለሁ::

<u>ማሳሰቢያ</u>

በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አስፈላጊ አይደለም::

ሚያዝያ 1986 ዓ.ም

I. ከተ.ቁ. 1—3 ለተጠየቁት ጥያቄዎች፣ ተገቢ የሚሆኑትን መረጃዎች በተሠጡት ክፍት ቦታዎች ላይ ያስፍሩ::

1. ዕድሜ
2. ጾታ
3. ወደ ኮሌጅ ከመግባትዎ በፊት በማስተማር ሙያ ተሠማርተው ነበርን? አዎ______ የለም______

II. በዐቢይ የአማርኛ ኮርሶች ላይ የቀረቡ ጥያቄዎች

መመሪያ፣ ለእያንዳንዱ ጥያቄ በመልስነት ሊቀርቡ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ አምስት አማራጮች አሉ:: እነርሱም፣ 4/በጣም እስማማለሁ 3/እስማማለሁ 2/በመጠኑ እስማማለሁ 1/አልስማማም 0/በጣም አልስማማም የሚሉ ናቸው:: ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ትይዩ፣ ከ4—0 ተ.ቁ. የተመለከቱ ክፍት ቦታዎች በሠንጠረዥ ቀርበዋል:: ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሚሰጡትን አስተያየት በመምረጥ፣ በሠንጠረዡ ውስጥ ባለው ክፍት ቦታ x ምልክት ያድርጉ::

| | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. በኮሌጅ ውስጥ የተማርኳቸው አቢይ የአማርኛ ኮርሶች የሚከተሉትን የቋንቋ ክሂሎች በተመጣጠነ ቅንብር አቀርበውልናል:: | | | | | |
| ሀ. ማዳመጥን | | | | | |
| ለ. መናገርን | | | | | |
| ሐ. ማንበብን | | | | | |
| መ. መጻፍን | | | | | |
| 2. በአቢይ ኮርሶች ይዘት ውስጥ የሚከተሉትን የቋንቋ ክሂሎች ለማስተማር በቂ ልምምድና ክኀጅት አገኘቻለሁ:: | | | | | |
| ሀ. ማዳመጥ | | | | | |
| ለ. መናገር | | | | | |
| ሐ. ማንበብ | | | | | |
| መ. መፃፍ | | | | | |

| | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
|---|---|---|---|---|---|
| 3. በአቢይ ኮርሶች አማካይነት ሥነልሳን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሚጫወተውን ሚና በሚገባ ተረድቻለሁ፡፡ | | | | | |
| ሀ. የቋንቋን አጠቃላይ ባሕርይ በሚመለከት | | | | | |
| ለ. የአማርኛን ድምጾችና ምዕላዶች በሚመለከት | | | | | |
| ሐ. የአማርኛን ሰዋሰዋዊ መዋቅር በሚመለከት | | | | | |
| መ. ሥነ-ልሳን የማስተማሪያ መሣሪያን ለመምረጥ የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ | | | | | |
| ሠ. ሥነ-ልሳን ለመርሀ ትምህርት /ሰነደ ትምህርት አዘገጃጀት ያለውን አስተዋፅኦ | | | | | |
| 4. አቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ውስጥ የአማርኛን ቋንቋ ለየ ለየ አገልግሎት ተገንዝቤያለሁ፡፡ | | | | | |
| ሀ. በሥነ-ጽሑፍ ዘርፎች | | | | | |
| ለ. በመገናኛ ብዙሃን | | | | | |
| ሐ. በሕብረተሰቡ ውስጥ በሚሰጠው የመግባቢያ አገልግሎት | | | | | |
| 5. በአቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ውስጥ አማርኛን የማስተማሪያ ዘዴ ተረድቻለሁ፡፡ | | | | | |
| ሀ. በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደትን ለመቆጣጠር የሚያስችለኝን ስልት አውቄያለሁ፡፡ | | | | | |
| ለ. በአማርኛ አፍ የፈቱትንና ያልፈቱትን በተለያዩ ዘዴ ለማስተማር የሚጠቅም ስልት ተገንዝቤያለሁ፡፡ | | | | | |
| ሐ. በተማሪዎች መካከል የሚኖር ግላዊ ልዩነትን ለማገናዘብ የሚያስችለኝን ዘዴ አገኝቻለሁ፡፡ | | | | | |
| 6. በአቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ውስጥ ተገቢው ትኩረት ያልተሰጠው፡- | | | | | |
| ሀ. ማዳመጥ ነው | | | | | |
| ለ. መናገር ነው | | | | | |
| ሐ. ማንበብ ነው | | | | | |
| መ. መጻፍ ነው | | | | | |

| | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
|---|---|---|---|---|---|
| 7. በአቀራረቡ ሁለተኛ ደ/ት/ቤት የማስተማር ልምምድ ወቅት የአቢይ ኮርሶች አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነበር፡፡ | | | | | |
| ሀ. የዕለት ትምህርት ዕቅድ በማዘጋጀት ረገድ | | | | | |
| ለ. የትምህርት ይዘትን በመምረጥ ረገድ | | | | | |
| ሐ. ከማስተማሪያ መጽሐፍ ጋር በመተዋወቅ ረገድ | | | | | |
| መ. ከመርሀ-ትምህርት ጋር በመተዋወቅ ረገድ | | | | | |
| ሠ. የክፍል ውስጥ የተማሪ አስተማሪን ተራክቦ በማስገንዘብ ረገድ፡፡ | | | | | |
| ረ. ፈተና በማዘጋጀት ረገድ | | | | | |
| 8. በማስተማር ልምምድ ወቅት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ለማሟላት የአቢይ ኮርሶች ይዘት ረድተዋል፡- | | | | | |
| ሀ. የዕለት ትምህርት ርዕስ ጉዳይን በመምረጥ | | | | | |
| ለ. ለክፍል ውስጥ ሥነ-ሥርዓት አጠባበቅ | | | | | |
| ሐ. ከተማሪዎች የሚነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ | | | | | |
| መ. የተማሪዎችን ፍላጎት ለመረዳት | | | | | |
| ሠ. የተማሪዎችን ችሎታ ለመለየት | | | | | |
| 9. በአቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ውስጥ ተገቢው ትኩረት ያልተደረገበት፡- | | | | | |
| ሀ. የቋንቋ ክሂል ክፍል ነው | | | | | |
| ለ. የሥነ-ጽሑፍ ክፍል ነው | | | | | |
| ሐ. የሥነ-ልሣን ክፍል ነው | | | | | |
| መ. የሥነ-ዘዴ ክፍል ነው | | | | | |
| ሠ. የቋንቋ ፈተና አዘገጃጀት | | | | | |
| 10. አቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ለማዘጋጀት የሚያስችል ልምድ ተካቷል፡፡ | | | | | |
| ሀ. በክፍል ውስጥ ቋንቋን የመፈተንን ዓላማ በመረዳት ረገድ፡- | | | | | |

| | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
|---|---|---|---|---|---|
| ለ. በቋንቋ ፈተና ውስጥ የሚካተቱ የቋንቋ ፈተና ይዘቶችን በመምረጥ ረገድ | | | | | |
| ሐ. በልዩ ልዩ የቋንቋ ፈተና ዓይነቶች መናራ ቸውን በመገንዘብ:- | | | | | |
| መ. የቋንቋ ፈተና ለመማር ማስተማሩ ሂደት የሚሰጠውን አስተዋፅኦ በመረዳት ረገድ | | | | | |
| 11. አበይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት፣ ለአማርኛ ቋንቋ መዓበር አጋዥ /ደጋፊ/ የሆኑ መረጃዎችን በመጠቀም ረገድ ተገቢ ትኩረት ተሰጥቷል | | | | | |
| ሀ. ምርምርና የዘገበ አፃፃፍ | | | | | |
| ለ. ትርጉምና አገልግሎቱን | | | | | |
| ሐ. ገዐዝና ለአማርኛ ቋንቋ የሚሰጠው ድጋፍ | | | | | |
| 12. በአጠቃላይ በአበይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች ያተኮሩት | | | | | |
| ሀ. በቋንቋ ክሂሎ ላይ ነው | | | | | |
| ለ. በቋንቋና ሥነ-ልሣን ላይ ነው | | | | | |
| ሐ. በሥነ-ዘዴ ላይ ነው | | | | | |
| መ. በተጓዳኝ ደጋፊ መስኮች ላይ ነው | | | | | |
| ሠ. በሥነ-ጽሑፍ ትምህርቶች ላይ ነው | | | | | |
| ረ. በሁሉም ላይ የተመጣጠነ ትኩረት ያደርጋሉ:: | | | | | |
| 13. በአበይ ኮርሶች ማጠቃለያ ላይ የሚቀርቡልዎ ፈተና የሚያመኩነው፣ | | | | | |
| ሀ. በምርጫ ጥያቄዎች ላይ ነው | | | | | |
| ለ. ባዶ ቦታ በመሙላት ላይ ነው | | | | | |
| ሐ. አዛምዶ በመመለስ ላይ ነው | | | | | |
| መ. እውነት ውሸት ላይ ነው | | | | | |
| ሠ. አጪጭር የጽሑፍ መልስ በመጠየቅ ላይ ነው | | | | | |
| ረ. ሰፋ ያለ ማብራሪያ በመጠየቅ ላይ ነው | | | | | |
| 14. በአበይ የአማርኛ ትምህርቶች ሂደት ውስጥ ስራ የጥናት ርዕስ /ሲሚስተር ወረቀት/ ተሰጥቶዎት ስርተው ለመምህርዎ አስረክበው ያውቃሉ:: | | | | | |
| 15. የሰሩት የሲሚስተር ወረቀት ታርሞ ተመለሰለዎታል:: | | | | | |
| 16. ወረቀትዎ ታርሞ ከተመለሰልዎ እርማቱ የሚያተኩረው | | | | | |
| ሀ. በፍሬ ነገሩ ላይ ብቻ ነው | | | | | |
| ለ. የቋንቋው ቀንበር ግምር ይታረማል | | | | | |

III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ያለዎትን አስተያየት በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ ይጻፉ::
/የመመለሻ ቦታ ቢጠብዎ በጀርባው ባለው ቦታ መጠቀም ይችላሉ/

17. በአቢይ የአማርኛ ኮርሶች ይዘት ውስጥ ለአማርኛ ማስተማር አያገለግልም የሚሉት የትምህርት ይዘት ካለ፣ ከነምክንያትዎ ይግለጹ::

18. ከአቢይ የአማርኛ ኮርሶች ውስጥ የበለጠ ይስፋፋ የሚሉት ካለ ከነምክንያቱ ይግለጹ::

19. አበይ የአማርኛ ክርሶችን ይዘት በሚመለከት የሚሰነዝሩት ሀሳብ ካለ ያብራሩ:: /በመጠይቁ ውስጥ ከቀረቡት ጥያቄዎች ውጭ/

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የእኔ የግል ሥራ መሆኑንና በጽሁፉ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ተዛማጅ ጽሁፎችና መረጃዎች በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ::

ስም ደረጀ ገበሬ

ፊርማ ____________

ቦታ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ቀን ሰኔ 9/1986